# አዲስ ዘመን

አንድ

እሁድ 81ኛ ዓመት ቁጥር 345 ነሐሴ 15 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## ‹‹መንግሥት ለሰላም እጁን ቢዘረጋም አሸባሪው ሕወሓት የሀሰት ትርክት በመደርደር ለሰላም ዝግጁ አለመሆኑን እያሳየ ነው››

- ዶክተር ለገሰ ቱሉ
የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር



**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት ለሰላም እጁን ቢዘረጋም አሸባሪው ሕወሓት ግን ያደገበትን የሀሰት ትርክት በመደርደር ለሰላም ዝግጁ አለመሆኑን እያሳየ ነው ሲሉ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዶክተር ለገሰ ቱሉ አስታወቁ፡፡

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዶክተር ለገሰ ቱሉ በወቅታዊ አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ መንግስት በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ያለውን ችግር በሰላም እንዲፈታ ከሕወሓት ጋር ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ድርድር ለማድረግ ዝግጁ ነው፡፡ይህም መንግስት ለሰላም ያለውን ጽኑ አቋም ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ ሕወሓት ያደገበትን የሀሰት ትርክት በመደርደር ለሠላም ዝግጁ አለመሆኑን አሳይቷል፡፡ ከሰሞኑ በአፈቀላጤው ጌታቸው ረዳና በዓለም ጤና ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ቴድሮስ አድሃኖም እየተሰጡ ያሉ የተፈበረኩ መረጃዎችም ሕወሓት ለሰላም ዝግጁ አለመሆኑን የሚያሳዩ ናቸው ፡፡

‹‹መንግሥት ለሰላም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






## የዋጋ ንረትን በዘላቂነት ለመቆጣጠር ድጎማና የዋጋ ጣሪያ ማስቀመጥ እንደሚገባ ተጠቆመ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- በገበያው የሚስተዋለውን የዋጋ ንረት ለማስተካከል በመሰረታዊ ፍጆታዎች ላይ ድጎማ ማድረግና አይነቶችን አጥንቶ የዋጋ ጣሪያ ማስቀመጥ እንደሚገባ በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሃብት ባለሙያ፣ መምህርና ተመራማሪ ዶክተር ዱጋሳ ሙሉጌታ ገለጹ።

ዶክተር ዱጋሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ለሚስተዋለው የዋጋ ንረት በመሰረታዊ ፍጆታዎች ላይ ድጎማ ማድረግና አይነቶችን አጥንቶ የዋጋ ጣሪያ ማስቀመጥ ያስፈልጋል።

የዋጋ ንረቱ ሕዝቡን እያማረረ እንዳይቀጥል ወቅታዊና ፈጣን እልባት ሊሰጠው ይገባል። አጋጣሚን በመጠቀም ለፖለቲካ ፍጆታ እንዳይውል መንግስት በገበያ ውስጥ ያለውን ሕገ ወጥ አሰራር ማጥራት፣ የደህንነት ስራውንም ማጠናከር እንዳለበትም ተናግረዋል።

ግሽበት ባይመጣ ጥሩ ቢሆንም በኢኮኖሚው ግን ማስወገድ አይቻልም ያሉት ዶክተር ዱጋሳ፤ የራሱን ቀመር ተከትሎ መስራትና የመጣው በምን ምክንያት እንደሆነም መታየት እንዳለበት አመልክተዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ግሽበት በአቅርቦት እና ፍላጎት አለመጣጣም ሊፈጠር ይችላል፣ ሰው ሰራሽ ግሽበትም አለ። ኮቪድ፣ የውስጥ ችግር፣ የራሺያና የዩክሬን ጦርነት ከአለም አቀፍ

የዋጋ ንረትን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡- አዩብ ተፈሪ

ዶክተር ዱጋሳ ሙሉጌታ

## በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ የሚያጋጥሙ የሀሰት ማስረጃዎችን መከላከል የሚያስችል ስርዓት እየተዘጋጀ ነው

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ የሚያጋጥሙ የሀሰት መረጃዎችን ለመከላከል የሚረዳ ስርዓት እየተዘጋጀ መሆኑን የሥራና ክህሎት ሚኒስቴርና የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ገለጹ።

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴርና የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት "የተቀናጀ የሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ሠርቲፊኬት ሲስተም" ማልማት የሚያስችል ስምምነት ትናንት ተፈራረሙ።

ስምምነቱን የፈረሙት የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል እንደተናገሩት፤ በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ የተለያዩ የሃሰት ማስረጃዎች ያጋጥማሉ። በቀጣይ ትውልድ ገዳይ የሆነውን የሃሰት ማስረጃ ለመከላከል ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ ይውላል።

በመላ አገሪቷ ከአንድ ሺህ 800 በላይ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት መኖራቸውን የገለጹት ሚኒስትሯ፤ አዲስ የሚለማው የቴክኖሎጂ ስርዓት ተቋማት አሰራራቸው በዕውነት ላይ የተመሰረተ እንዲሆንና ዜጎች በትክክለኛ ማስረጃ ብቻ እንዲገለገሉ የሚረዳ ነው ብለዋል።

ሰዎች የሌላቸው ክህሎት እንዳላቸው ተደርጎ በሃሰት ማስረጃ አማካኝነት ወደሥራ ሲገቡ እንደ አገርም የሚያስከትለው ጉዳት ከፍተኛ መሆኑን የጠቆሙት ወይዘሮ ሙፈሪያት፤ በተመሳሳይ የሙያ ብቃት ምዘና ሳያገኙ ወደ ውጭ አገራት ለሥራ እንደሚሄዱ ዜጎችም በግላቸው ለጉዳት እንደሚጋለጡ ገልጸዋል።

አዲስ የሚለማው ቴክኖሎጂ ችግሩን በመቅረፍ

በቴክኒክና ሙያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






## በጦርነቱ ጉዳት ከደረሰባቸው 536 የጤና ተቋማት 463ቱ አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል

ገጽ 4



ዜና

# ቢሮው ተቋማት ከብልሹ አሠራር የፀዳ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት እንደሚገባቸው አሳሰበ

## - በከተማ አስተዳደሩ ተቋማት መካከል በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ስምምነት ተፈርሟል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ተቋማት ከብልሹ አሠራር የፀዳ ቀልጣፋ አገልግሎት ለዜጎች ለመስጠት ከመቼውም ጊዜ በላይ መሥራት እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ አሳሰበ፡፡

በቢሮውና በከተማ አስተዳደሩ ሥር በሚገኙ 55 ተቋማት መካከል በ2015 በጀት ዓመት በቅንጅት በሚከናወኑ ተግባራት ላይ የተሻለ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል የውል ስምምነት ተፈርሟል።

በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃይል ልማት ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሒክማ ከይረዲን በወቅቱ እንደገለጹት፤ የሚፈለገው ውጤት እስኪመጣ ድረስ ተቋማት ከብልሹ አሠራር የፀዳ ቀልጣፋ አገልግሎት ለዜጎች ለመስጠት ከመቼውም ጊዜ በላይ በቁርጠኝነት መሥራት አለባቸው።

ተቋማት ለዜጎች የሚሰጡት አገልግሎት ፈጣንና ቀልጣፋ ለማድረግ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል ያሉት ወይዘሮ ሒክማ፤ በ2014 የተለያዩ የሕግ ማዕቀፎችን በማሻሻልና ተቋማዊ ለውጥ በማካሄድ የአገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል ጥረት መደረጉን ጠቁመዋል።

በተከናወኑ ሥራዎች መሻሻሎች ቢኖሩም አሁንም ዜጎች በተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የተለያዩ ቅሬታዎችን ያቀርባሉ። በ2015 በጀት ዓመት ፈጣን፣ ቀልጣፋና ከብልሹ አሠራር የፀዳ አገልግሎት ለመስጠት በቅንጅት መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል።

በ2014 በጀት ዓመት ዜጎች የሚያነሱትን ጥያቄ መነሻ በማድረግ ተቋማትን መልሶ የማደራጀት ሥራ ተሠርቷል ያሉት ኃላፊዋ፤ መሻሻሎች ቢኖሩም ዜጎች ከሚያነሱት ጥያቄ አንጻር አመራሩ የተሰጠውን ኃላፊነት በውጤታማነት መምራት ይገባዋል። ሠራተኛውም የተሰጠውን የሙያ ኃላፊነት በጥሩ ስነምግባር መወጣት አለበት ሲሉ ገልጸዋል።

የቢሮው አንዱ ተልዕኮ ተቋማት ውጤታ የሆነ አሠራርና አደረጃጀት እንዲዘረጉና ለዜጎች ተደራሽ የሆነ አገልግሎት እንዲሠጡ ማገዝ መሆኑን አስታውሰው፤ ተገልጋዮች የሚያነሱትን ቅሬታ መነሻ በማድረግ የመንግሥት አገልግሎቶችን በተሻለና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲመሩ ክትትል እንደሚደረግ ጠቁመዋል።

በተቋማት ውስጥ ግልጽነትና ተጠያቂነት ማስፈን የተገልጋዩን እርካታ ለማሳደግ እንደሚያግዝ አመልክተው፤ ለዚህም በከተማ አስተዳደር ደረጃ ሌብነትና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚረዳ ዕቅድ መዘጋጀቱን ገልጸዋል።

የየተቋማቱ አመራርና ሠራተኛ የአገልጋይነት ስሜትን ተላብሶ ከሙስናና ብልሹ አሠራሮች በራቀ መንገድ ሕዝብን ማገልገል እንደሚገባው አስገንዝበው፤ ችግር በተገኘበት ወቅት አስፈላጊው የማስተካከያ ርምጃ እንደሚወሰድ አሳስበዋል።


አገልግሎቶችን ለዜጎች ተደራሽ ለማድረግ በሚከናወኑ ጥረቶች ውጤታማ ለማድረግ የለሙ ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል ያሉት ወይዘሮ ሒክማ፤ በዚህም ብልሹ አሠራሮችን በማስወገድና ለዜጎች ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት ውጤት ማምጣት ይቻላል ብለዋል፡፡

የመንግሥትን አገልግሎት ዜጎች በሚፈልጉት መልኩ አቀናጅቶ በመስጠት በኩል ያለውን ጉድለት በትብብር በመሙላት በ2015 የተሟላ አገልግሎት ለመስጠት በቁርጠኝት መሥራት አለብን ሲሉም መልዕክት አስተላልፈዋል።



**ወይዘሮ ሒክማ ከይረዲን**

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃይል ልማት ቢሮ እና በከተማ አስተዳደሩ ተቋማት መካከል በቅንጅት ለመሥራት የሚያግዘው የውል ስምምነት ግልጽነትና ተጠያቂነትን በማስፈን ለዜጎች ፈጣን፣ ቀልጣፋና ከአድሏዊ አሰራር የፀዳ አገልግሎት ለመስጠት እንደሚያግዝ ተገልጿል፡፡



**አርቲስት ፋንቱ ማንደዩ**



**አርቲስት እንቁሥላሴ ወልደአገኝ**

# ሙዳይ የበጎ አድራጎት ማህበር ለሶስት ቀን የሚቆይ የባህል ሳምንት እያከበረ ነው

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- ሙዳይ የበጎ አድራጎት ማህበር ከነሐሴ 13 እስከ 15 ቀን 2014 ከአዲስ አበባ ባሕል፣ የኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር የባህል ሳምንት እያከበረ ነው።ማህበሩ ለተቸገሩ ሕጻናት እና እናቶች ሁሉም ወገን በአለው አቅም ልክ ድጋፍ እንዲያደርግም ጥሪ ቀርቧል።

ነሐሴ 13 በተካሄደው የባህል ሳምንት ማስጀመሪያ የቡሄ፣ የአሸንዳ፣ ሻዕደይና የሶለል በዓል በሙዳይ በጎ አድራጎት የተለያዩ ታዋቂ አርቲስቶችና ኮሜድያን በተገኙበት ተከብሯል።

የሙዳይ በጎ አድራጎት መስራች ወይዘሮ ሙዳይ ምትኩ የባህል ሳምንቱ ዋነኛ ዓላማ ሀገር ተረካቢ ልጆቻችን ባህላቸውን አውቀው እንዲያድጉ ማስተማር አለብን ብለዋል።

አገር ተረካቢ የሆኑት ልጆቻችን ኢትዮጵያ ምን ምን ባህሎች እንዳሏት ጠንቅቀው እንዲያውቁ ማሳየት እንደሚገባም ገልጸዋል።

የሙዳይ በጎ አድራጎት ማህበር የሰው ሀብት አስተዳደር አቶ መስፍን ሞገስ በበኩላቸው፤ ማህበሩ ከአንድ ሺህ 100 በላይ ህጻናትና እናቶች የአልባሳት፣ የሙሉ ጤና ምርመራ አገልግሎት እንዲያገኙ በማስቻል የበጎ አገልግሎት ስራዎችን እየሰራ እንደሚገኝ ጠቅሰዋል።

ማህበሩ 650 ህጻናት የምግብ፣ የመጠለያ ፣የህክምና፣ የትምህርት የአልባሳት እና የንፅህና መጠበቂያ ድጋፍ የሚያደርግ መሆኑን ጠቁመው፤ ለ450 እናቶች የምግብ፣ የመጠለያ፣ የአልባሳት፣ የንጽህና መጠበቂያ የህክምና እና የሙያ ሥልጠና ድጋፍ እያደረገ ነው። ከእህት ኩባንያዎች ጋር በመተባበርም ለ1000 እናቶች የስራ ዕድል ፈጥሯልም ብለዋል።

እናቶች ከተረጂነት ስሜት ተላቀው እራሳቸውንና ልጆቻቸውን ማስተዳደር እንዲችሉ የመልሶ ማቋቋም ስራ በልዩ ትኩረት እየሰራ መሆኑንም ገልጸዋል።

ማህበሩ ላለፉት 22 ዓመታት በሰራው የበጎ አድራጎት ስራው ከአንድ ሺህ 500 በላይ ሰዎች እራሳቸውን እንዲችሉ ማድረጉን ገልጸው፤ በአሁኑ ጊዜም በሁሉም ፕሮጀክቶች ሁለት ሺህ 650 ቀጥተኛ ተጠቃሚዎችን እና 18 ሺህ 850 ቀጥተኛ ያልሆኑ ተጠቃሚዎችን ተደራሽ እያደረገ መሆኑንም አመላክተዋል።

ሙዳይ በጎ አድራጎት ማህበር በ2014ዓ.ም በሰሜን ኢትዮጵያ በተፈጠረው ግጭት ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ እና ከወላጆቻቸው ጋር የተጠፋፉ ልጆችን አሰባስቦ መጠለያ ጣቢያ ውስጥ በማስገባት የምግብ፣ የአልባሳት እና የተለያዩ ድጋፎችን እያደረገ በመሆኑ ትልቅ ኩራት እንደሚሰማው ገልጸዋል።

በጦርነቱ ምክንያት ጥቃት ለደረሰባቸው ከ500 በላይ ሴቶች በስነልቦና ስልጠና እና ሙሉ የህክምና ድጋፍ በማድረግ ላይ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ማህበሩ በገርጂ፣ በኮተቤ እና በአቃቂ በጎርፍ እና በተለያዩ የተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው ለሚገኙ ሰዎች የማዕድ ማጋራት ስራዎችን ማድረጉን ገልጸዋል።

በቀጣይም በመንግሥት የተፈቀደለትን ቦታ ሲረከብ መጠነ ሰፊ ድጋፍ ለማድረግ መዘጋጀቱን በመግለጽ፤ በሀገር ውስጥ እና በውጭ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አስተላልፈዋል።

አርቲስት ፋንቱ ማንዶዬ ሙዳይ በጎ አድራጎትን ሲጎበኙ የመጀመሪያ ጊዜያቸው መሆኑን ገልጸው፤ ማህበሩ ትልቅ ኃላፊነት ወስዶ ወላጅ የሌላቸው፣ ማየት እና መስማት የማይችሉ ህጻናትን ጭምር አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረጉ የሚመሰገን ተግባር ነው ብለዋል።

አርቲስት እንቁሥላሴ ወልደአገኝ በበኩላቸው፤ በሙዳይ በጎ አድራጎት የሚታዩትን የነገ ሀገር ተረካቢ የሆኑ ተተኪ ትውልድ መርዳት እንደሚገባ ጠቁመዋል። የነገሀገር ተረካቢ ህፃናት ላይ የበጎ አድራጎት ሥራዎች ለመሥራት በግላቸውም በሙያቸው ለማገዝ ቃል ገብተዋል።

ኮሜዲያን አዝመራው ሙሉሰው በበኩሉ፤ እንደ ሙዳይ ያሉ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን መደገፍና የተለያዩ በዓላትን አብሮ ማክበር እንደሚገባ ገልጿል። ሳቄንም ጨዋታዬንም በሙዳይ በጎ አድራጎት በማካሄድ እደግፋለሁ ሲሉ አርቲስቶቹ ቃል ገብተዋል።

# ቡሄን በበጌምድሯ እንቁ ደብረታቦር

**ዳግማዊት ግርማ**

ያለፈውን ዓመት ክፉ በመልካም ትዝታ ለመተካት ጥሩውን በናፍቆት ለማስታወስ ወጣ ገባ በሚባልባት ነገን በተስፋ በሚጠበቅባት በዓመቱ አስራ ሁለተኛ ወር በሆነችው ወርሀ ነሀሴ ላይ ነን።

ክረምት ሊወጣ በጋው ሊመጣ ሀገሬው በአዲስ ዓመት “እንቁለጣትሽ” ሊል ልብን በተስፋ ሊሞላ ሲሻ የነሀሴን ወር በቡሄ፣ በሻደይ፣ ሶለልና አሸንድዬ በዓል ድልድይነት ላይ ይረማመዳል።

የቡሄ በዓል ከነ ሙሉ ክብሩ በደብረታቦር ከተማ ላይ አለ። ደበረታቦር የቡሄ በዓል በሚከብርባት ሰሞን ለሰርጓ ብዙ ጥሎሽ እንደተጣለላት አዲስ ሙሽራ ፍንክንክ ስትል ትከርማለች።

በሷ መኖር መልካም የሆነልን እኛ ከብዙ ጋቢዎች አምልጦ በሚጋረፈው ብርድ በምትታወቀው በታቦር ተራራዋ እመቤት ታዛ ስር ተጠልለናል።

ቡሄ ከአሸንድዬ ጋር ተጣምሮ በሚከበርባት ውቧ ከተማ ከሰላሳ በላይ ሚዲያዎች ከደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ በተደረገልን ጥሪ መሰረት እንግዳ ሆነን ተገኝተናል።

ደብረታቦር ከተማ ከተለያዩ ስፍራዎች የመጡ እሷን ባይ ወገኖቿን መቀነቷን ታጥቃ ስታስተናግድ ከርማለች።

የቡሄ በዓል በንጋት ኮከብነት ላለችበት ደቡብ ጎንደር ዞን ብቻ ሳይሆን ለመላው የአማራ ክልል ብሎም ለመላው ኢትዮጵያ ኩራትና ክብር ነው።

የቡሄ በዓል መጠሪያ በሆነው ደብረ ታቦር በተሰየመችው በደብረ ታቦር ከተማ ሌላ ውብ መልክ አለው። ሃይማኖታዊውንም ትውፊታዊውንም ሚናውን ይወጣል።

ደብረታቦርን በደብረታቦር የተሰኘው ሰናይ ሃሳብ በደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ ሃሳብ ጠንሳሽነት እንዲሁም የበላይ አመራርነት ስር ኗሪ ነው። የድግሱ ባለቤት እንግዶቹን ለመቀበል ሽብረብ ሲያበዛ የከረመው የደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ ነው።

ቡሄ በመባል የሚታወቀው የደብረታቦር በዓል ደብረታቦርን በእንግዳ ዶፍ አጥለቅልቋታል። የከተማዋ ነዋሪዎች የአምናውን የጠላት ወረራ አሸንፈው ለዛሬ ቀን እንዲደርሱ ያደረጋቸውን አምላካቸውን ከማመስገን አልቦዘኑም።

የቡሄ ወይም የደብረታቦር በዓል መሰረት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ሲሆን በእምነቱ አስተምህሮ መሰረትም ኢየሱስ ክርስቶስ በደቀመዛሙርቱ ፊት ብርሃነ መለኮቱን በደብረ ታቦር ተራራ ላይ ከመግለጡ ጋር ተያይዞ ነው። ቡሄ ማለት ብራ፣ ብርሃን፣ ደማቅ የሚል ትርጉም አለው፡፡

ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናትም ባህሉም ሃይማኖቱም ሀገርን ጠቃሚ ነው ብለው ከጉዳያቸው ፅፈው ከበዓሉም ለመሳተፍ መልእክታቸውንም ለማስተላለፍ በከተማዋ ተገኝተዋል።

የቡሄ በዓል በተከበረበት ደብረታቦር ከተማ በታቦር ተራራ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን በሃይማኖታዊና ትውፊታዊ ስርዓቶች ተከብሯል።




በበዓል አከባበሩ ላይ ከታደሙት የመንግስት ተሿሚዎች መሀል አንዱ የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል ናቸው። እርሳቸውም በወቅቱ ባስተላለፉት መልዕክት የቡሄን እሴት ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስቀጠል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ኃላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው ሲሉ ተናግረዋል።

ሚኒስትሩ የቀደሙ አባቶችና ትውልዶች የቡሄ በዓል ሊከበርባት ትውፊታዊና ሃይማኖታዊ ይዘት ሳይለቅ ዛሬ ላይ ለመድረስ የከፈሉትን ብዙ ዋጋ አላሳጡትም፤ ይልቁንም ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎችም እሴቱን ለማቆየት ብዙ የቤት ስራዎች ይጠበቁባቸዋል ሲሉ አደራቸውን ይመለከታቸዋል ላሏቸው አካላት ሰጥተዋል።

ሚኒስትሩ የዘንድሮውን የደብረታቦር በዓል ሲያከብሩ አምና በዚህ ጊዜ በከተማዋ ስለነበረው ውጥንቅጥም አልዘነጉም ነበር። መከላከያ ሰራዊት፣ ልዩ ሀይልና ፋኖ በመተባበር አሸባሪውን ሕወሓት አከርካሪው ተመቶ ከከተማዋ የተመለሰበት ቀን መሆኑን ጭምር ነው ሚኒስትሩ ያወሱት።

የድግሱ ባለቤት የደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር አነጋግረኝ ጋሻውም በበኩላቸው፤ ሀሳቤን ገላጭ ነው ያሉትን በዓሉንና ህዝቡን የሚመለከት መልዕክት አስተላልፈዋል።

ኢትዮጵያዊ ባህሎች እየጠፉና በውጭና መጤ ባህሎች እየተወረሩ መምጣታቸውን በማሰብ ዩኒቨርሲቲው የቡሄን በዓል ለማክበር ተነሳስቶ አራተኛ ዙር ላይ መድረሱንም ነው ዶክተር አነጋግረኝ ጋሻው የገለፁት።

ዶክተር አነጋግረኝ አምና ከሕወሓት ጋር በነበረው ጦርነት ምክንያት ከተማይቱ የደብረታቦር በዓልን ማክበር አለመቻሏንም በፀፀት አውስተውታል።

የዛሬ ዓመት በዚህ ጊዜ በነበረው አስከፊ ሁኔታ ምክንያት መከላከያ ሰራዊት እና ህዝቡ ባይቀለብሱት ኖሮ ከተማችን ላይ ከፍተኛ ውድመት ይፈጠር ነበርም ነው ፕሬዚዳንቱ ያሉት።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ የሆኑት ዶክተር ሂሩት ካሳውም በበዓል አከባበሩ ላይ ከታደሙት የመንግስት የስራ ኃላፊዎች አንዷ ናቸው።

ዶክተር ሂሩት በመልእክታቸው ኢትዮጵያ የታሪክና የሃይማኖት ሀብታም እንደሆነች በመመስከር የቡሄ በዓል ሃይማኖታዊና ትውፊታዊ ትሩፋቱ ከኢትዮጵያ አልፎ አለማቀፋዊ መሆን እንደሚችልም ጠቁመዋል።

ዶክተር ሂሩት ታሪክን አምጠው ወልደው ለትወልድ ላስተላለፉ እናት አባቶች ምስጋናቸውን አቅርበው ለከርሞ በሰላም በፍቅር እንዲያደርሰን መልካም ምኞታቸውን አስተላልፈዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ ለሰላም መንገዱ ስኬት እንቅፋት እየሆነ ባለው አሸባሪው ሕወሓት ላይ ጫና ሊያደርግ ይገባል!

የኢትዮጵያ መንግስት በሰሜን ኢትዮጵያ ለተፈጠረው ችግር ዘላቂ መፍትሄው ሰላማዊ አማራጭ መሆኑን በጽኑ ያምናል።ማመን ብቻም ሳይሆን ለተግባራዊነቱም ተጨባጭ እርምጃዎችን እየወሰደ ይገኛል። ይህንንም በተለያዩ ወቅቶች አረጋግጧል። አሁንም እያረጋገጠ ይገኛል።

መንግስት ለሰላም ቁርጠኛ መሆኑን ከህግ ማስከበር እንዲሁም ከህልውና ዘመቻዎቹ በፊትም አሳይቷል፤ ጦርነት ውስጥ እንዳይገባ ብዙ ጥሯል ። ጦርነት ብዙ ዋጋ እንደሚያስከፍል ሰላማዊ አማራጭ ጥሩ መፍትሄ መሆኑን በተለያዩ መንገዶች አስታውቋል። አሸባሪው ህወሓት ራሱ በለኮሳቸው ጦርነቶች ድል ተመትቶም፣ አሸናፊነት በመንግስት መዳፍ ውስጥ ሆኖም መንግስት ሰላማዊ አማራጭ ወሳኝ መሆኑን በማመን ስለሰላም ሰርቷል፤ በህልውና ዘመቻው ማግስት በጦርነቱ የተማረኩ የቡድኑን ከፍተኛ አመራሮች ጭምር ከእስር በመፍታት ትልቅ ዋጋ ያስከፈለ እርምጃ መውሰዱም የዚሁ ቁርጠኝነቱ ማሳያ ነው።

የአፍሪካ ህብረት ለሰሜኑ ግጭት ሰላማዊ መፍትሄ ለማምጣት መንቀሳቀስ ሲጀምርም ጉዳዩን ወዲያው ተቀብሎ አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ ሲያደርግ ቆይቷል፤ ይህን ያደረገው ለዲፕሎማሲ ፍጆታ ሳይሆን ዘላቂ ሰላም ለማምጣት የሚደረግ የትኛውም ጥረት ዋጋ እንዳለው በመገንዘብ ነው። ከዚህም አልፎ በሰላም ውይይቱ የሚሳተፍ አብይ ኮሚቴ በመሰየምና ወደ ስራ በማስገባት በኩልም ፈጥኖ ተንቀሳቅሷል።

አብይ ኮሚቴውም ፈጥኖ የሰሜኑን ግጭት በዘላቂነት ለመፍታት የተኩስ አቁም ስምምነት ላይ በአጭር ጊዜ ውስጥ መድረስ እንዳለበት አጽንኦት በመስጠት፤ የሰላም ሂደቱን ለማፋጠን ይረዳ ዘንድም ወደ ተኩስ አቁም ስምምነት ሊያደርስ የሚችል እና ለቀጣይ የፖለቲካ ውይይቶች መሰረት በሚጥል የሰላም ምክረ ሀሳብ ላይ ውይይት በማድረግም የምክረ ሀሳብ ሰነድ አዘጋጅቶ ለአፍሪካ ህብረት ከፍተኛ ወኪል እንዲቀርብ መወሰኑም የዚሁ ለሰላም ያለው ቁርጠኝነት ማሳያ ነው ።

የሰላም ንግግር ግን በአንድ ወገን በሚደረግ ጥረት ብቻ ፈጽሞ ስኬታማ ሊሆን አይችልም። በመንግስት በኩል ጥረቱ በተጨባጭ የሚታይ ቢሆንም ፣ በአሸባሪው ህወሓት በኩል ግን ተጨባጭ ሁኔታዎች አይታዩም። ቡድኑ እስከ አሁንም ለሰላም ንግግሩ የሰየመውን አካል ይፋ አላደረገም፤ ለሰላም ዝግጁነቱን ከማረጋገጥ ይልቅ ቅደመ ሁኔታዎችን በመደርደር ላይ ተጠምዷል። እነዚህ ቅደመ ሁኔታዎች የሰላማዊ አማራጩ ደንቃራዎች እንጂ በየትኛውም መልኩ አስቻይ ሁኔታዎች ሊሆኑ አይችሉም።

ቡድኑ አንዴ የአፍሪካ ህብረት ውይይቱን መምራት የለበትም ይላል ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ የአፍሪካ ህብረት የሰየማቸው የናይጄሪያው የቀድሞ ፕሬዚዳንት ኦሊሴጉን ኦባሳንጆ ውይይቱን መምራት የለባቸውም አልኩ እንጂ አፍሪካ ህብረትን አልፈልግም አላልኩም ይላል ። ይህ የተምታታ የቡድኑ አካሄድ ቡድኑ ለሰላም ንግግሩ ቁርጠኛ አቋም አለመያዙን ያመላከተ ነው ።

በአሁኑ ወቅትም ለሰላም ዝግጁ ከመሆን ይልቅ ለጦርነት ዝግጁ መሆኑን የሚጠቁሙ መረጃዎች እየተሰሙ ናቸው። የአፍሪካ ህብረት ንግግሩን ለማስጀመር እየተዘጋጀ፣ የኢትዮጵያ መንግስትም ይህን እየተጠባበቀ ባለበት በእዚህ ወሳኝ ወቅት፣ አሸባሪው ህወሓት ለሰላማዊ ንግግር ተዘጋጅቶ መቅረብ ሲገባው ሰላማዊ ንግግር የማስጀመሩን ሂደት በሚጎዱ የጦርነት አዝማሚያዎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየተንቀሳሰ ነው ።

የሰላም ንግግሩን በተለይም በቡድኑ እገታ ውስጥ የሚገኘው የትግራይ ህዝብ ከሁሉም በላይ በጉጉትና በተስፋ ይጠብቀዋል። ሰላም ወዳዱ የኢትዮጵያ ህዝብና አለም አቀፉ ህብረተሰብም ለንግግሩ መጀመር የሰጡት ትኩረት ከፍተኛ ነው ። ይህን መሰሉን ሀገራዊ፣አህጉራዊና አለም አቀፋዊ አጀንዳ ማቆርፍድ ፣ አልፎም ተርፎም ለማምከን መሞከር ተገቢነት የለውም።

ይህን አዝማሚያ ስለሰላም እሰራለሁ የሚሉ አለም አቀፋዊና አህጉራዊ አካላት፣ ሀገሮችና ቡድኖች በሙሉ ጉዳዩን በአጽንኦት መከታተል ብቻም ሳይሆን ለሰላም ድርድሩ እግሩን እየጎተተ ባለው አሸባሪው ህወሓት ላይ ጫና በማሳደር የሰላም ንግግሩ እንዲጀምር በትኩረት መስራት ይጠበቅባቸዋል።

ለሰላም የመቆም ተጨባጭ ማሳያው ወቅት አሁን ነው። ተቀራርባችሁ ተነጋገሩ ብሎ እየተመላለሱ ማስገነዘብ አንድ ነገር ነው፤ ብቻውን ግን በቂ አይደለም። ደንቃራዎችን ማስወገድ ፣ አፈንጋንጩን ወደ ንግግር ማስገባት ሲወጣም መመለስ ያስፈልጋል። ይህን ሰላማዊ ንግግር በመጀመር በኩል አሁን ደንቃራዎችን የፈጠረ ቡድን ታይቷል። እዚህ ላይ በትኩረት ሰርቶ ንግግር እንዲጀመር ማድረግ ከሁሉም ወገን ይጠበቃል።

በእዚህ ላይ አለመስራት በውይይቱ ላለመሳተፍ እያንገራገረ እንዲሁም ሶስተኛውን ጦርነት ለመጀመር እያቆበቆበ ለሚገኘው አሸባሪው ህወሓት መሳሪያ የማቀበል ያህል ይሆናል። ይህ እንዲሆን እድል መስጠት የኢትዮጵያ መንግስትንም የአፍሪካ ህብረትንም የሰላም ቁርጠኝነት ዋጋ ማሳጣትም ነው። ከዚህም አለፍ ሲል ደግሞ ተጨማሪ ሰብአዊ ቀውስና ቁሳዊ ውድመት እንዲመጣ መፍቀድም ይሆናል።

ያለጦርነት መኖር ከማይችል ቡድን ጋር ሰላማዊ ንግግር ለማካሄድ የሚደረግ ጥረት አሁንም ብዙ ስራን ይፈልጋል። ይህንን በተጨባጭ ተገንዝቦ ስራዎችን አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል ። የመንግስት የሰላም አማራጭ አብይ ኮሚቴ አለም አቀፉ ህብረተሰብ ከአፍሪካ ህብረት ጎን እንዲቆም ላቀረበለት ጥያቄ አፋጣኝ መልስ መስጠት ይጠበቅበታል።

በተለይ ለትግራይ ህዝብ ሰብአዊ ድጋፍ እያቀረቡ ያሉ እንዲሁም ለሰብአዊ መብት እንቆረቆራለን የሚሉ አካላት በሙሉ በትግራይ ያለው ችግር በእርግጥ እንዲወገድ የሚፈልጉ ከሆነ ከተወያዮቹ ባልተናነሰ መልኩ ለዚህ የሰላም ውይይት መጀመር ወሳኝ ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል።

እነዚህ አካላት ቀደም ሲል ሲያደርጉት እንደነበረው የቡድኑን አጀንዳ ከማቀንቀን ወጥተው ፣ ችግሩ በትክክል እንዲፈታና ተልእኳቸውም ውጤታማ እንዲሆን ቡድኑ በጀመረው መንገድ ጊዜ ሳያባክንንና ቅደመ ሁኔታዎች ሳይደረድር በሰላማዊ በንግግሩ እንዲሳተፍ ጫና መፍጠር ይኖርባቸዋል። ለዘላቂ ሰላም የሚያስፈልገውም፤ ሊከፈል የሚገባውም ዋጋ ይሄው ነው።

ኢፕድ

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

# ሶስቱ የጥፋት ሀይሎች ጥምረት

አሲ ሴሮ

ምሁራን እንደሚናገሩት የኢትዮጵያ ፈተናዎች ከሶስት ነገሮች ይመነጫሉ። አንደኛው ሀገሪቱ የምትገኝበት መልከአማድራዊ አቀማመጥ ስትራቴጂያዊ መሆኑ፤ በቀይባህር አቅራቢያ መገኘቷ በአካባቢው የሃይል የበላይነትን ለማመረጋገጥ በሚሹ አካላት ሁልጊዜም በትኩረት ውስጥ እንድትኖር የማድረጉ እውነታ። ሁለተኛው በዚህ ዘመን ተግዳሮቱ በግልጽ መታየት የጀመረው በአባይ ወንዝ ላይ ኢፍትሃዊ የውሃ አጠቃቀም ለዘላለም ጸንቶ እንዲቆይ የሚፈልጉ ሀገራት የሚያደርሱት ጫና ሲሆን ሶስተኛው ደግሞ በተፈጥሮ ሃብት መታደሏ ነው።

እነዚህ ሶስት የፈተና ምንጮች ሀገሪቱ ዘወትር በቀውስ አጀንዳ ውስጥ እንድትኖር አድርገዋታል።ለመልማት የምታደርገውም ጥረት በሌሎች ኃይሎች እንደስጋት እየታየ ከለውጥ መንገድ ለማደናቀፍ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል። አሁንም በተመሳሳይ መልኩ እየተደረገ ነው።

ኢትዮጵያውያንን በጀግንነት ታግለው ማሸነፍ እንደማይችሉ ስለሚያውቁ እነዚህ የውጭ ኃይሎች የውስጥ ባንዳዎችን በገንዘብ ገዝተው ሀገሪቱም የማመስ የቆየ ታሪክም አላቸው። ከውስጥ ባንዳዎች ጋር ተቆራኝተው ኢትዮጵያን የደም ምድር ለማድረግ ዘወትር ሲሰሩ ይታያሉ። ከድሮ እስከ ዘንድሮ የታየውም ይህ እውነታ ነው።

በአለንበት ወቅት ለሀገሪቱ በጎ የማይመኙ፤ ኢትዮጵያ ከፍታ ስጋት የሚሆንባቸው እነዚህ ሀይሎች የህዳሴውን ግድብ ግንባታን ለማስተጓጎል ሶስት የሽብር ኃይላትን ምርጫቸው አድርገዋል።ህውሓት፤ ሸኔንና አልሻባብን።እነዚህ ሶስት ኃይላት ምንም የሚያስተሳስራቸውና አንድ የሚያደርጋቸው ነገር የለም። ሆኖም አንድ የጋራ አላማ ግን አላቸው፤ ለውጭ ጠላቶች ተላላኪ በመሆን ኢትዮጵያን ማፍረስ።

ይህንኑ አላማቸውንም ለማሳካት በሰሜን፤ በምስራቅና በምዕራብ ሀገሪቱ ክፍል ጦርነት በማወጅ እና ሀገሪቱን የግጭት ማዕከል በማድረግ ኢትዮጵያን ለማፍረስ እየተንቀሳቀሱ ነው። በቀደሙት ጊዜያት በየቦታው በርካታ ንጹሃን ዜጎችን ገድለዋል፤ አፈናቅለዋል፤ለስደት ዳርገዋል።

አሸባሪው ህወሓት ኢትዮጵያን ለ27 አመታት ባስተዳደረባቸው አመታት ጸረ ኢትዮጵያዊ አቋም በመያዝ ጭምር ሀገሪቱ እንድትፈርስ ብዙ ሰርቷል። ዜጎችን በብሄር፤ በሀይማኖትና በቡድን በመከፋፈል እርስ በእርስ እንዳይተማመኑና ወደ እርስ በእርስ ግጭት እንዲያመሩ ያለ መታከት ሰርቷል። የሀገሪቱን አንጡራ ሃብት ያለ ርህራሄ በመዝረፍ በውጭ ባንኮች አከማችቷል።በዘረፈው ገንዘብም የሽብር ድርጊቶችን ለማስፋፋት በስፋት ተንቀሳቅሷል።

ይህ የሽብር ቡድን የዘረፈው ገንዘብ አልበቃ ብሎት ለውጭ ጠላቶች ያለውን ታማኝነት በግልጽ አንጸባርቋል። ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ጋር የምትወዛገብባቸውንና በግልጽ የተወረሱ መሬቶቿን ያለ ህፍረት የኢትዮጵያ ግዛቶች እንዳልሆኑ በመመስከር ከሃዲነቱን አረጋግጧል። ለሀገሩ ሉአላዊነትና ዳር ድንበር ሲዋደቅ ከቆየው ከትግራይ ህዝብ ስነ ልቦና ውጭ ባንዳነቱን በገሃድ አሳይቷል። ከውጭ ጠላቶች የሚሰጠውንም ተልዕኮ ለመሳካት ከአሸባሪዎቹ ሸኔና አልሻባብ ጋር በማበር በተለያዩ አካባቢዎች በሽብር ተግባር ውስጥ ተሳትፏል።

ይህ እኩይ የሽብር ቡድን ኢትዮጵያ በጦርነት ደቃለች፣ በፖለቲካ፣ በጎሳና በሃይማኖት ተከፋፍላ ለመፈራረስ አንድ ሐሙስ የቀራት አገር ሆናለች ብሎ በዓለም መገናኛ ብዙኃን ሚርት በማስነገር ጭምር የሀገሪቱ ገጽታ በብዙ እንዲበላሽ አበክሮ ሰርቷል።የህዳሴው ግድብ እንዲኮላሽም ስልጣን ላይ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ያላሳለሰ ጥረት አድርጓል። ለግድቡ የተዋጣውን ገንዘብ ለግል ጥቅሙ ከማዋል ጀምሮ በአደባባይ ከውጭ ጠላቶች ጋር ተመሳሳይ አቋም በማራመድ በህዳሴ ግድብ ላይ ጸረ ኢትዮጵያዊ አቋም ይዟል።

ቡድኑ በእብሪትና በማናለብኝነት በከፈተው ጦርነት ሽንፈትንና ውርደትን ተከናንቦ ዛሬ አንድ ጥግ ይዞ ቢገኝም በአገኘው አጋጣሚም ሁሉ የሽብር ድርጊቶችን ከማቀድና ከመተግበር፤ ሀገርና ህዝብን ወደ ከፋ ችግር የመክተት ምኞቱን እውን ከልማድረግ ተኝቶ የሚያድር አይደለም። በአሁኑ ወቅትም መንግስት የሰጠውን የሰላም እድል ከመጠቀም ይልቅ ቅድመ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ የትግራይን ወጣት ለዳግም እልቂት እያዘጋጀ ነው።

በኦሮሚያ ክልል በወለጋ አካባቢ ባለፉት አራት ዓመታት የደረሱ ግድያዎች በርካታ ናቸው። በርካታ ዜጎች የዘር ተኮር ግድያና መፈናቀል ተፈጽሞባቸዋል። ከ2013 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 2014 ዓ.ም. መባቻ ጀ በወለጋ አካባቢ በርካታ ግፎች ተፈጽመዋል።

በ2013 ዓ.ም. ጥቅምት ወር በምዕራብ ወለጋ ዞን ጉሊሶ ወረዳ ላይ፤ በመጋቢት 2013 ዓ.ም. ምዕራብ ወለጋ ባቦ ጋምቤል ወረዳ፤ በተገባደደው 2014 ዓ.ም በጥር 2014 ዓ.ም. ቄለም ወለጋ ጊዳሚ ወረዳ ፤ በቅርቡም በሰኔ ወር በምዕራብ ወለጋ ጊምቢ ወረዳ እና በቄለም ወለጋ ሀዋ ገላን ወረዳ ንጹሀን ዜጎች በአሸባሪው ሸኔ በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድለዋል።

አሸባሪው ሸኔ ምን አይነት አላማ የሌለውና የኢትዮጵያ ጠላቶች በሆኑ የውጭ ሃይላት ሳንባ የሚተነፍስ ዕኩይ ቡድን ነው። ዋነኛ ዓላማውም ከአሸባሪዎቹ ህውሓትና አልሻባብ ጋር ሆኖ ኢትዮጵያን ማፍረስ ነው። አሸባሪዎቹ ህውሓትና ሸኔም ኢትዮጵያን ለማፍረስ ድንበር ተሻግረው አለም አቀፍ አሸባሪ ከሆነው አልሻባብ ጋር ወዳጅነት መስርተዋል።ይህንኑ ተማምነውም የአልሻባብ ቡድን ኢትዮጵያ ላይ በቅርቡ የሽብር ጥቃት ለመሰንዘር ሞክሯል።

ከትላልቅ ከተሞች ውጪ በርካታ የሶማሊያ አካባቢዎችን ተቆጣጥሮ የሚገኘው ይህ ታጣቂ ቡድን፣ በሶማሊያ ውስጥ ያልተቋረጠ ከባድ የቦምብ እና የሽምቅ ጥቃቶችን በመፈጸም ለበርካቶች ሞት ምክንያት ሆኗል።ለአገሪቱ ሕዝብና መንግሥት ከባድ የደኅንነት ፈተና እንደሆነም አለ።

ከአልቃኢዳ ጋር ግንኙነት እንዳለው የሚነገርለት አልሻባብ ከህውሓትና ከሸኔ ጋር የፈጠረውን የሶትዮሽ ጥምረት ተገን አድርጎ በኢትዮጵያ ላይ ጥቃት ለመሰንዘር ሞክሯል። ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል እንደሚባለው አሸባሪዎቹ ህውሓትና ሸኔ የኢትዮጵያን ህዝብ ለባዕዳን አሸባሪ ሃይላት አሳልፈው በመስጠታቸውም የአልሸባብ ኃይሎች በሶማሌ ክልል አቶ በተባለው ቦታ ላይ ጥቃት ካደረሱ በኋላ ሁለተኛው ጥቃት የፈጸመው በዬድ ላይ ነበረ። ሆኖም ጀግናዎቹ የምስራቆቹ አንበሶች አሳፍረው መልሰዋቸዋል። ለወሬ ነጋሪም ሳይተርፉም በመጡበት ቀርተዋል።

ቡድኑ በሶማሌ ልዩ ኃይልና በመከላከያ ሰራዊት ድባቅ ባይመታ ኖሮ የሶማሌ ክልልን በማለፍ ባባሌና በአርሲ አካባዎች በህቡዕ ከሚንቀሳቀሰው ሸኔ ጋር የመገናኘት አላማ ነበረው። ሆኖም ድንበሩን በፍጹም ለባዕዳን አሳልፎ የማይሰጠው የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊትና የሶማሌ ልዩ ኃይል ከ800 በላይ የአልሸባብ አባላትን ከመግደል ጀምሮ በአሜሪካ ጭምር በጥብቅ የሚፈለጉትን የቡድኑን መሪዎች በመግደል ጀግንነታቸውን አስመስክረዋል።

ኢትዮጵያን የማመሱ ሶስትዮሽ ሰንሰለት በጀግኖቹ ኢትዮጵያን ተጋድሎ ተበጣጥሷል፤ የአሸባሪዎቹም ምኞት እንደጉም በኖ ጠፍቷል። ሶስተኛው የውሃ ሙሌት ተከናውኗል፤ ሁለተኛውም ተርባይን ብርሃን መስጠት ጀምሯል።




# በጦርነቱ ጉዳት ከደረሰባቸው 536 የጤና ተቋማት 463ቱ አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- በአሸባሪው የሕወሓት ወረራ በአፋርና አማራ ክልሎች ጉዳት ከደረሰባቸው 536 ጤና ተቋማት ውስጥ 463 የሚሆኑት አገልግሎት መስጠት መጀመራቸውን ጤና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ ከዚህ ውስጥ 319 ጤና ተቋማት በከፊል አገልግሎት የጀመሩና ወደ ተሟላ አገልግሎት ለመመለስ ተጨማሪ ሥራ የሚጠይቁ መሆናቸውንም ጠቁሟል፡፡

የጤና ሚኒስትሯ ዶክተር ሊያ ታደሰ እንደገለጹት፤ በአሸባሪው የሕወሓት ወረራ በአፋርና አማራ ክልሎች ጉዳት ከደረሰባቸው 536 ጤና ተቋማት ውስጥ 463 የሚሆኑት አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል፡፡ ከዚህ ውስጥ 319 ጤና ተቋማት በከፊል አገልግሎት የጀመሩና ወደ ተሟላ አገልግሎት ለመመለስ ተጨማሪ ሥራ የሚጠይቁ መሆናቸውንም አስታውቀዋል፡፡

በሰሜኑ የአገራችን ክፍል በተከሰተው ጦርነት ጉዳት ከደረሰባቸው ተቋማት ውስጥ የጤና ተቋማት ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ ያሉት ሚኒስትሯ፤ ለዚህ ምላሽ ለመስጠት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተለያዩ የድንገተኛ ምላሽ ሥራዎችን ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር ሲሠራ ቆይቷል፡፡ ይህን ለማስተግበር እቅድ ተዘጋጅቶ እንደ ሴክተርና ከሌሎችም ሴክተሮች ጋር በገንዘብ ሚኒስቴር በሚመራ የተጀመሩ የመልሶ ግንባታ ሥራዎች ሲሠሩ መቆየታቸውን ጠቁመዋል፡፡

በአማራ ክልል ከተጎዱት 40 ሆስፒታሎችና 453 ጤና ጣቢያዎች 10 ሆስፒታሎችና 134 ጤና ጣቢያዎች ወደ ሙሉ አገልግሎት መመለሳቸውን ጠቅሰው፤ 25 ሆስፒታሎችና 273 ጤና ጣቢያዎች ደግሞ ከፊል አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም በክልሉ በርካታ ጤና ኬላዎች በመልሶ ግንባታ ወደ ሥራ መግባታቸውን አስታውሰው፤ አምስት ሆስፒታሎች እና 46 ጤና ጣቢያዎች አሁንም ድረስ አገልግሎት መስጠት እንዳልቻሉ አክለው ገልጸዋል፡፡

በአፋር ክልል ጉዳት ከደረሰባቸው ሁለት ሆስፒታሎችና 41 ጤና ጣቢያዎችም አንድ ሆስፒታልና 20 ጤና ጣቢያዎች ታድሰው በከፊል አገልግሎት መጀመራቸውን አመልክተው፤ አንድ ሆስፒታልና 21 ጤና ጣቢያዎች እስካሁን ወደ ሥራ መመለስ አልተቻለም፡፡ በሁለቱም ክልሎች ወደ ሥራ ያልገቡ ቀሪዎችን ተቋማት ወደ ሥራ ለመመለስ የጸጥታ ችግር እንቅፋት መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

ከክልል ጤና ቢሮዎች፣ ከፌዴራል ሆስፒታሎች፣ ኤምባሲዎች፣ ከልማት አጋር ድርጅቶች፣ ዳያስፖራዎችና የኢትዮጵያ ወዳጆች በመተባበር በተሠራው ሥራ መሠረታዊና ሕይወት አድን የሆኑ ጤና አገልግሎቶች በግጭቱ በተጎዱ ጤና ተቋማት ውስጥ ማስጀመር ተችሏል ያሉት ዶክተር ሊያ፤ እስካሁን ድረስ ከባለድርሻ አካላት በግብአት፣ በመሳሪያ በገንዘብ 600 ሚሊዮን ብር የሚገመት ሀብት ተሰብስቧል ብለዋል፡፡

እስካሁን ድረስ በግለሰብና ተቋም ደረጃ እገዛ ላደረጉ ባለድርሻ አካላት ምስጋና አቅርበው፤ በርካታ ጤና ተቋማት ወደ ሥራ መመለሳቸው አበረታች ቢሆንም ሁሉም ተቋማት የተሟላ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ከፍተኛ ሥራ ስለሚጠይቅ አሁንም ሁሉም ባለድርሻ አካላት ርብርብ እንዲያደርጉ ጠይቀዋል፡፡

# የዋጋ ንረትን በዘላቂነት ለመቆጣጠር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ጫና ጋር ተደምሮ ግሽበት እንዲፈጠር ምክንያት ሊፈጥር እንደሚችልም ነው የጠቀሱት።

የምግብ ዘይት ከውጭ አገር ይገባል፤ በአገር ውስጥም ይመረታል። ሲሚንቶ አንዳንዴ ምርቱ እያለ ይደበቃል፣ ስኳር በህገ ወጥ መንገድ ወደ ጎረቤት አገር ይሻገራል፤ በአቋራጭ ለመበልጸግ የሚፈልጉ አካላት የሚፈጥሩት ሰው ሰራሽ አካሄድን ማስቆም እንደሚያስፈልግም ተናግረዋል።

አንዳንድ ደላሎችና ነጋዴዎችም በገበያው ሰንሰለት የሚፈጥሩት ጣልቃ ገብነት ገበያውን እንዳይጎዳ ጥብቅ ክትትል መደረግና ምርት በመደበቅና መሰል ሕገ ወጥ ተግባር ላይ የተሰማሩ ነጋዴዎች ላይ አስተማሪ ርምጃ መውሰድ እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል።

በገበያ ሰንሰለቱ፤ መርዘም ዋጋ መናርን ስለሚፈጥር አላግባብ ጣልቃ ገቦችን ከግብይት ሰንሰለቱ በማስወጣት ሕዝብ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ስርዓት መዘርጋት እንደሚያስፈልግም ነው የጠቆሙት።

በአትክልትና ፍራፍሬ፣ በስጋ እና በጤፍ ምርት ላይ የተሰማሩ አርሶ አደሮችን በመደጎም ምርት እንዲያድግ በማድረግ ገበያውን ማረጋጋት ያስፈልጋል ብለዋል።

ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ ለቴክኖሎጂ ልዩ ትኩረት መስጠት እና የአመራረት ስርዓቱን ማዘመን እንደሚያስፈልግ፣ የማዳበሪያ ግብዓት ጉዳይና ስርጭት ሁኔታ ላይ ያለውን ችግር መፍታት እንደሚገባም ነው ዶክተር ዱጋሳ የተናገሩት።

ዩኒቨርሲቲዎችም ለአርሶ አደሩ ጥቅም አዳዲስ ቴክኖሎጂን ማፍለቅ አለባቸው። መንግስትም ተገቢውን ባለሙያ በተገቢው ቦታ ላይ ማስቀመጥና አንጻራዊ ሰላም ማስፈን እንደሚገባውም አመልክተዋል።

ሕዝቡ የአስተሳሰብ ለውጥ በማምጣት ወደ ልማት እንዲሰማራ፣ ውስን ሃብትን ባግባቡ መጠቀም እንዲለምድ፣ የጊዜን ዋጋ እንዲገነዘብ፣ ቁጠባን ባህል እንዲያደርግ ማድረግ እንደሚያስፈልግም አመልክተዋል።

በሌላ በኩልም ለፖለቲካ ፍጆታ ሕዝብንና መንግስትን በማቃቃር ከሂደቱ ለመጠቀም ለሚፈልጉ አካላት እድል መንፈግ፣ ሙስናንም ለዋጋ መናር ምክንያት እንዳይሆን መከላከል እንደሚገባም ጠቁመዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ከድህነት ለመላቀቅ፤ ከጠባቂነት አስተሳሰብ መራቅ፣ ከስሜታዊነት ይልቅ በስሌት መንቀሳቀስ፣ ከሐሜትና አሉባልታ ወጥቶ ምክንያታዊ መሆንና ምርትና ምርታማነትን ማሳደግና ወጣቱን ወደ ስራ ማስገባት ይገባል። ቅንነት፣ ግብረገብነት፣ ደግነትና መተባበር ያስፈልጋል። ከጦርነት ትርፍ ባለመኖሩ በውይይት መፍታት ያስፈልጋል።

# ‹‹መንግሥት ለሰላም እጁን ቢዘረጋም አሸባሪው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ዶክተር ለገሰ፤ ሰብዓዊነትን፣ ሠላምንና የሰው ልጅ መሠረታዊ ጤናን በገለልተኝነት ማረጋገጥ መርህን ያደረገው የአለም ጤና ድርጅት መሪ የሆኑት ዶክተር ቴድሮስ አድሃኖም ሠላምን አሻፈረኝ በማለት የተቋሙን ገለልተኝነት ጥያቄ ውስጥ በሚያስገባ መልኩ የሀሰት ትርክትና ወሬ በመደርደር አለም አቀፉን ማህበረሰብ ለማደናገር እየሰሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

መንግሥት ለሠላም እጁን የዘረጋ ቢሆንም ልዩ ልዩ ቅድመ ሁኔታዎችን በመደርደር እስካሁን ድረስ ተደራዳሪዎችን ያልሰየመው አሸባሪው ሕወሓት ለሠላም ዝግጁ አለመሆኑን እያረጋገጠ ነው ያሉት ዶክተር ለገሰ፤ ይህም የትግራይን ሕዝብ ለከፋ ሰቆቃ በመዳረግ በግጭት ውስጥ የመኖር ፍላጎቱን ለማስቀጠል ያለውን ፍላጎት ያሳየ ነው ብለዋል፡፡

መንግስት ለሠላም የዘረጋውን እጅ መቼም ቢሆን እንደማያጥፍ አመልክተው፤ አሸባሪው ቡድን ለሌላ ጦርነት ነጋሪት በመጎሰም ለሰላም ዝግጁ አለመሆኑን እያረጋገጠ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

እንደ ዶክተር ለገሰ ገለጻ፤ ለሕዝቡ የደህንነት ስጋት የነበሩ የጸጥታና ደህንነት ስጋቶች በተሟላ ብቃት በቁጥጥር ስር እየዋሉ ነው፡፡ በየአካባቢው ሕዝቡን መግቢያና መውጫ ያሳጡ የሸበር ቡድኖችና ኢ- መደበኛ አደረጃጀቶች በተደረገው የተቀናጀ የህግ ማስከበር እንቅስቃሴ አበረታች ውጤት የተገኘ መሆኑን የብሔራዊ ፀጥታና የደህንነት ምክር ቤት በግምገማ አረጋግጧል፡፡

አሸባሪዎቹ አልሸባብ፣ ሸኔና ሕወሓት ከውጭና ከውስጥ ጠላቶቻችን ጋር በመቀናጀት ኢትዮጵያን ለማፍረስ ያሰቡት ትልም በመላው የጸጥታ አካላት የተቀናጀ ስራ ቅስማቸው እንዲሰበር መደረጉን አውስተው፤ በአሸባሪው ሸኔ ላይ እየተወሰደ ባለው እርምጃ የሽብር ቡድኑ አባላትና አመራሮች በቁጥጥር ስር ሲውሉ፣ በርካቶች መደምሰሳቸውን ዶክተር ለገሰ ተናግረዋል፡፡

ህገ ወጥ የገንዘብና የጦር መሳሪያ ዝውውርን ለመቆጣጠር በተደረገው ጥረትም በዚህ ሳምንት ብቻ 12 ሚሊዮን ብር የሚገመት የገንዘብ እና የኮንትሮባንድ ዕቃዎች በቁጥጥር ስር ውለዋል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ድርጊቱ በሽብር ቡድኖች መሪነት በቅንጅት ከውስጥና ከውጭ በመናበብ ኢትዮጵያን በሁሉም መስክ ለማዳከም የሚሰራ መሆኑን መላው ህዝብ ሊረዳ ይገባል ብለዋል፡፡

የአሸባሪው ሕወሓት፣ የሸኔ እና የአልሸባብ ጥምረት፣ ሕገወጥ ገንዘብና መሳሪያ አዘዋዋሪዎች ታግዘው ከጠላቶቻችን ጋር ተቀናጅተው በመላው አገሪቱ ስርዓት አልበኝነት እንዲነግስ፣ ያለመረጋጋት እንዲፈጠር በሁሉም አቅጣጫ የወጠኑት ሕልምም ከሽፏል ብለዋል፡፡

በደቡብ ክልል የሚነሱ የአደረጃጀትና የክልልነት ጥያቄዎች በህገ መንግሥቱ የተቀመጡ መርሆዎችን በመከተል ምላሾችን በሰከነ መንገድ መጠበቅ እንደሚገባ የገለፁት ሚኒስትሩ፤ የግጭት ነጋዴዎችና የጥቂት ፖለቲከኞች የጥቅም ማስፈፀሚያ ላለመሆን መጠንቀቅ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡ የመደራጀት ጥያቄዎች የሕዝብን ፍላጎትና ጥቅም ባስከበረ መልኩ በህጋዊ መንገድ ቀርበው ምላሽ ማግኘት እንደሚችሉም ጠቁመዋል፡፡

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የህዳሴ ግድብ ሶስተኛ ዙር የውሃ ሙሌትና የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር በስኬት የተጠናቀቁበት ነው ያሉት ዶክተር ለገሰ ቱሉ፤ መንግስት 336 ነጥብ 7 ቢሊየን ብር ገቢ በመሰብሰብም ስኬታማ አፈጻጸም መመዝገቡንም ጠቅሰዋል።

እነዚህ ስኬቶች ኢትዮጵያ በፈተና ውስጥ እያለፈች የማትሰበር፣ ዜጎቿም ችግር የማይገታቸውና ታሪካዊ አሻራ የሚያሳርፉ መሆኑን ያሳየ ነው ሲሉ ዶክተር ለገሰ ተናግረዋል፡፡

# በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ የሚያጋጥሙ የሀሰት ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የሀሰት መረጃዎች ለመለየት የሚረዳና ለትክክለኛው ሙያ ትክክለኛውን ሰው ለመመደብ የሚያስችል ስርዓት በመሆኑ እንደአገር ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ወይዘሮ ሙፈሪያት ተናግረዋል።

የቴክኖሎጂ ስርዓቱ የቴክኒክና ሙያ ተመራቂዎችን የዕውቅና ሰርተፍኬት ከሰው ንክኪ ነጻ በሆነና ከሙስናና ስርቆት በፀዳ መልኩ ለማቅረብ የሚያግዝ በመሆኑ በዘርፉ የሚስተዋሉ የሃሰተኛ ማስረጃ ችግሮችን በቀላሉ ለመለየት ያግዛል ብለዋል።

የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ኢንጅነር ወርቁ ጋቸና በበኩላቸው፤ የተቀናጀ የሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ሠርቲፊኬት ሲስተሙን በስድስት ወራት ውስጥ አጠናቆ ለማስረከብ ጥረት እንደሚደረግ ገልጸዋል።

ኢንስቲትዩቱ ባለው የሰው ኃይልና የፋይናንስ አቅም የሚያለማው የቴክኖሎጂ ስርዓቱ በትምህርት ዘርፉ በተለይም በቴክኒክና ሙያ ተቋማት በኩል የሚታየውን የአገልግሎት አሰጣጥ በማዘመን ውጤታማነትን ለማሳደግ የሚያግዝ መሆኑን ተናግረዋል።

ቴክኖሎጂው እንደሀገር ያሉ የሥራ ዕድል ፈጠራ ተግባራት በትክክለኛው ማስረጃ ላይ ተመስርተው እንዲከናወኑ የሚያግዝ በመሆኑ፤ በተቀመጠው የስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ አስፈላጊው ጥረት ይደረጋል ብለዋል።

በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ቴክኖሎጂ አማካኝነት የተለያዩ ተቋማት አሰራራቸውን እንዲያዘምኑ የሚደረገው ጥረት መቀጠሉን የገለጹት ኢንጂነር ወርቁ፤ ጥራትና ውጤታማነትን የሚጨምሩ የተለያዩ የምርምር ስራዎችም በኢንስቲትዩቱ አማካኝነት እየተከናወኑ መሆኑን ጠቁመዋል።

የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት የተቀናጀ የሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ሠርቲፊኬት ሲስተሙን በእራሱ የሰው ኃይልና የፋይናንስ አቅም ለማልማት 26 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ብር እንደሚያወጣ አስታውቋል።



# ነፃ ሃሳብ



በቀምላቸው አበበ ይማም (ሞሺ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# “25 ቢሊየን ከአኃዝ ዜና በላይ ታሪክ ቀያሪ ነው !”

በመንግስታቱ ድርጅት የአየር ንብረት ፕሮግራም (ዩኤንኢፒ)ሀገራችን ኢትዮጵያን ለአየር ንብረት ለውጥ ክፉኛ ከተጋለጡ 10 ሀገራት አንዷ መሆኗን ይገልጻል። መልሶ የአየር ንብረት ለውጥን ከማያባብሱ ዜጎች ተርታ ያሰልፋታል። ኢትዮጵያውያን በአማካኝ ወደ ከባቢ አየር የሚለቁት ግሪንሀውስ ጋዝ 1.3 ሜትሪክ ቶን ወይም 1300 ኪግ ነው፣ በአንጻሩ የአሜሪካውያን 20ሺህ ኪግ፤ ኩየታውያን ደግሞ 60ሺህ ኪግ ግሪንሀውስ ጋዝ ወደ ከባቢ አየር ይለቃሉ። የቻይናና የሕንድማ አይነሳ። ይህ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ለከባቢ አየር ሙቀት መጨመር እዚህ ግባ የሚባል ድርሻ የሌላቸው ሀገራት የበለጸጉ ሀገራት ከኢንዱስትሪ አብዮት ጀምሮ ወደ ከባቢ አየር በለቀቁት ከፍተኛ መጠን ያለው ግሪንሀውስ ጋዝ በተፈጠረ የአየር ንብረት ለውጥና የከባቢ አየር ሙቀት የተነሳ ለተደጋጋሚ የዝናብ ዕጥረት ፣ ለድርቅና ርሀብ ተዳርገዋል።

ሀገራችን ከ1966 ዓም ጀምሮ በየአስር አመቱ ይጎበኛት የነበረው ድርቅ ከቅርብ አመታት ወዲህ በየአመቱ የሚከሰት ሆኗል። ዘንድሮ እንኳ በቦረና፣ በሱማሌና በደቡብ ክልል የተከሰተው ድርቅ በእንስሳትና በአርብቶ አደሩ ላይ ያስከተለውን ከፍተኛ ጉዳት አይተናል። በመንግስት ርብርብ ድርቁ በሰዎች ላይ የከፋ ጉዳት ባያስከትልም የህልውናቸው መሠረት የሆኑ እንስሳቱ ላይ ግን የከፋ ጉዳት አድርሷል ። መጠኑ ቢለያይም እንደ 1966ቱ፣ 77ቱና 87 ሰዎች በርሀብ እንደ ቅጠል አልረገፉም። በአናቱ የሕዝብ ቁጥር ዕድገቱን የሚመጥን ምርት ባለመመረቱ፤ በፍላጎትና በአቅርቦት መካከል ያለው ሰፊ ክፍተት ባለመጥበቡ፤ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ህወሓት በከፈተው ጦርነትና እዚህም እዚያም በተከሰቱ ቀውሶች፤ በኮቪድ 19ና ራሽያ ዩክሬንን በመውረሯ በተፈጠረ የዋጋ ግሽበቱና የኑሮ ውድነቱ የተነሳ በከተሞች ሳይቀር ድምጽ አልባ ርሀብ ተከስቷል ። ኑሮው አልቀመስ ብሏል።

ሀገራችን ዛሬ ለምትገኝበት ውስብስብ ችግር በርካታ ምክንያቶችን መደርደር ቢቻልም ዋነኛዎቹ ግን ሁለት ናቸው። እነሱም አበክረን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት አለመገንባታችን፤ የተፈጥሮ ሀብታችንና የሰው ኃይላችንን በአግባቡ አቀናጅተንና አልምተን አለመጠቀማችን ናቸው። ሰፊ ለም መሬት፣ አመቱን ሙሉ የሚፈሱ ወንዞች፣ የከርስ ምድር ውሃ፣ ዝናብና ወደ 123 ሚሊየን ከሚገመተው ሕዝብ 70 በመቶው ወጣት ስለሆነ ከምግብ ዋስትና አልፈን የተትረፈረፈ ምርት አምርተን ኢንድስትሪውን፣ የአገልግሎት ዘርፉንና የውጭ ንግዱን ይዘን መነሳት እየቻልን ዛሬም እርዳታን የምንቀላውጥ መሆናችን አንገት ያስደፋል።

ከለውጡ ወዲህ ግን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታውን ከግብርና ልማቱ ፣ ከአካባቢ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ጋር መሳ ለመሳ በማስኬድ በአጭር ጊዜ ውስጥ ያልተጠበቀ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ ችለናል። በ2025 ዓም ደግሞ የግሪንሀውስ ጋዝ ልቀቷን ወደ ዜሮ ለማውረድ ግብ ተጥሎ እየተሰራ ነው ። ባለፉት አራት አመታት 25 ቢሊየን ችግኞችን የተከለች ሲሆን የኤሌክትሪክ ፍላጎቷንም ከታዳሽ ኃይል ማለትም ከግድብና ከንፋስ እያገኘች ሲሆን በቀጣይም ከእንፋሎት ለማመንጨትም እየሰራች ትገኛለች።

አገራችን በታሪኳ ከፈጸመቻቸው እየፈጸመቻቸው ካሉ ግዙፋን ፕሮጀክቶች ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ጨምሮ አንድ ላይ ቢደመሩ የ” አረንጓዴ አሻራ“ን ያህል ክብደት አልሰጣቸውም። የህዳሴውም ሆነ የሌሎች ታላላቅ ግድቦች ህልውና እንዲሁ 80 በመቶ አገሬው ኑሮ የተመሰረተበት ግብርና እጣ ፈንታ የሚወሰነው ዛሬ በትጋት በምንከውነው የአካባቢ ወይም የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራ ነውና። በቀደሙት ሶስት አመታት ከ18 ቢሊዮን በላይ አገር በቀል ችግኞችን ለዛውም ከሞላ ጎደል ስነ ምህዳርን ታሳቢ ያደረጉ በመላው የአገሪቱ ክፍሎች መትከል ተችሏል። ከተተከሉ ችግኞች መካከል እንደ አቡካዶ፣ ማንጎ፣ አፕል፣ ፓፓየ፣ ሙዝ እንዲሁም ቡና የመሳሰሉት ይገኙበታል። በአራቱም ዙር ከ90 ሚሊየን በላይ ሕዝብ በችግኝ ተከላው ተሳትፏል።

ከፍ ብዬ ለመግለጽ እንደሞከርሁት ችግኝ መትከል የአየር ንብረት ለውጥን፣ የአለም ሙቀት መጨመርን ወይም የአካባቢ ጥበቃ ችግሮቻችን ለመፍታት የማይተካ ሚና አለው። ድህነትን፣ የምግብ ዋስትና ጉድለትን፣ የምርታማነት ተግዳሮትን፣ ድርቅን፣ ርሀብን፣ የዝናብ መቆራረጥንና መቅረት፣ የውሀ እጥረትን፣ የኑሮ ውድነትን፣ በፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገትና በምርት አቅርቦት መካከል ያለውን ክፍተት፣ ስራ አጥነት ፣ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰትን፣ የጸጥታና የደህንነት ችግርን፣ ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገውን ሽግግር በማሳለጥ እና ሁለንተናዊ ብልፅግናን ለማለም መስፈንጠሪያ በመሆን ያገለግላል። ለዚህ ነው ችግኝ ተከላን የችግሮቻችን ሁሉ መፍቻ ማስተር ኪይ ነው የምለው።

በየአመቱ በአገራችን ከ92ሺህ ሔክታር መሬት በላይ ደን ይመነጠራል። ይጨፈጨፋል። በዚህ የተነሳ የደን ሽፋናችን ከ50 አመታት በፊት ከ35 በመቶ ከነበረበት ደረጃ ወደ ሶስት በመቶ አሽቆልቁሎ ነበር። ለዝናብ እጥረት፣ ለድርቅና ለከባቢ አየር ሙቀት ተዳረግን። በየአመቱ ምርታችን ከ10 በመቶ በላይ መቀነስ ጀመረ። በየአመቱ ከ35 እስከ 40 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይቀንሳል። ሆኖም ባለፉት አራት አመታትም ሆነ ከዚያ በፊት በተከናወኑ የችግኝ ተከላና የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች የደን ሽፋኑን ወደ 17 በመቶ ማገገሙ ይበል የሚያሰኝ ነው።

የበጋ ስንዴ፣ የኩታ ገጠም ግብርናን ፣ በተወሰነ ደረጃ ስነ ምህዳርን ታሳቢ ያደረገ የቴክኖሎጂና የሜካናይዜሽን እገዛ፣ የከርሰና የገጸ ውሃን አሟጦ የመጠቀም፣ ፍራፍሬና አትክልት ላይ ለመስራት፣ በተለይ ከአለፈው አመት ጀምሮ የከተማ ግብርና ትኩረት ማግኘቱ፤ በአርብቶ አደሩ የሚገኙ ጦም ያደሩ ሰፋፊ መሬቶችን በመስኖ ለማልማት አበረታች ጥረትና ርብርብ መደረጉ እና ከውጭ የሚገባውን ስንዴ ለማስቀረት ግብ መጣሉ የአተያይ ለውጥ በማምጣቱ ተስፋ ያስቀረጠን ግን ደግሞ ብቸኛ ሊባል በሚችለው ግብርና ከምግብ ዋስትና ባሻገር ተስፋችንን እንድናድስ አድርጎናል። ለዚህ ነው ተስፋ ሰጭ ጅምር እውቅና መስጠት የሚያስፈልገው።

ችግሮቻችንን ሁሉ ፈታተን፣ በታትነንና አገላብጠን ብንመረምራቸው አብዛኛዎቹ ከአንድ ቅርጫት የሚገኙ ናቸው። የተፈጥሮ ሀብታችንን በአግባቡ ካለመንከባከብ፣ ካለመጠበቅና ካለማልማት ቅርጫት። የአለም ሙቀት መጨመርን ተከትሎ በመጣ የአየር ንብረት ለውጥ የተነሳ የተፈጥሮ ሀብታችን እየተጎሳቆለ በመምጣቱ ማለትም መሬታችን የተራቆተ ፣ ዝናባችን የአጠረና የተቆራረጠ በመሆኑ የከርሰና የገጸ ምድር ውሃችን በመመናመኑ ግብርናው ውጤታማ ሊሆን አልቻለም።

በዚህ የተነሳ በግብርና ላይ የተመሰረተው የዜጋው ህይወት፤ የአገሪቱ ልማት ችግር ላይ ወድቋል ። ይህ

> ሀገራችን ከ1966 ዓም ጀምሮ በየአስር አመቱ ይጎበኛት የነበረው ድርቅ ከቅርብ አመታት ወዲህ በየአመቱ የሚከሰት ሆኗል። ዘንድሮ እንኳ በቦረና፣ በሱማሌና በደቡብ ክልል የተከሰተው ድርቅ በእንስሳትና በአርብቶ አደሩ ላይ ያስከተለውን ከፍተኛ ጉዳት አይተናል

የሀብት ውስንነትን ፈጥሯል። በዚህ የተነሳ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ከአመት አመት እየተባባሱ መጡ። እነዚህን ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት ደግሞ የተፈጥሮ ሀብታችን እንዲያገግም ሌት ተቀን መሰራት አለበት። መሬት ማገገም፣ ውሃ መያዝ አለባት። ይህ ደግሞ እውን ሊሆን የሚችለው ችግኝ በመትከልና የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎችን በስፋት በማከናወን ነው።“ አረንጓዴ አሻራ“ የበሽታውን ምልክት ከማከም ይልቅ መነሻውን በማያዳግም ሁኔታ የመፈወስ አቅም እንዳለው በማመን ነው፤” አረንጓዴ አሻራ ! “ የእንቆቅልሾቻችን ሁሉ መፍቻ ቁልፍ (ማስተር ኪይ) የምለው።

ለዚህም ነው 25 ቢሊየን ችግኞችን መትከል ከቁጥርና ከአኃዝ በላይ በየአመቱ የሚከሰተውን ድርቅ፣ የበርሀማነት መስፋፋት፣ የአፈር መከላት፣ የዝናብ ዕጥረትና መቆራረጥ፣ የገጸና የከርሰ ምድር ውሃ መቀነስን በመከላከል፤ የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ባሻገር ከተመጽዋችነት የመላቀቅ የማሪያም መንገዳችን፤ ሉዓላዊነታችን ሙሉኡ ማድረጊያችን፤ የሀገሪቱ ሁለንተናዊ ብልጽግና ማርሽ መቀየሪያ፤ አስተማማኝ ሰላም ማስፈኛችን፤ እውነተኛ አንድነትና እርቅ ማረጋገጫችን፤ ወዘተረፈ ስለሆነ አረንጓዴ አሻራ ከአኃዝ በላይ ከመሆኑ ባሻገር ጠቅላይ ሚንስትሩ እንዳሉትም እንደ ሀገርና ሕዝብ ብቸኛ መዳኛችን ነው። የአራት አመቱ የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብርን መጠናቀቅ አስመልክቶ ጠቅላይ ሚንስትር አብይ ያስተላለፉት መልዕክትም የአረንጓዴ አሻራው 25 ቢሊየን ችግኝ ተተክሏል ከሚለው የአኃዝ ዜና በላይ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው።

ክቡር ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ የአራት ዓመቱ የአረንጓዴ አሻራ ዘመቻ መጠናቀቅን አስመልክተው ባወጡት መግለጫ በአረንጓዴ አሻራ ሥራዎች ከችግኝ ማፍላት እስከ እንክብካቤው 25 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን መሳተፋቸውን፤ በኢትዮጵያ ሲካሄድ የቆየው የአረንጓዴ አሻራ ዘመቻ በአገሪቱ አረንጓዴ ባህልን በመፍጠር ስኬታማ መሆኑን መግለጻቸውን የኢትዮጵያ ፕሬስ ኤጀንሲ ዘገባ ያወሳል። ኢትዮጵያ የከተሞቿን የአረንጓዴ ሽፋን ለማሳደግ የአረንጓዴ አሻራ ዘመቻን መጀመሯን፤ ለአራት ዓመት በቆየው ዘመቻ 20 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ወጥና ብትነሳም፤ ዜጎቿ 25 ቢሊዮን ችግኞችን በመትከል ካስቀመጡት ግብ በላይ ፈጽመዋል። የአረንጓዴ አሻራ ዘመቻው ሲጀመር 40 ሺህ ብቻ የነበሩት የችግኝ ማፍያዎች አሁን ላይ ወደ 121 ሺህ ማደጋቸውንና በዓመት ሰባት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ችግኝ የማፍላት አቅም ላይ መደረሱን ፤ አረንጓዴ ባህልን ከመፍጠር ባለፈ ዘመቻው ለ767 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር ያበረከተውን ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅኦም ማንሳታቸውን የኤጀንሲው ዘገባ ያመለክታል።

ከዚህ ባለፈ ለችግኝ ተከላ የሚያስፈልጉ ቦታዎችን በመምረጡ እና ለተከላ በማዘጋጀቱ ረገድም የታየው ውጤት አበረታች መሆኑን፤ በመላው አገሪቱ የሚገኙ ከተሞች አሁን ላይ የአረንጓዴ ስፍራ አስፈላጊነትን ተረድተው ቦታ እያዘጋጁ መሆኑ ለተፈጠረው አረንጓዴ ባህል ማሳያ ነው። የአረንጓዴ አሻራ ባህል ለቀጣዩ ትውልድም የሚቆይ መሆኑን፤ በዚህ ስኬት ውስጥ የፖለቲካ ፍላጎት እና ቁርጠኝነት ቁልፍ ሚና መጫወቱን፤ በአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብሩ በርካቶች መሳተፋቸውን፤ አሁንም ብዙ ሥራ የሚጠበቅብን ቢሆንም ንቅናቄው በአገሪቱ ፍሬ እንዳፈራ ጠቅላይ ሚንስትሩ አስታውቀዋል።

ያለፉትን ጥቂት ሳምንታት ብቻ በዓለም ዙሪያ የተስተዋሉት የጎርፍ አደጋ፣ የደን ቃጠሎ፣ ኃይለኛ ማዕበል እና ያልተለመደ ሙቀትን የመሰሉ ሁኔታዎች ለዓየር ንብረት ለውጥ ዓይነተኛ ማሳያዎች መሆናቸውን፤ የአፍሪካ ቀንድ ያስተናገደው ድርቅ የዚሁ የአየር ንብረት ለውጥ ውጤት መሆኑን፤ በኢትዮጵያም የዓየር ንብረት ለውጥ የውሃ ምንጮችን ማድረቁን በአንዳንድ የአገሪቱ ክፍሎችም የድርቅ አደጋን ማስከተሉን፤ አሁን ላይ ዓለም እየተሰቃየ ያለበትን ይህን ችግር ለመፍታት ከስብሰባዎች ያለፈ ተግባራዊ መፍትሄ መውሰድ ያስፈልጋል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ማሳሰባቸውን ኤጀንሲው ዘግቧል።

ሀገሪቱ የታዳሽ ኃይል በሆኑት የውሃ፣ ንፋስ፣ ፀሐይ እና የእንፋሎት የኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ላይ የምታውለው መዋዕለ ንዋይ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል በበኩሏ እየተወጣች የምትገኘው ኃላፊነት መሆኑን፤ አሁንም ብዙ ሥራ ቢጠበቅም በአገሪቱ አረንጓዴ ባህልን በመፍጠሩ ረገድ ዘመቻው እንደተሳካ፤ አፍሪካ ብሎም ዓለም ተፅዕኖው እየከፋ የመጣውን የአየር ንብረት ለውጥ ለመከላከል ልክ እንደ ኢትዮጵያ ተግባራዊ የአረንጓዴ አሻራን በመፍትሄነት ሊጠቀሙ እንደሚገባ ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ መልዕክት አስተላልፈዋል።

አረንጓዴ አሻራ የሕዳሴያችን ዋልታና ማገር ነው !

ሀገራችን ኢትዮጵያ በጀግኖች ልጆቿ ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር !

አሜን።

# የሕይወት ገጽታ

# ‹‹ቆሻሻ በመጥረጊያ እንደሚጸዳ ሁሉ የአገርም ችግር በጥበብ ኃይል ይጸዳል››

-አርቲስት እጅጋየሁ ተስፋዬ



ፎቶ በገባቦ ገብሬ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ጥበብ ትክክለኛ እና እውነተኛ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ የምንጠቀምበት ኃይል ነው። በተጨማሪም ለማንኛውም ሁኔታ ትርጉም ያለው መፍትሄ ለመምረጥ የሚያስችል አቅም የሚፈጥርልን ነው። ጥበብ በሕይወታችን ዘመን ሁሉ በሰው ዘንድ አስደሳች የሆነ አስተሳሰብን፣ ንግግርን እና ድርጊትን የሚያቀዳጅ ነው። ከዚያም ሻገር ሲል ጥበብ አሸናፊ የሆነ ሕይወትን ለመምራት የሚያስችል ነው። ምክንቱም በጥበብ ያልተመራ ሕይወት ምንግዜም ውድቀትን እንጂ ስኬትን ሊያመጣ አይችልም። እናም ማስተዋላችን ከጥበብ ጋር የተቆራኘ ከሆነ ውጤታማ እንሆናለን።

ማስተዋል አንድን ነገር የምንገነዘብበት፣ ከባለፈው ስህተቶቻችን በመነሳት የወደፊቱን የምናስተካክልበት መሳሪያ ነው። ያለ ማስተዋል የሚራመድ ሰው በሕይወት ጎዳና ላይ ከሚያጋጥመው ነገሮች በመነሳት በግራ መጋባት ሊሞላ፥ ቶሎ ተስፋ ሊቆርጥ ወይንም በቀላሉ ወጥመድ ውስጥ ሊገባ ይችላል። በመሆኑም ‹‹ጥበብን ባንፈልግ ችግር እና መከራ በቤታችን ላይ እንጋብዛለን። ጥበብን ብንሻት ግን ህይወትን እና ሞገስን ያገኛል ( መጽሐፈ ምሳሌ 8፡35-36›› እንዲል መጻሐፍ ቅዱስ ይህንን ተገን አድርገን መንቀሳቀስ ይኖርብናል። ይህንን ያነሳነው ያለምክንያት አይደለም። ጥበብን ከብልሃቱና ከድርጊቱ ጋር አስተባብረው የዘለቁና የተጠቀሙ አንዲት እንስትን ልናስተወውቃችሁ ስለፈለግን ነው።

እንግዳችን አርቲስት እጅጋየሁ ተስፋዬ ይባላሉ። በሥዕልም ሆነ በሐውልቱ ሥራ አንቱታን ያተረፉ ናቸው። በእጃቸው ፍሬ የሁሉንም ቤት ያንኳኩና ያስተማሩም ናቸው። አገራቸውንም በማስተዋወቁ ረገድ ትልቅ አሻራ ያስቀመጡ እንደሆኑ ታሪካቸው ይመሰክራል። በሥዕሎቻቸውም ሆነ በሐውልት ሥራቸው ህይወትን ሲኩሏት ኖረዋል።

ስዕል የእርሳቸው የልጅነት ስጦታቸው ብቻ አልነበረም። ለአገራቸው የሚያግዙበትና ችግርን እንድታልፍበት ያደረጉበት መፍቻቸው ነው። ተማሪ ሳሉ በ1977 በድርቅ ምክንያት የተጎዱ ወገኖችን ለማገዝ በሚደረግ ዘመቻ ላይ አሳዛኝ ሀውልት በመስራት የእርዳታ መሰብሰቢያ አድርገውት ብዙ ገቢ ያስገኙ እንደነበሩም በወጋችን መካከል አጫውተውናል። ከዚያም በኋላ የተለያዩ መረጃዎችን ለማስተላለፍ፤ ፖለቲካውን ለማሳለጥና ልጆችን ለማስተማርም ተጠቀመውበታል።

## በነጻነት የተገነባው ልጅነት

ተወልደው ያደጉት አዲስ አበባ እቴጌ መነን አካባቢ በተለምዶ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሆስፒታል የሚባል ቦታ ነው። ልጅነታቸው የነጻነት መድረካቸው ስለነበረም ወንዳወንድ ሆነው ነው እድገታቸውን ያጣጣሙት። ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ሳይቀሩ ከወንዶች እኩል ያደርጋሉ። በተለይ ክብደት ማንሳት ላይ ማንም አያህላቸውም። የእግር ኳሱም ላይ እንዲሁ ጥሩ ተጨዋች ነበሩ። በዚህ ባህሪያቸው ብዙዎች ይደነቁ ነበር። ምክንያቱም ለሁሉም ታዣዢና ተላላኪ ናቸው። የተባሉትን በፍጥነት ያደርጋሉም።

እንግዳችን እንደሴቶችም የቤቱ ሥራ ላይ በጣም ጎበዝ ናቸው። በተለይ የመጀመሪያ ልጅ በመሆናቸው የማይሰሩት ሥራ አልነበረም። ሙያ ያላት ግን ደግሞ ጨዋታ የምትወድ ሴት ሆነው ነው ያደጉት። ለዚህ ደግሞ በሁለት ቤት ውስጥ ማደጋቸው ትልቅ አስተዋዕጾ አበርክቷል። ማለትም ከእናትና አባታቸው ቤት ባለፈ አቶ አበበ ከበደና ወይዘሮ ጥሩወርቅ አስፋው በሚባሉ አሳዳጊያቸው ቤትም ልጅነታቸውን አሳልፈዋል። እንደውም ሰፊው የልጅነት ጊዜያቸው ያለፈው የደጅአዝማች አስፋው ቤተሰብን በመቀላቀል ነው።

በወቅቱ ባላባት እየተባሉ በሚጠሩ ሰው ቤት በማደጋቸውም ብዙ ነገራቸው በቅንጦት የተሞላ እንዲሆንላቸው አድርጓል። ነጻነት ተሰምቷቸው የፈለጉትን እያደረጉ እንዲጓዙም ፈቅዶላቸዋል። በተለይም በሚሰሩት ሥራ እርግጠኛ እንዲሆኑ ያደረጋቸው ይህ መሆኑን ይናገራሉ። አልችለውም የሚል ስሜት እንዳይሰማቸውም ሆነው አድገዋል። በዚህም በመሞከር ብቻ ያምናሉ እንጂ መውደቃቸውን አይቆጥሩትም። ሌላው በዚህ ቤት ማደጋቸው የጠቀማቸው ነገር አገር ወዳድ እንዲሆኑና ታሪካቸውን እንዲያውቁ መደረጋቸው ነው። ሁሌም በአገራቸው እምነትና ተስፋ ያላቸውም ሆነውም አድገዋል። ለጋሽና ነጻ መሆንንም የተማሩበት ቤት ነው። አድማጭና ታሪክ አዋቂም አድርጓቸዋል። በተጨማሪ ጠያቂነትን ያዳበሩበት ቤታቸው እንደሆነም አጫውተውናል።

አሳዳጊያቸው እንደእርሳቸው ብዙ ልጆችን በመውሰድ ተንከባክበው ለወግ ማዕረግ አብቅተዋል። ለእርሳቸው ዛሬ ላይ መድረስም የእነርሱ ሚና ምንም መተኪያ የለውም። ይህ ደግሞ አርአያነታቸውን ተከትለው እንዲሰሩ መስመር የጠረገላቸው እንደሆነም ያስረዳሉ። በተለይም ሕጻናት ላይ በቻሉት ሁሉ ለመሥራት ያነሳሳቸው ይህ ምስጢራዊ እድገታቸው መሆኑንም ያነሳሉ።

ልጅነታቸውን ከስፖርቱ ጋር በተያዘ ቴሌቪዥን ላይ እስከመቅረብ ያደረሳቸው ነው። ምክንያቱም በአካባቢያቸው የስፖርት አሰልጣኝ የነበረ አቶ ግርማ ቸሩ የሚባል ሰው ነበረ። እናም እርሱ ጋር እየሄዱ ይሰሩ ነበርና በቀረጻው ላይ በስፋት ይታዩ እንደነበር ያስታውሳሉ። ይህ ደግሞ ከሥዕል ሙያቸው ጋር ተዳምሮ ተዋቂነትን እንዲያተርፍላቸው አድርጓቸዋል። ልዩ ፍላጎታቸውና የልጅነት ሕልማቸው የተጣጣመውም ከዚህ አንስቶ እንደነበር ያወሳሉ። ሕልማቸው እውቅ ሰዓሊ መሆን ሲሆን፤ እንዳደረጉትም ያምናሉ።

## ቢቆራረጥም ስኬታማ የሆነው ትምህርት

የትምህርት ጅማሮዋቸው ህልማቸውን ሳይረሳ የሄደ ነው። በእያንዳንዱ ቅጽበት ከሥራቸው ጋር በማያያዝ ለዛሬ በቅተውበታል። ገና የመጀመሪያ ትምህርታቸውን በእቴጌ መነን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትቤት ሲማሩ ጀምሮ የሥዕል ዝንባሌያቸው እስከ ዩኒቨርስቲ ዘለቃል። መጀመሪያ እስከ ዘጠነኛ ክፍል ተምረው መደበኛውን ትምህርት በማቋረጥ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ወደ ሥዕል ትምህርትቤት አመሩ። በጊዜው ደግሞ 12ኛ ክፍልን ማጠናቀቅን አይጠይቅምና ጊዜ ሳይሰጡ ህልማቸውን እውን ለማድረግ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስር ባለው አለፈለገ የስነጥበብ ትምህርትቤት ገቡ።

በወቅቱ ትምህርቱ የሚሰጠው አምስት ዓመት ቢሆንም ድግሪ የሚል ስያሜ አልነበረውም። ዲፕሎማ እየተባለ ነው የሚሰጣቸው። ስለሆነም ሥዕልና የተለያዩ ትምህርቶችን በሦስት ዓመት ውስጥ አጠናቀው በአንድ መስክ ማለትም በሐውልት ሥራ ሁለት ዓመታትን በመከታተል ነበርም የተመረቁት። ምርቃታቸውም በማዕረግ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ሴት ሐውልተኛ በሚል ነው። ለዚህም በትምህርትቤቱ አሻራቸውን ያኖሩበት ሐውልት ምስክር እንደሆነ ያስረዳሉ።

አርቲስት እጅጋየሁ የጀመሩትን ነገር አለማጠናቀቅ መሸነፍ እንደሆነ ያስባሉ። በዚህም ያቋረጡትን ትምህርት በማታው ክፍለጊዜ በተፈሪ መኮንን ትምህርትቤት መከታተል ችለዋል። ማለትም ከዘጠነኛ ክፍል ያቋረጡትን ትምህርት እስከ 12ኛ ክፍል ተምረው በከፍተኛ ውጤት አጠናቀዋል። ማታ የተማሩበት ምክንያት ቀን ሥራዎችን ስለሚሰሩና የስዕል ትምህርትቤት ስለሚማሩ ነው። እናም ሁለቱን አጣጥመው ተገቢውን እውቀት ጨብጠው ትምህርቱን ማጠናቀቅ ችለዋል።

ቀጣዩ የትምህርት ቆይታቸው የሚወስደን ደግሞ ጣሊያን አገር ሲሆን፤ ብዙ ልምድ የቀሰሙበት ነበር። በተለይም የደረሳቸው ዩኒቨርሲቲ ብዙዎች የሚመኙት አካዳሚ አፍ ፋይን አርት እስኩል አፍ ካራራ የተባለ ዩኒቨርስቲ መሆኑና የሐውልት ትምህርትን ለመማር እንደ ማርብልና እምነበረድን እንዲሁም ነሐስን በቀላሉ ማግኘት የሚችሉበት መሆኑ በሙያቸው የላቁና የሚፈለጉ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። የመጀመሪያ ድግሪያቸውን በተሻለ ውጤት ያጠናቀቁትም ለዚህ ነው። በእርግጥ ከዚህ በፊትም ቢሆን የትምህርት እድል አግኝተው ነበር። ራሺያ ላይ። ሆኖም አገሪቱ ላይ ያለው የሶሻሊዝም የፖለቲካ አመለካከት ሲያዩት ምንም እንኳን በዚያ ሄደውም አርት ስኩል ያስተማሯቸውን መምህራን ዳግም የሚያገኙባት ቦታ ቢሆንም ፖለቲካው ብዙም ምቾት ስላልሰጣቸው ሊመርጡት አልፈለጉም። በዚህም ዓመታትን ያለትምህርት ቆዩ። የጣሊያኑ ውድድር ሲመጣም ተወዳድረው ገቡ።

ባለታሪካችን ወደ እንግሊዝ አገር በማቅናትም ሌላ ትምህርት ተምረዋል። ይህም በኦፕን ዩኒቨርስቲ የተከታተሉት የሳይኮሎጂ ትምህርት ሲሆን፤ በሁለተኛ ድግሪ የተመረቁበት ነው። ይህንን የተማሩበት ምክንያትን ሲያነሱም ከሕጻናት ጋር ያላቸውን ቅርበት ለማጠንከር አስበው እንደነበር ያወሳሉ። ፍላጎታቸው በእውቀት የተገነባ መምህር መሆን ነበርና አሳክተውታል። የማዕረግ ተመራቂም ነበሩ።

## ሥዕልና ገጸ በረከቱ

መምህሮቻቸው ሳይቀሩ ማስተማሪያ ሲቸግራቸው እርሳቸውን መርጠው ያሰሯቸዋል። በዚህም አበርክቷቸው መማሪያ ስዕሎችን ከመስራት ይጀምራል። ገና አርት እስኩል ላይ የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ እያሉ ነበር በቴሌቪዥን ጣቢያው ውስጥ የሚሰራው የስዕል ፀሐፊው በመታመሙ የተነሳ ተክተው በወቅቱ ኮምፒውተር ስላልነበረ ለቴሌቪዥን የሚሆን ጽሁፍ እንዲሰሩ የታዘዙት። በዚህም ለወራት ያህል ደሞዝተኛ ሆነው አሻራቸውን ያሳረፉ ኢትዮጵያዊት ሰዓሊ ሆነዋል።

የሥዕል ሥራ ኤግቢሽንን ማሳየት የጀመሩትም እንዲሁ የሦስተኛ ዓመት ተማሪ ሳሉ ነበር። ይህ ደግሞ የገቢ ምንጫቸው ከማድረጋቸው ባለፈ ብዙዎችን የሚያስተምሩበትና የውጪ ሀገራትን ጭምር የሚስቡበት ማስተማሪያ እንዲሆንላቸው ረድቷቸዋል። እንደውም ከዚህ ኤግዚቢሽን ጋር በተያዘ ተምሮ ማስተማር ስለነበር በምስካዬ ሕዙናን መድህኒአለም አዳራሽ ተሰቷቸው እነሎሬት አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ በተገኙበት አቅርበው በስዕል ስራዎቻቸው ብዙዎችን ማስደመም ችለዋል።

በተከታታይም ሳይመረቁ ለአራት ጊዜ የሥዕል አውደርዕይ ማዘጋጀት የቻሉና የራሳቸውን እድል በራሳቸው ያመቻቹት ወይዘሮ እጅጋየሁ፤ ይህ አጋጣሚ የውጪ ኤግዚቢዥኖች ላይ እንዲሳተፉ ዕድል ፈጥሮላቸዋል። በዚህም ውጪ ሄደው ስለአገራቸው ከመመስከርና ከማሳወቅ ባለፈ ያላቸውን አቅም ያሳዩበትን አጋጣሚ ፈጥሮላቸዋል። እነዚህ ጥረቶቻቸው በሥዕሉ ዘርፍ ወንድ እንኳን የማይደፍረውን የሐውልት ሥራ መርጠው ዛሬ ድረስ የዘለቁ ናቸው። ምክንያቱም ጠንካራ ድንጋይን መፈልፈልን ጭምር ይችሉበታል። መስተዋትን ፣ እምነበረድንና ነሐስንም በሚፈልጉት ቅርጽ እያሳመሩ ማስደመምን የተካኑም ናቸው። ለዚህ ደግሞ ከልጅነታቸው ጀምሮ አዘውትረው ሲሰሩት የነበረው የስፖርት እንቅስቃሴ ትልቅ ድርሻ ነበረው። በቀላሉ የማይፈተኑ አድርጓቸዋልና።

ጣሊያን አገር እንኳን ሳሉ በደማሚት ተራራውን ከናዱ በኋላ በቅርጽ በቅርጽ የሚሰራውን ሐውልት በእጅ ጥበባቸው ከማንም በተሻለ መልኩ የሚከሽኑት በጸና መሰረት ላይ በማደጋቸው ነው። የንሀስ ሥራዎቻቸውም ቢሆኑ ፈታኝነት ያላቸውም ቢሆኑም ወርቅ ናቸው። ምክንያቱም ለአገራቸው አምጥተው ያስረከቡት አንዱ ማሳያ ሆኗል።

እንግዳችን በእጅ ጥበባቸው በአገር ውስጥ ብቻ ሳሆን ባህር ማዶ ተሻግረውም እውቅናን አግኝተዋል። መጀመሪያ በትናንሽ ትምህርትቤቶች በማስተማር ከዚያም በቤታቸው የተለያዩ የሐውልትና የሥዕል ሥራዎችን በመሥራትና በመሸጥ እንዲሁም ኤግዚቢሽኖችን በማዘጋጀት ተዋቂነታቸውን አጎልብተዋል። ይህ ከሆነላቸው በኋላ ደግሞ ትልቅ በሚባሉ ተቋማት የማገልገል ዕድል አግኝተዋል። አንዱ የአውሮፓውያን ኮሚሽን ሰራተኞች የሚማሩበት ትምህርቤት ሲሆን አሁን ድረስ በቦታው ላይ እያስተማሩ ይገኛሉ። በተጨማሪም የማስተማሪያና ለልጆች የሚሆኑ መጻሐፍት ዝግጅቶች ላይ ሥዕል በመሥራት በስፋት ይሳተፋሉ። በእርግጥ

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

ይህ ሥራቸው በአገር ውስጥ የጀመረ ነበር። ይኸውም በስፖርት መምህሩ ግርማ ቸሩ አማካኝነት ሲሆን፤ የስፖርት መጸሐፍትን ሲያዘጋጅ ሥዕሉን የሰሩት እርሳቸው ነበሩ።

እንግዳችን በቤተመንግስት ውስጥ ጭምር እየተወሰዱ ትልልቅ ፖስተሮችን የሰሩ ናቸው። አለማቀፍ የሥዕል አውደርዕዮችንም እንዲሁ አገራቸውን በመወከል በተለያየ ጊዜ ተሳትፈዋል። ወደ ቤልጅየም በማምራት ሙያቸውን መሰረት አድርገው በርካታ ተግባራትን ፈጽመዋል። አንዱ ማስተማር ሲሆን፤ በዚያው አካባቢ ይኖር የነበረ የሥዕል ትምህርትቤት አንድ ክፍል ሰጥቷቸው የሥዕል ፍቅር ያላቸውና በትርፍ ጊዜያቸው መማር የሚፈልጉ ሰዎችን ያስተምሩ ነበር። ሁለት ዓመትም በዚህ ሥራ ላይ ቆይተዋል። ሉክሰን በርግ ላይም እንዲሁ ይህንኑ ሥራቸውን ከውነዋል። ከላይ እንዳልነው የአውሮፓውያን ስኩል ውስጥ የኮሚሽኑ ሰራተኞችና የተለያዩ ድርጅቶች ዳይሬክተር ልጆች የሚማሩበት ሲሆን፤ ከ16 ዓመት በላይ የቆዩበትና አሁንም የሚያስተምሩበት ነው።

እንግዳችን የሥዕል መምህር መሆናቸው በብዙ መልኩ ጠቅሟቸዋል። አንዱ ሁሉም ቦታ ላይ መግባት ስለሚችሉ በእያንዳንዱ ቦታ ላይ ሲሄዱ የቋንቋ ጉዳይ እንዳያሳስባቸው ቋንቋ መማራቸው ነው። አሁን ቢያንስ ከአምስት በላ ቋንቋዎችን ጠንቅቀው ያውቃሉ። ለአብነትም ጣሊያንኛ፣ እንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛና ጀርመንኛ ተጠቃሽ ናቸው።

**አበርክቶ**

አርቲስት እጅጋየሁ ገና ልጅ ሳሉ ነው ለሀገራቸው ማበርከትን የተለማመዱት። ጣሊያን ከመሄዳቸው በፊት «ደስተኛ ልጅ» የሚል ርዕስ ያለው ሐውልት ሰርተው ለብሔራዊ ሙዚዬም አበርክተዋል። በተመሳሳይ በቅርቡ እንዲሁ ከንሐስ የሰሩትን ስምንት ኪሎ ክብደት ያለው የልጅ ምስል ከፍተኛ ወጪ የወጣበት ቢሆንም ለብሔራዊ ሙዚዬም በማስረከብ አገር ወዳድነታቸውን አሳይተዋል።

አርቲስት እጅጋየሁ «የቃኘው ጦር ሰፈር» እየተባለ የሚጠራውን የስብሰባ አዳራሽ በውብ የእጅ ጥበባቸው ያስዋቡም ናቸው። በእርግጥ በወቅቱ በግዴታ ያደረጉት ነበር። የሠሯቸው ሥዕሎችም ፖለቲካው የሚፈልገውን ብቻ ነው። ነገር ግን ምንም አይቆጫቸውም። ምክንያቱም ሰፊው አዳራሽ የእርሳቸውን የእጅ ጥበብ ውጤት ይዞ ወጥቷል፤ ታሪክ አድርጎ አስቀምጦላቸዋል። ሌላው የሠሩት ነገር ወደ ሁለት መቶ የሚሆኑ የሌሊን፤ የማርክስና ሄንግልስ መሰረታዊ ጽንሰ ሀሳቦችን የያዘውን ፖልትሬት ነው። ሦስት ሜትር በሁለት ሜትር ይደርሳልም። ለሁሉም ማህበረሰብ በሚደርስ መልኩ የሠሩት ተግባር ሲሆን፤ ኢትዮጵያን በእነዚህ ሥዕሎች መድረሳቸውም ከአበርክቷቸው አንዱ እንደነበር ያነሳሉ።

ከሁሉም በላይ ዛሬ ድረስ የሚያስደስታቸው ሌላው ሥራቸው ለድርቅ ኮሚሽን ማስተባበሪያ ወይም በዛሬው የእርዳታ ኮሚሽን ማስተባበሪያ ድጋፍ ማሰባሰቢያ የሚሆን ሐውልት ሰርተው ያስረከቡ ነው። ብዙ ሰው አይቶ የሚያዝንበትና ኪሱን የሚዳብስበት ነበር። ካለው ላይ ሳይሰስት እንዲሰጥ የገፋፋ በመሆኑም ብዙ ገቢ እንዲሰበሰብበት ሆኗል። በገቢውም ብዙዎች ከችግራቸው ተላቀዋል።

እንግዳችን ለሀገራቸው ዲፕሎማትም ናቸው። ማለትም በተለይም ተማሪዎችን ከማስተማር አንጻር በሥዕሉ ብቻ ሳይሆን ከዚያም አልፈው ይሄዳሉ። ለአብነት ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ መሆኗን ሉሲን በመጥቀስና የሰዎች ሁሉ እናት መሆኗን በማስረዳትም ይሰብካሉ። ለዚህ መነሻቸው ደግሞ የተማሪዎች ጻብ እንደሆነም ያነሳሉ። ጣሊያን ላይ እያሉም ከኢትዮጵያ ኢንባሲ ጋር በቅርበት ይሰሩ ነበር። የእጅ ሥራ ውጤቶቻቸውን ማለትም በነሐስና በእምነበረድ የተለያዩ ቅርጻቅርጾችን የሠሯቸውን ለአንባሲው አበርክተዋል። ኢትዮጵያዊያን በሚሳተፉባቸው መድረኮች ሁሉ እየተገኙ የቻሉትን የሚያበረክቱም ሆነው ቆይተዋል። ከዚያም በኋላ አሁን በሚሰሩበት ሉክሰንበርግ ወይዘሮ ሄኖኬ ወልደ መድህን በምትባል ኢትዮጵያዊት በተቋቋመ «REE» የሚባል ድርጅት ውስጥም ይሳተፉሉ። ድርጅቱ በሕጻናት ላይ ልዩ ትኩረት በማድረግ የሚሰራ ሲሆን፤ ከ20 ዓመት በላይም በድርጅቱ ውስጥ በማገልገላቸው ብዙ ነገር ለአገራቸው እንዲበረከት አስተዋዕጾ ካደረጉ መካከል ናቸው። የኢትዮጵያ ሕጻናት በሚደገፉበት ሁሉ እርሳቸው አሉ።

በቅርቡም በጦርነቱ ለተጎዱ አካባቢዎች የሚያደርጓቸው ነገሮች እንዳሉ የነገሩን አርቲስት እጅጋየሁ፤ አንዱ የድርጅቱ ፕሬዚዳንት በሆነችው እንስት አማካኝነት የተሰበሰበው የህክምና ቁሳቁስ ሲሆን፤



ሁለተኛው እርሳቸው ከሚያስተምሩበት ትምህርትቤት የተሰጣቸው ኮምፒዩተር ነው። ይህም በኮንቴነር ታሽጎ እየተጓጓዘ ያለ ነው። በአጭር ጊዜ ለተጎዱት ተቋማትም ይደርሳል የሚል እምነት አላቸው ። እርሳቸው በምክትል ፕሬዚዳንትነት የሚመሩት ይህ ድርጅት ቀደም ባሉት ጊዜያትም ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር በመነጋገር ድጋፎችን አድርጓል። በተለይም የአገር ውስጥ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ላይ ሰፊ ሥራ ሰርቷል። ከእነዚህ መካከልም ድርጅቱ « ጸረ ወባ » ከሚባል ድርጅት ጋር በመተባበር በባህርዳር ክሊኒክ ማሰራቱ አንዱ ነው።

«ስለ እናት » ከሚባል ድርጅት ጋርም እንዲሁ በመንግስት ፈቃድ መሰረት እየሰሩ ይገኛሉ። አሁንም ቢሆን ኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰሩና ድጋፍን የሚሹ ብዙ ነገሮች ስላሉ መንግስት ከፈቀደላቸው ከድርጅቶች ጋር በመሆን ለመስራት ቁርጠኛ ናቸው።

**መልእክተ እጅጋየሁ**

«ዘረኝነት አይገባኝም ነበር። ጥቁር ነች ተብዬ መገለልን እንኳን ያወኩት በብዙ ነገር ከተፈተንኩ በኋላ ነው። ምክንያቱም ኢትዮጵያዊያን ከልጅነታችን ጀምሮ ያደግነው ጠንካራ፣ ነጻና ማንም የማይወስንልን መሆናችንን እየተነገረን ነው። አሁንም የኃያልነታችንና የአልደፈርም ባይነታችን ምንጭ ያ አስተዳደጋችን ነው ብዬ አስባለሁ። ነገር ግን ማንነት በጥቅም ሲለወጥ ነገሩ ተበላሸ። ፍቅር ቦታውን ለገንዘብ ለቀቀና መቃቃር መጣ። ይህም ቢሆን ግን ተስፋችን ሁሌም ይኖራል። ምክንያቱም እኛ በችግር የተፈተን እንጂ የወደቅን አይደለንም። ስለዚህም ምንም እንኳን ጨለማው የበዛብን ቢመስለንም ብርሃኑ ግን እሩቅ አይደለምና በእምነታችን ይህንን ልናጠነክረው ይገባል» የመጀመሪያው መልእክታቸው ነው።

የቤት ቆሻሻ በቤተሰብ እንደሚጠረግ ሁሉ የአገርም ችግር በጥበብ ኃይል ይጸዳል የሚሉት ባለታሪካችን፤ አሁን የመቃቃራችን ምስጢር ከየትም የመጣ ሳይሆን እኛ በከፈትነው ቀዳዳና ባለመሥራታችን እንደሆነ ይናገራሉ። አንድነትን በሚያመጡ ጉዳዮች ሁሉ ላይ አለመሥራታችን ቤተሰባዊ ግንኙነታችንን አላልቶታል ባይ ናቸው። ያለንን ተሞክሮና ሙያ ተጠቅመን ብንሰራ አይደለም አገራችንን ሌላንም መታደግ እንችል ነበር። ሆኖም ሥነ ጥበቡም ላይ ሆነ ሌሎች ዘርፎች ላይ ያለነው ባለሙያዎች አቅማችንን አሟጠን ስለ አገራችን አልመሰከርንም። አልሰራንምም። ይህ ደግሞ የውጪው ጣልቃ ገብነት እንዲሰፋ አድርጎታል። እናም አሁን ነቅተን ጥፋታችንን ወይም ችግራችንን እኛው በእኛው መፍታት አለብን። ሌላ እንዲፈታልን አንፍቀድ። በራችንን ከከፈትን አጣልተውን በእኛ ገንዘብና ሀብት ይከብራሉ። ከዚያም አልፎ ሴረኞችን እናበረክታለን። ስለሆነም በጥበብ ኃይል ቆሻሻውን አጽድተን ጥፋተኞች ይቅርታ እንዲጠይቁና አንድነታችን እንዲጎለብት እንስራ ይላሉ።

ለውጪዎች ራሳን አሳልፈን መስጠትም መቆም እንዳለበት የሚጠቁሙት ባለታሪካችን፤ እነርሱ የእኛን ውድቀት እንጂ ልማት አይፈልጉም። እንዳሸማቀቅናቸው ማሸማቀቅ እንጂ ቀና እንድንል አይፈቅዱልንም። እየደረሱ ያሉ ጫናዎችም መልከ ብዙ የመሆናቸው ምስጢር ይህ ነው። እናም አሁን ያለንበት ጊዜ ከምንም በላይ ሁላችንም በያለንበት መስክ ኢትዮጵያን ለማስቀጠል በጋራ የምንቆምበት ጊዜ ላይ ነን። ኢትዮጵያ የጋራ አገራችን እስከሆነች ድረስ የሚደረገው መስዋዕትነትም አገር ለማሻገር እንጂ የአንድን አካል ፍላጎት ለማሟላት እንዳልሆነ መረዳቱ ተገቢ ነው። የምናደርገው ርብርብ የሁላችንን ፍላጎት የሆነችውን ኢትዮጵያ ወደፊት ለማስቀጠል መሆን ይገበዋልም ሲሉ ይመክራሉ።

ከውስጥም ከውጪም የሚሰነዘርብን ጥቃት በጋራ ከቆምን መመከት እንችላለን። እስካሁን በመጣንበት መልኩ ከተጓዝን ደግሞ ምንም እንኳን መልከ ብዙ ባህሪ ያላቸው ጥቃቶች ቢደርሱብንም እንደምናሸንፈው መጠራጠር የለብንም። ጸንተን ቆመንና ጥንካሬያችንን በአንድነት ገንብተነው ከተሻገርነው የማንቆፍረው ድንጋይ ሊኖር

አይችልም። ለዚህ ደግሞ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በያለበት በጎ አስተዋጽኦ ማበርከት አለበት ሌላው ምክራቸው ነው።

## ማረሚያ

ባለፈው ሳምንት በዚሁ አምድ ስር ባወጣነው ጽሑፍ "የኢትዮጵያ ማህበራዊ ኢንሹራንስ" የሚለው በ"የኢትዮጵያ ማኔጅመንት ኢንስቲቲዩት"፤ "የአማራ ማህበራዊ ኢንሹራንስ" በ"የአማራ ማኔጅመንት ኢንስቲቲዩት"፤ "ዶ/ር አለማየሁ አዘዘ" የሚለው በ"ዶ/ር አለማየሁ አረዳ"፤ እንዲሁም "ረ/ ፕሮፌሰር ዘሪሁን" የሚለው "ተ/ፕሮፌሰር ዘሪሁን" እንዲስተካከል እየጠየቅን ለተፈጠረው ስህተት ይቅርታ እንጠይቃለን።

ኢኮኖሚ

# ባህልና ቱሪዝም

# በልጃገረዶች የሚደምቀው አሸንዳ፣አሸንድዬ፣ሻደይ፣ሶለል

ስምስም መንግሥቱ

ልጃገረዶቹ ከፀጉር እስከ እግር ጥፍራቸው ለመዋብ የማያደርጉት የለም። ፀጉራቸውን ሹሩባ ይሰራሉ፤ የእጅና የእግር አልቦው፣ከብር የተሰራ የአንገት ጌጥ የአይን ኩሉም አይቀርም። የሚለበሰውም በእጅ የተፈተለ የሀገር ባህል ልብስ ነው።

አሸንድዬ የሚባል ቄጠማ ደግሞ ከወገብ በታች በልብሱ ላይ ይውላል። ከወገብ በታች የሚንዘረፈፈው ቄጠማ በጨዋታ ወቅት ሲወዛወዝ አሸንድዬ፣ ሶለል፣ ሻደይ ለሚጫወቱ ልጃገረዶች ድምቀት ይሰጣቸዋል።

ከልጃገረዶቹ መካከል ግጥም ለማውጣት የተመረጠችው ውዳሴ፣ ሙገሳና ወቀሳ በዘፈን መልክ ስታቀርብ በተቀባዮች በከበሮና በጭብጨባ ሲታጀብ ታዳሚውን ያስደምማል።አልባሳቱም መዋቢያውም ዘመን አመጣሽ አለመሆኑ ደግሞ ለባህል የተሰጠውን ትኩረት ያሳያል።

በግጥምና ዜማ የሚጫወቱትም ባህልን መሠረት ያደረገ ነው። ልጃገረዶቹ ምንም እንኳን በእለቱ የበለጠ ተውበው ቢታዩም፣ ባአካባቢው የሚገኙ ባህላዊ መዋቢያዎችን ነው የሚጠቀሙት። ከአዘቦቱ ለየት ብለው መታየታቸው ደግሞ ቀልብን እንዲስቡ ያደርጋቸዋል። የሁሉም አይን ያርፍባቸዋል። አጠቃላይ ባህላዊ እሴቱ ያመዝናል።

በእንዲህ ካለው የልጃገረዶች ጨዋታ እጮኛ ለመፈለግ የሚያንዣብብ ወንድ አይጠፋም። ይህም አንዱ የባህል መገለጫ ነው። አሁን በምንገኝበት ዘመን በተለያየ አጋጣሚ በሚፈጠር ግንኙነት ሳይሆን አንድ ወንድ ለትዳር የምትሆነውን ለመፈለግ እንዲህ ያለውን አጋጣሚ ይጠቀማል።

ታዲያ ይህን አጋጣሚ ተጠቅሞ ከሚጫወቱት መካከል እጮኛ የሚፈልግ ወንድ ምርጫው ላይ ጥንቃቄ እንዲያደርግ ይመከራል። ምክንያቱ ደግሞ በእለቱ በሚጠቀሙት መጋጌጫ ውበታቸው ጎልቶ ስለሚወጣና ሁሉም አይንን የሚስቡ በመሆናቸው መልክ መረጣ ላይ ያኔ በውበቷ ተማርኮ በኋላ ላይ እንዳይቆጭ ነው ምክሩ። በዚህ ምክንያት በዚህ ጊዜ የሚደረግ የእጮኛ ምርጫ ቢቀር የሚሉም አይጠፉም።

ልጃገረዶቹ ንጹህና ውብ ሆነው ለመጫወት ከነሐሴ ወር መግቢያ ጀምሮ በየአካባቢያቸው ይሰባሰባሉ፤ ይመካከራሉ፤ ቀኑንም በጉጉት ነው የሚጠባበቁት። እንኳን ልጃገረዶቹ ባልቴቶቹም ቢሆኑ የጨዋታው ተሳታፊዎች በመሆናቸው ይናፍቃሉ።

የልጃገረዶች ጨዋታ ተብሎ የሚታወቀው አሸንድዬ፣ሶለል፣ሻደይ መነሻው ወይንም ይዘቱ ኃይማኖታዊ ነው። በኦርቶዶክስ አማኞች ዘንድ የፍልሰታ ጾም ለ16 ቀናት ከተጾመ በኋላ በ16ኛው ቀን ጾሙ ይፈታል። ልጃገረዶቹ ከጾም ፍችው ቀን ጀምሮ ለቀናት በየቤቱ እየዞሩ የሚጫወቱት ደግሞ ባህላዊ መልክ አለው። መልካም ተብሎ ከሚጠቀሰው የማህበረሰብ እሴቶች አንዱ መመራረቅና ቸር መመኘት በመሆኑ ልጃገረዶቹ በየቤቱ እየዞሩ ሲጫወቱ ይመረቃሉ፤ እነርሱም ይመርቃሉ፤ ለከርሞ በሰላም ለመገናኘት ቸር ይመኛሉ።

ይህ ሁሉ ባህላዊ እሴቱ የሚናፈቅ በመሆኑ ነው ማህበረሰቡም ልጃገረዶቹን በየቤቱ ተዘጋጅቶ የሚጠብቃቸው። ቤቱ ሲገቡም ቤት ያፈራውን ለበዓል የተዘጋጀ ምግብና የሚጠጣ ይቀርብላቸዋል። እነርሱም የሄዱበትን ቤት ባለቤት ገና ከበር ጀምሮ ነው እያወደሱ ወደ ውስጥ የሚዘልቁት።

ቤት ውስጥ ከገቡ በኋላ ደግሞ የሚደረግላቸው መስተንግዶ ጥሩ ከሆነ ሙገሳውን ያዥጎደጉዱታል፤ በደንብ ይጫወታሉ። መስተንግዶው ለስሜታቸው ጥሩ ካልሆነ ደግሞ ስድብ አዘል ነቀፌታ በማቅረብ የቤቱ ባለቤት መልእክታቸው እንዲገባው በጨዋታቸው ጠቆም በማድረግ ወደሚቀጥለው ቤት ያመራሉ።

በዚህ ሁኔታ አካባቢያቸውን ያካልላሉ። ቤተሰብ ለልጆቹ ነፃነት የሚሰጥበት ጊዜ ነው። በአካባቢው የሚፈራ ወይንም ከማህበረሰቡ በኑሮ የተሻና የሚከበር እንኳን ቢሆን ቤቱ ለሚጫወቱት ልጃገረዶች ክፍት ነው። መስተንግዶውንም ካላሳመረ ከመተቸት



አያመልጥም። የነፃነት ልኩ እስከዚህ ድረስ ነው የሚገለጸው። የቤተሰብ ቁጥጥር ያለባት ልጃገረድ እንኳ በዚህ የጨዋታ ጊዜ አትከለከልም። ከጓደኞችዋ ጋር በጨዋታ እንድታሳልፍ ይፈቀድላታል።

ከነሐሴ 16ቀን ጀምሮ የሚካሄደው የልጃገረዶች ጨዋታ ተብሎ የሚታወቀው ይህ ወቅት በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በእጅጉ ይታወቃል። በተለይ ደግሞ በትግራይና አማራ ክልሎች በየአመቱ ይከበራል። ባህላዊ ጨዋታውም በአንዳንድ ነገር ካልሆነ በስተቀር መሰረታዊ የሚባል ልዩነት እንደሌላው ነው መረጃዎች የሚያሳዩት። ይህ የልጃገረዶች ጨዋታ የአዲስ አመት መድረስንም የሚያሳይ በመሆኑ ድባቡና ስሜቱ ይለያል።

ዘንድሮም በአሉን ለማክበር ዝግጅቶች እየተደረጉ ናቸው። ከዋዜማው ጀምሮ ድባቡ አካባቢን የሚያደምቀው የልጃገረዶች ጨዋታ አዲስ አበባ ከተማንም ሞቅ ደመቅ እያደረጋት ነው። በዓሉን አስመልክቶ የሚከናወኑ ዝግጅቶችም በማስታወቂያ አስቀድሞ ተላልፈዋል። ዋናው በዓሉ የሚካሄድባቸው በተለይም የአማራ ክልል የተለያዩ ቅድመ ዝግጅት ማድረጉን በተለያየ የመገናኛ ዘዴ አስነግሯል። በማህበራዊ ድረገጾች የሚለቀቁት መረጃዎች የበዓሉን መድመቅ የሚያሳዩ ናቸው።

ከጥቂት አመታት በፊት ኑሮዋን አዲስ አበባ ከተማ ያደረገችው ወጣት ገነት መብራቱ ተወልዳ ባደገችበት ትግራይ ክልል መቀሌ ከተማ ከአካባቢ ጓደኞችዋ ጋር የነበራትን የአሸንድዬ የጨዋታ ጊዜ ሁሌም ታስታውሰናለች። እርስዋና የአካባቢዋ ልጆች በእለቱ ስለሚለብሱትና ስለሚያደርጉት ጫማ እንዲሁም ስለሚዋቡበት መጨነቅ የሚጀምሩት ከነሐሴ ወር መግቢያ አንስቶ ነው።

ይህንንም የሚያሟላላቸው ቤተሰብ በመሆኑ ቀድሞ ቤተስብን ማሳሰብ አለባቸው። አዲስ ልብስ መግዛት ባይቻል እንኳን በእለቱ የሚለበሰው የባህል ልብስ በመሆኑ እናቶቻቸው የሚለብሱትን ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል። የባህል አልባሳቱ በጥልፍ የተዋቡ ቢሆኑ ይመረጣል። ዋናው ግን የባህል ልብስ መሆኑ ነው የሚፈለገው።

ለመዋቢያ ስለሚጠቀሙባቸው ጌጣጌጦች ወጣት ገነት እንደነገረችኝ በሹርባው ላይ በግንባር ላይ ‹‹ጨጉኻጉሂት››የሚባል ጌጥ ይደረጋል። በጨሌ የሚሰራ ጌጥ ነው። ጨሌ ካልተገኘም የተለያየ ቀለማት ባለው ክር ይዘጋጃል። ድሪ የሚባል ደግሞ በእጅና በአንገት መካከል ከቀሚሱ በላይ የሚውል ጌጥ ነው። ይሄም ጌጥ የተለያየ ቀለም ባለው ክር ነው የሚሰራው። በወገብ ላይም መቀነት ይደረጋል።

ለአንገት ጌጥ ደግሞ በመጠን የተለያዩ ሶስት መስቀሎች በክር አጭር፣መካከለኛና ረጅም ሆኖ ውበት ባለው መልኩ ይደረጋል። በመጠን አነስተኛዋ መስቀል በአካባቢው ‹‹ህንቆ››ተብላ ትጠራለች። ትልቁ መስቀል ደግሞ ‹‹ዝብጦ››ይባላል። ሶስቱን መስቀል ማድረግ ካልተቻለ ከነህስ ወይንም ከብር የተሰራ ጌጥ ይደረጋል። ከብር የተሰራ ቢሆን ግን ይመረጣል። የእግር አልቦው አስገዳጅ ባይሆንም ማሟላት ከተቻለ ቢደረግ ይመረጣል። ለእግር ጫማ ደግሞ ኮንጎ ነው የሚደረገው። በዚህ ሁኔታ ነው ልጃገረዶቹ ደምቀው ለመታየት ጥረት የሚያደርጉት።

የልጃገረዶቹ ጨዋታ የሚጀምረው ነሐሴ 16 በመሆኑ ለጨዋታው የሚሰባሰቡትም በዚህ ቁጥር የተገደቡ ይሆን ብዬ አሰቤ ወጣት ገነትን ጠየኳት። እርስዋም የአካባቢው ልጆችና ጓደኛማማቾች ናቸው የሚሰባሰቡት። ስብስቡም በቁጥር አይገደብም አለችኝ።

ጨዋታው የሚጀመረው ነሐሴ 16ቀን ከሰአት በኋላ ነው። ጨዋታውም በምስጋና ለመጀመር በዕለቱ አብረው ለመጫወት የተሰባሰቡት ልጃገረዶች አስቀድመው በየአካባቢያቸው ወደሚገኘው ቤተእምነት ይሄዳሉ። ከእምነት ተቋም መልስም ተሰባስበው ‹‹መፀት፣መፀት አሸንዳ...››ብለው በዓሉን የሚያበስር ጨዋታ ይጫወታሉ።

ወደ መኖሪያ ቤቶች በመሄድ የሚጫወቱት ግን በማግሥቱ ነው። የሚሄዱበት ቤትም አይመረጥም። አቅማቸው እስከፈቀደ ድረስ አካባቢያቸውን ያዳርሳሉ። ወደየቤቱ ሲሄዱም ሲቃረቡ ‹‹ዞማአዲ አንበሳ አድሎሚ ህዝምበለ ሀውደርህገዞአሚ››ይላሉ። እዚህ ቤት ውስጥ አንበሳ አለ ወይ ከቤቱ በስተኃላ ድምጽ ይሰማል እንደማለት ነው።

የሄዱበት ቤት በሩ ዝግ ከሆነባቸው ደግሞ የቤቱ ባለቤት በሩን እንዲከፍትላቸው ‹‹አጋፋሪ ጎይታይ በሪህዘኛ ክፈት እዚህ በረኛ››ይላሉ። ጌቶች ከበርዎ ላይ ቆመናል፤ በሩን ክፈቱልን እንደ ማለት ነው። የደጁ በር ተከፍቶላቸው ወደ ውስጥ እንዲገቡ ሲጋበዙ ማወደስ ይጀምራሉ። የቤቱን እማወራ ‹‹አቲ እቤቴ ፀሐዬ መፃዬ ኮ መፃዬ...››እያሉ ያወድሳሉ። የቤቱ ባለቤትም ከተጫወቱ በኃላ ምግብ ያቀርባሉ። ገንዘብም ይሰጣሉ።

እዚህ ላይ ግን ስጦታውና መስተንግዶው በአቅም ነው። ሁሉም አቅሙ የቻለውን ነው የሚያደርገው። ተጫውተው ሲወጡም ጥሩ መስተንግዶ ከተደረገላቸው እንደ ነሐሴ ዝናብ ፈሰሰልን ብለው ምስጋናቸውን በዘፈን ያቀርባሉ። ስስት ያሳየውን ደግሞ ‹‹ይሄ ሰው ሽሮ ነው የሚበላው እንዴ በዓሉን የረሳው››የሚል መልእክት ያስተላልፋሉ። እንዲህ በየቤቱ ዞረው ያገኙትን ገንዘብ አለመከፋፈላቸው ደግሞ ለየት ያደርጋቸዋል። ገንዘቡን በሙሉ ለቤተክርስቲያን ነው የሚሰጡት።

ወጣት ገነት በሀገር ቤት የነበራትን የልጅነት ትዝታዋንም እየቀሰቀስኩባት ስለነበር በጨዋታችን መካከል ሀሳብ ውስጥ ገባች። እንደ ልጅነቷ ባይሆንም ቀኑን ለማሰብ ከጓደኞችዋ ጋር ለመዋል ነው እቅዷ። በዓሉ ለእርስዋ ልዩ ስሜት ይሰጣታል። በአሉን ‹‹ውስጤን እስኪያመኝ ድረስ ነው የምወደው›› የምትለው ወጣት ገነት፣ በልጅነትም፣በዕድሜም ከፍ ቢሉ ለጨዋታው ያለው ስሜት አይለያይም ትላለች። እንደውም ከፍ ሲባል የበዓሉን ትርጉም ለመረዳት ጥረት እንደሚደረግና በዓሉ ባህላዊ ይዘቱን ሳይለቅ እንዲከበር መቆርቆሩ የበለጠ እንደሚሆን ነው ያጫወተችኝ።

አሁን ላይ በዓሉ በተለይ በከተሞች ባህላዊ ይዘቱን ይዞ እየቀጠለ እንዳልሆነ ይሰማታል፤ ተበርዟል ብላ የምታምነው በአልባሳቱ ነው። በተለይ በከተማ የባህል አልባሳት ሽፎን በሚባል የጨርቅ አይነት መተካቱ ነው። ፀጉርም ሹሩባ መሰራት ያለበት ሰውሰራሽ ዊግ የሚባለው ተቀጥሎ ሳይሆን፣የተፈጥሮ ፀጉር መሆን እንዳለበትና ከተፈጥሮ ውጭ የሆነው መዋቢያ ከባህል ውጭ እንደሆነ ታስረዳለች።

የበዓሉ መገለጫዎች የሆኑት ሁሉ መቅረት እንደሌለባቸው ታምናለች። እንደርታ፣ተንቤን፣ራያ አካባቢዎች ባህሉን ጠብቆ የሚካሄደው የልጃገረዶች ጨዋታ በከተሞችም በተመሳሳይ መሆን እንዳለበት ትገልጻለች።

ከተማ ተወልዳ ብታድግም ከመቀሌ ወጣ ብሎ በሚገኝ ሶፎሎ በሚባል አካባቢ ነዋሪ የሆኑ አክስቷ ጋር ሄዳ የአካባቢው ልጃገረዶች በዓሉን በምን ሁኔታ እንደሚያከብሩት ለማየት ዕድሉን አግኝታለች። በዚህም በከተማና በገጠሩ መካከል ያለውንም የበዓል አከባበር ልዩነትም ተገንዝባለች።

በዕድሜ ከፍ ማለቷና በትምህርት መግፋቷ ደግሞ የበለጠ ለባህሉ ትኩረት እንድትሰጥ አድርጓታል። ከእንግዲህ በኃላ ጨዋታውን መጫወት ብቻ ሳይሆን፣ ባህሉ ተጠብቆ እንዲቀጥልና ዓለምም እንዲያውቀው ለማድረግ የግሏን አስተዋጽኦ ለማበርከት እቅዱና ፍላጎቱ አላት፤ ነገሮች ከተመቻቹላት።

ወጣት ገነት ባህሉን ጠብቆ ለማቆየትም ሆነ ሁሌም በደስታ በዓልን ለማሳለፍ ሰላም መቅደም አለበት ትላለች። አሁን በሀገሪቱ የሚታየው የሰላም እጦት ተወግዶ ህዝቦች በሰላምና በፍቅር እንዲኖሩ ምኞቷ ነው። ‹‹አሸንዳ ማለት አንድነት፣ሰላም፣ነጻነት የሚገለጽበት ነው››በማለት ሁሉም በዚህ እሳቤ ለሰላምና ለፍቅር ከተጋ የተሻለ ነገር ይመጣል የሚል እምነት አላት።

ወጣት ገነት የሰላም እጦት የምትወደውን አሸንዳ የልጃገረዶች ጨዋታ በትውልድ አካባቢዋ እንዳታከብር አድርጓል። በአሁኑ ጊዜም በተለምዶ ቡና ጠጡ በሚባለው ንግድ ሥራ ላይ ተሰማርታ ኑሮዋን እየመራች ትገኛለች። የሰላም እጦቱ በባዮቴክኖሎጂ የትምህርት ዘርፍ ሁለተኛ ዲግሪ እያላት ከሙያዋ ውጭ በሆነ ሥራ ላይ እንድትሰማራ እንዳደረጋትም ትናገራለች።

አሸንዳ የልጃገረዶች በዓል አንዱ የቱሪዝም መስህብ ሆኖ ለሀገር ገቢ ማስገኛ ሊሆን እንደሚችል መዘንጋት የለበትም። ይሁን እንጂ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ባጋጠመው ጦርነት በዓሉ በተለይም በዋናነት በሚከበርባቸው አካባቢዎች ተቀዛቅዞ መቆየቱ ይታወቃል።

አሁን ላይ ደግሞ በሚታየው አንጻራዊ ሰላም መነቃቃቶች ተፈጥረዋል። በአሉ ባለፈው አመት ከጸጥታ ችግር ጋር ተያይዞ ባይከበርም ዘንድሮ እንደሚከበር ታውቋል።

በዚህ ላይ የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ ተጠይቀው በሰጡት ማብራሪያ እንዳሉት፤ በዓሉ ለሀገሪቱ የቱሪዝም እንቅስቃሴ አስተዋጽኦ እንዲኖረው በተለይም በላልይበላ ከተማ ላይ በዓሉን መሠረት የደረገ ሲፖዚየም ለማካሄድና በዚህ ላይ ጥናታዊ ጽሁፎች ቀርበው ውይይት እንዲካሄድባቸው መድረክ ለማዘጋጀት ታቅዷል።

ዝግጅቱ የቱሪዝም ማህበረሰቡንም ለማነቃቃት የሚያስችል መሆኑን ጠቅሰው፣ ለዚህም ጥሩ አጋጣሚ እንደሚፈጠር ታምኖበታል ይላሉ። የላልይበላ አካባቢ ማህበረሰብ አብዛኛው በቱሪዝም ኢንዱስትሪው የሚተዳደር በመሆኑ በሆቴል፣በትራንስፖርትና በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ዝግጁ እንዲሆን ይነቃቃል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም በዚህ አቅጣጫ እየሰራ እንደሚገኝ ጠቅሰው፣ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል አጋጥሞ በነበረው ጦርነት ተቋርጦ የነበረው የአየር በረራ በመጀመሩ ለቱሪዝም ኢንዱስትሪው መልካም የሆኑ አጋጣሚዎች እንደሚፈጠር ተስፋ ተጥሏል ይላሉ።

አሸንዳ፣አሸንድዬ፣ሻደይ፣በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና ባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) በማይዳሰሱ ወካይ ቅርሶች ለማስመዝገብ ጥረቶች እንደነበሩ ይታወሳል።መልካም በዓል።

# ሳምንቱን በታሪክ

# የሰማዩ ባቡር ትዝታ

ተገኝ ብሩ

የመጀመሪያው አውሮፕላን ወደ ኢትዮጵያ ከገባ ነሐሴ 12 ቀን 93 ዓመት ሞላው። በነዚህ ዓመታትም የአገሪቱ አቪየሽን ዘርፍ ብዙ ውጣ ውረዶችን አሳልፎ ዛሬ ላይ ለትልቅ ስኬት በቅተል። በዛሬው የሳምንቱን በታሪክ አምዳችንም የመጀመሪያው አውሮፕላን ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ የነበረውን ኩነት ከሪፖርተር ጋዜጣና ከሌሎች ምንጮች ያገኘነውን መረጃ እንደሚከተለው አጠናክረነዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ በሰማው አዲስ ነገር ተደንቆ ከረመ። ይህ መደነቅ ጉጉት ፈጥሮበታልና ከባዱ የክረምት ብርድ ከቤቱ አላዋለውም። በዚያን ወቅት በተሰበሰበበት አጋጣሚ ሁሉ በከተማው ስለተናፈሰው እንግዳ ነገር ሲያወጋ ከርሟል። ተሰባስቦ ቡና ሲጠጣ፣ በእድርና እቁብ ሰበብ ሲገናኝ፣ ቤተሰብ ሰብሰብ ብሎ ወግ ሲያደራ በቅርቡ ይሆናል ስለተባለው ጉዳይ እያነሳ አጀብ አለ።

በሰማው ነገር እጁን በአፉ የማይጭን ከቶም አልነበረም። ወሬው ሁሉ አዲስ የሚሰማው አስደናቂ ነገር ሆነ። ቀኑ ሲደርስ ንጋት ላይ ተጣራርቶ አጀብ የተባለለትን ነገር ለማየት ወጣ።

ነሐሴ 12 ቀን 1921 ዓ.ም የአዲስ አበባ ነዋሪ የሰማውን ለማመን፤ የተባለውን አዲስ ክስተት ለማረጋገጥ ከ15 ኪሎ ሜትር በላይ አቋርጦ በባዶ እግሩ ወደ ገፈርሳ ሜዳ ተመመ። ነዋሪው ለጉዳዩ አዲስ ነበርና እንኳን አምኖ መቀበል፣ ጭራሽ ለማሰብ ፈጽሞ አይቻለም ያለውን እውነት ለማረጋገጥ በቦታው ተገኘ። ይህ ክስተት ከተከሰተ ያለፈው ነሐሴ 12 ቀን 93 ዓመት ሞላው።

ክስተቱ እንግዳ በመሆኑ የህዝቡ ስሜት የተለየ ነበር። የአገሪቱ ንጉስ ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ከነሚኒስትሮቻቸው፣ መኳንንቱ፣ መሳፍንቱ፣ ዲፕሎማቶችና የሃይማኖት አባቶች ሳይቀሩ የታደሙበት ነበር። ይሄ ክስተት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ እጅግ እንግዳ የሆነውን ነገር ይዞ መጣ። ገፈርሳ ከወትሮ በተለየ በአበባ ተሸቆጥቁጣ፣ በዘንባባ ተሞሽራና በሰንደቅ ዓላማ አሸብርቃ አዲሱን ሁነት ለማስተናገድ ትጠባበቃለች።

ይህ ሁሉ ጉጉትና ጥበቃ ያኔ ብዙዎች «በራሪው የሰይጣን ክንፍ» ያሉትን አውሮፕላን ለማየት ነው። እዚያ ሜዳ ላይ የተሰባሰበው ሕዝብ በርቀት በሚያያቸው አሞራዎች ሁሉ አዲሱ እንግዳ እየመሰለው ቆየ። ሰማይ ላይ አይኑን ተክሎ «በራሪው ሰይጣን» ያለውን የመጀመሪያውን አውሮፕላን ለማየት ጓጓ።

ከብዙ ቆይታ በኋላ ግን የሆነ ድምፅ ከርቀት ወደ ህዝቡ ቀስ በቀስ ይቀርብ ጀመር። ሕዝቡ በየአቅጣጫው ባለ የሰማይ ጥግ በዓይኑ አማተረ። ወቅቱ ክረምት ነው፤ ሰማዩ ዳምኗል። ምንም የሚታይ ነገር ሳይኖር ድምፅ ብቻ ይመጣል። ቆይቶ ግን ድምፁም በጣም እየቀረበና ይበልጥ እየጮኸ መጣ። ያኔ ጉጉቱ ወደ ፍርሀት ተቀየረ።

ከጥቂት ቆይታ በኋላ የክረምቱ ጭጋግ ከተዋጠው ሰማይ፣ ያ ሲጠበቅ የነበረው «በራሪው የሰይጣን ክንፍ» ደመናውን ቀዶ ወጣ። ወደ መሬት መቅረብም ጀመረ። ሕዝቡ በድንጋጤ በየአቅጣጫው ይፈረጥጥ ጀመር። ታሪካዊው የመጀመሪያው አውሮፕላን ገፈርሳን ደጋግሞ ዞሮ ድንኳኖቹ ፊት ለፊት ዠርገግ ብሎ አረፈ።

የህዝቡ ትርምስ ቆመ፣ ድንጋጤው ወደ ደስታ ተቀየረ። ገፈርሳም ተደሰተች፣ ፉጨትና ጩኸት በረከተ። ሕዝቡ ካፒቴኑን ተሸክሞ ተቀበለው። ንጉሱ ዘለው ከድንኳናቸው ወጡ። ተስፈንጥረው ካፒቴኑ ላይ ተጠመጠሙበት። ይህ ሁሉ የሆነው የመጀመሪያዋ ፓቴዝ አውሮፕላን ወደ አገራችን በመምጣቷ ነበር።

መንገድ ሳይሠራለት፣ ሐዲድ ሳይነጠፍለት በአየር ላይ ተንሳፎ የመጣው ያ አውሮፕላን የአየር ባቡር የሚል ስም ወጣለት። በዚህ ሁኔታ ነበር የዛሬ 93 ዓመት በኢትዮጵያ የአቪዬሽን ታሪክ የተጀመረው።

ንጉስ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አቀባበሉን በማስመልከት እዚያው ለተሰበሰበ ህዝብ እንዲህ በማለት ንግግር አደረጉ። "ኢትዮጵያ በጥንት ሥልጣኔዋ ዘመን ከኢየሩሳሌምና ከአረብ፣ ከህንድም መንግሥታት ጋር በንግድና በፖለቲካ ትገናኝ ነበር። አሁንም ያንን ማዕረጓንና ኃይሏን ለመመለስ፣ እንዲሁም የአገር ውስጥ ጉዳያችንን በፍጥነት ለመፈጸም እንዲረዳን ይኼንን የአየር ባቡር አስመጣን..."




ይህ የንጉሡን ንግግር ስንመረምረው የአውሮፕላኑ መምጣት ሁለት ዓበይት አላማዎች እንደነበሩት መረዳት ይቻላል። የመጀመሪያው ብሔራዊ ኩራትን መመለስ ሲሆን በዚያውም ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን መቀዳጀት የሚሉ ትልልቅ ዓላማዎች አሉት። ዛሬ ለኢትዮጵያ ኩራት የሆነውና የአህጉሪቱ ታላቁ አየር መንገድ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የዚሁ ዓላማና ጥረት ውጤት ነው።

የመጀመሪያው አውሮፕላን ወደ ኢትዮጵያ የገባበት ዘመን በአገሪቱ የታሪክ ሒደት ውስጥ ከተን ስንመለከተው፣ ከዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ጀምሮ ኢትዮጵያን የማዘመንና የቀድሞ ክብሯን ለመመለስ ሲደረጉ ከነበሩ ጥረቶች መካከል አንዱ ሆኖ እናገኘዋለን።

በኢትዮጵያ አቬየሽን ታሪክ ስራ የተጀመረው ንጉሰ ነገስቱ በገዟቸው 3 የፈረንሳይ ስሪት ፖቴዝ አውሮፕላኖች ነው። የመጀመሪያውና በጽሑፉ መጀመሪያ ላይ የተጠቀሰው ፈረንሳዊው ሙሴ አንድሬ ማዬ ከጅቡቲ በማብረር ነሐሴ 12 ቀን 1921 ዓ.ም ያረፈችው ናት። አውሮፕላኗም «ንስረ ተፈሪ» ተብላ ተሰየመች። ጅቡቲ ቀርተው የነበሩትን ሁለቱን ፖቴዝ አውሮፕላኖች አንዷን ካፕቴን ማዬ፣ ሁለተኛዋን ደግሞ ጀርመናዊው ካውንት ሼዝበርግ እያበረሩ መስከረም 12 ቀን 1922 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ አመጧቸው።

እነዚህ አይሮፕላኖች ከመጡ በኋላ «ንስረ አስፋ ወሰን» እና «ንስረ መኮንን» የሚል ስያሜ ተሰጧቸው ነበር። ከዚያም የፈረንሳይ ተፎካካሪ የነበረው የጀርመኑ ጀንከርስ (Junkers) አውሮፕላን በባሮን ሻን ኢግል አብራሪነት በከተማዋ ውስጥ ጃን ሜዳ አረፈ። በጃንሜዳ ውስጥ በማረፉ ከፈረንሳዩ አውሮፕላን የበለጠ በርካታ ተመልካች እንዲኖር አድርጐታል።

የመጀመሪያ የአገር ውስጥ በረራ ጀንከርስ አውሮፕላን አዲስ አበባ ከደረሰ አንድ ወር በኋላ ነበር የአገር ውስጥ በረራውን የጀመረው። ያ ጉዞው የመጀመሪያው የአገር ውስጥ በረራ መሆኑ ነው። ያልተሳካው የመጀመሪያው በረራ ሊባልም ይችላል። ጀንከርስ የመጀመሪያ የአገር ውስጥ በረራው ሲሆን ተልዕኮውም የኢሊባቡር ጠቅላይ ገዥ የነበሩትን ራስ ናደውን ለማምጣት ነበር። ይህም አውሮፕላን በኢትዮጵያ በሽተኛ ለማጓጓዝ ሲበር የመጀመሪያው መሆኑ ነው። ራስ ናደው በጽኑ ታመው ነበርና የሚተኙበትን አልጋና ፍራሽ ጨምሮ ወደ ዋና ከተማቸው ጐሬ በረራውን ቀጠለ። ነገር ግን በአየር ሁኔታው አመቺ አለመሆን ምክንያት ተመልሶ «እንድብር» አካባቢ ለማረፍ ተገደደ። በማግስቱም ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ።

ከ1921 እስከ 1928 ዓ.ም. ድረስ የነበሩት ሰባት ዓመታት የኢትዮጵያ የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ ጠንካራ መሠረት የተጣለበት ወቅት ነበር። አውሮፕላን ከማብረር እስከ አውሮፕላን መሥራት፣ ከበረራ ትምህርት ቤት እስከ አውሮፕላን መጠገኛ ጋራዥ (ሀንጋር)፣ ከኢትዮጵያውያን አውሮፕላን ጠጋኞች እስከ ሴት አብራሪዎችን ማፍራት የተቻለበት ወቅት ነበር።

በኋላ ላይ የፋሽስት ወረራ በአቬሽን ኢንዱስትሪው ላይ ከፍተኛ ውድመት አደረሰ። በዚያም እጅግ አመርቂ የነበረው ሂደት ተገታ። አገራችን ከፋሽስት ወረራ በ1933 ዓ.ም. ነፃ በወጣች ማግሥት የኢትዮጵያ አየር መንገድ የአገራችን የነፃነት ብሥራት ሆኖ ተቋቋመ። አየር መንገዱ በዚህ ታሪካዊ ወቅት መቋቋሙ ከኋላ የአገሪቱን ቁጭት፣ ከፊት ደግሞ የሕዝቦቿን ራዕይ ተሸክሞ የሚበር አየር መንገድ እንዲሆን አደረገው።

በጻሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ አስተባባሪነት በኢትዮጵያ መንግሥትና በአሜሪካው ትራንስ ወርልድ ኤርላይንስ (TWA) ኩባንያ መካከል በተደረሰ ስምምነት መስከረም 1 ቀን 1938 ዓ.ም በ2 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር የኢትዮጵያ አየር መንገድ በቦርድ ተቋቋመ። የመጀመሪያ ዓለም አቀፍ በረራውንም መጋቢት 30 ቀን 1938 ዓ.ም በአስመራ በኩል በማድረግ ወደ ካይሮ አደረገ።

ከዚህ በኋላ አየር መንገዱ አገሪቱ የምትገኝበትን ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታና የጥንታዊ ቅርስ ባለቤትነት ዕድሎችን እየተጠቀመ በፍጥነት ማደግ ጀመረ። ከተቋቋመ ገና በአራተኛ ዓመቱም ዓለም አቀፍ በረራዎቹን ከካይሮ በተጨማሪ ወደ ጂቡቲ፣ ኤደን፣ ጅዳ፣ ናይሮቢ፣ ፖርት ሱዳን፣ ካርቱም፣ ቦንቤና ካራቺ አስፋፋ።

በኢትዮጵያ የአቪዬሽን ታሪክ ውስጥ አጠቃላይ ኢንዱስትሪውን ሥር ነቀል ወደ ሆነ የላቀ ደረጃ የወሰዱ ሁለት አብዮቶች ተከስተዋል። ሁለቱም አብዮቶች ታዲያ የተከሰቱት በኢትዮጵያ አየር መንገድ የዕድገት ግፊት የተነሳ ነው።

የመጀመሪያው አብዮት የመጣው የኢትዮጵያ አየር መንገድ በ1952 ዓ.ም የቦይንግ ጄት አውሮፕላኖችን ለመግዛት በመወሰኑ ነው። ይህ ውሳኔ አብዮት ያስከተለበት ምክንያት ደግሞ በወቅቱ የነበረውና በጣሊያን የተሠራው የልደታው አየር ማረፊያ፣ አዲስ የሚገዙትን ጄት አውሮፕላኖች የማስተናገድ ብቃት የሌለው መሆኑ ነው። በመሆኑም ውሳኔው ሌላ አዲስ ዘመናዊ አየር ማረፊያ ቦሌ ላይ እንዲሠራ ከማድረጉም በተጨማሪ የቅኝት (Air Navigation) እና የአየር ትራፊክ መቆጣጠሪያ መሣሪያዎችም ከጊዜው ጋር እንዲዘምኑ ምክንያት ሆኗል።

ከአዲሱ ኤርፖርት ግንባታ ጎን ለጎንም አየር መንገዱን ኢትዮጵያዊ የማድረጉ ከፍተኛ ጥረትም የሚዘነጋ አይደለም። የአየር መንገዱን ቁልፍ የሥራ ሒደቶችን (የበረራ፣ የጥገና፣ የሽያጭና የአስተዳደር ሥራዎችን) ከአሜሪካውያን ተረክቦ በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች የመተካቱ ጥረት እየተሳካ ሄዶ፣ በ1963 ዓ.ም. ኮሎኔል ስምረት መድህኔን የመጀመሪያው የአየር መንገዱ ኢትዮጵያዊ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አድርጎ በመሾም ትልቅ እመርታ አስመዘገበ።

ሁለተኛው አብዮት ደግሞ ርዕይ 2025 (እ.ኤ.አ.) ነው። ይህ ርዕይ ልክ እንደ 1952 ዓ.ም. ውሳኔ ሁሉ በአዲስ አበባ ኤርፖርትና በአየር ትራፊክ ቁጥጥሩ ላይ ሥር ነቀል ለውጥ እንዲመጣ ያስገደደ ክስተት ብቻ ሳይሆን፣ የአየር መንገዱንም የውስጥ አደረጃጀት ከመሠረቱ እየቀየረ ያለ ውሳኔ ነው።

እ.ኤ.አ በ2010 የተቀረፀው ይህ የ15 ዓመት የዕድገት መርሐ ግብር አየር መንገዱን ወደ ሰባት የተለያዩ የትርፍ ማዕከልነት በማዋቀር ወደ ግዙፍ የአቪዬሽን ግሩፕ ኮርፖሬትነት እያሳደገው ይገኛል። በዚህም አየር መንገዱን እ.ኤ.አ. በ2025 በ112 አውሮፕላኖች 18 ሚሊዮን መንገደኞችንና 710,000 ቶን ጭነቶችን ወደ 92 ዓለም አቀፍ መዳረሻዎች በማጓጓዝ በዓመት አንድ ቢሊዮን ዶላር ትርፍ ላይ ለመድረስ አልሟል። በእርግጥ አየር መንገዱ በአሁኑ ወቅት የዓለም አቀፍ መዳረሻዎችን ብዛት በመጨመር ከዕቅዱ ቀድሞ ማሳካት ችሏል።

ይህ የአየር መንገዱ ርዕይ የአዲስ አበባ ዓለም አቀፍ ኤርፖርትን በሁለት ዙር፣ በ2004 ዓ.ም በ1.1 ቢሊየን ብር እና በኋላም በአምስት ቢሊዮን ብር፣ ግዙፍ የማስፋፊያ ፕሮጀክቶች ውስጥ እንዲገባ ከማድረጉም ባሻገር፣ የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት በአዲስ አበባ አቅራቢያ ሌላ ግዙፍ የኤርፖርት ከተማ የመገንባት ውሳኔ ላይ እንዲደርስ ምክንያት ሆኗል። በአየር ትራፊክ ቁጥጥሩ ላይም ከፕሮሲጀራል ቁጥጥር እጅግ ዘመናዊ ወደሆነው የራዳር የአየር ትራፊክ ቁጥጥሩ እንዲቀየር ምክንያት ሆኗል። ዛሬ ላይ የኢትዮጵያ አየር መንገድ እንደ ቦይንግ B787 እና ኤርባስ A350 ያሉ ዘመናዊ አውሮፕላኖች ባለቤት ሆኗል። በሌሎች አየር መንገዶች ላይም እያደረገ ያለው ኢንቨስትመንትም የዚሁ ራዕይ 2025 አካል ነው።

በሄደበት የዓለም ጥግ ሁሉ በኩራት የአገራችን አምባሳደር የሆነው አየር መንገዳችን፣ የአገራችንን የቀድሞ «ማዕረጓንና ኃይሏን መመለስ» የሚለውን ታሪካዊ ተልዕኮ በብቃት እየተወጣ ይኼው ዛሬ ላይ ደርሷል።

# የዝነኞች ገጽ


# የማይዝለው ሁለገብ የስፖርት ሰው-እዮብ ተሰማ

**ቦጋለ አበበ**







ትውልድና እድገቱ አዲስ አበባ ነው። በሳንፎርድ እንግሊዝ ትምህርት ቤት ተምሯል። በእግር ኳስ ስፖርት መነሻው የቀድሞው ዝነኛ ክለብ አየር መንገድና ጥቁር አንበሳ ወጣት ቡድኖች ነበሩ። ከነዚህ ክለቦች ጋርም ከልጅነቱ አንስቶ የጠበቀ ቁርኝት ኖሮት ነው ያደገው። የብሔራዊ ቡድን ተጫዋቾች በነበረው ዝነኛው ገረመው ዘርጋ ከልጅነቱ አንስቶ በሚገባ ተገርቶ አድጓል። ‹‹እግሮቹ ከመሮጥ የማይቦዝኑ ስኬታማና ሁለገቡ የስፖርት ሰው ነው›› ይሉታል እዮብ ተሰማን በቅርብ የሚያውቁት።

## እዮብና ማራቶን

በትልቅ ደረጃ ለሚሮጡ እውቅ አትሌቶች የማራቶን ውድድርን ማሸነፍ መቻል ጀግንነት ነው። የማራቶን ሩጫን ተወዳድሮ አርባ ሁለት ኪሎ ሜትሮችን በብቃት ማጠናቀቅ መቻልም ለአንድ ተሳታፊ ትልቁ ስኬት ነው።በእርግጥ እንኳን ለአካል ብቃት፣ ለውጤት ለሚሮጡ አትሌቶችም ማራቶንን ማጠናቀቅ መቻል ቀላል ነገርአይደለም። ለዚህም ይመስላል የርቀቱ መክሊት ያላቸው ኢትዮጵያውያን ወይም ኬንያውያን አትሌቶች ከፊት በሚያጠናቅቁባቸው ውድድሮች የሌሎች በርካታ አገራት አትሌቶች መጨረሻ ሆነው ቢያጠናቅቁ እንኳን ውድድሩን በመጨረሳቸው ብቻ ደስታቸው ወደር ሲያጣ የምናስተውለው።

ታላላቅ አትሌቶች በጉብዝናቸው ወራት ማራቶንን በማሸነፍ አገራቸውን እንደሚያስጠሩት ሁሉ በርቀቱ በርካታ ጊዜ ሮጦ በማጠናቀቅም የአገርን ስም ከፍ ማድረግ ይቻላል። እንደ ኢትዮጵያ ላሉ በርካታ የዓለም ከዋክብት አትሌቶች ሁሌም የማይጠፉባቸው አገራት ይህን ቀለል አድርገው ይመለከቱት ይሆናል። ግን ቀላል አይደለም። ኢትዮጵያ በበርካታ ከዋክብት አትሌቶቿ በማራቶን ስኬታማ የመሆኗን ያህል በርካታ ጊዜ ተወዳድሮ በማጠናቀቅም የሚያስጠራት አላጣችም።

ባለፉት 40 ዓመታት ኑሮውን በአሜሪካን ሎስ አንጀለስ ካሊፎርኒያ ያደረገው ሁለገቡ የስፖርት ሰው እዮብ ተሰማ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው። ይህ ሰው ኑሮውን ባህር ማዶ ካደረገ በኋላ በዩኒቨርሲቲ ፣ በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያውያን ስፖርት ፌዴሬሽንና የብራዚል መለስተኛ ፕሮፌሽናል ቡድኖች ውስጥ በአጠቃላይ ለ19 ዓመታት እግር ኳስን አጠንክሮ ተጫውቷል። ሁለገብ የስፖርት ሰው ሲባልም በምክንያት እንደሆነ ከታሪኩ መረዳት ይቻላል። ይህን ስያሜ የሚያሰጠው በልጅነትና በወጣትነት ዘመኑ የነበረው የእግር ኳስ ሕይወት ብቻ አይደለም። ከእግር ኳስ ታሪኩ በኋላ ወደ አትሌቲክስ ስፖርት ጎራ ብሎ ባለፉት 28 ዓመታት የሰራቸውና እየሰራ ያለው ታሪክ አንድ የሚያስተምረን ነገር አለው። ታታሪነቱ፣ ከዓመት ዓመት አድካሚውን የማራቶን ሩጫ ለመወዳደር እድሜው ገፍቶ እንኳን ደከመኝ ሰለቸኝ ብለው የማይዝሉት እግሮቹ እንዲሁም ስኬቱ ለብዙዎች ተነሳሽነትን የሚፈጥር፣ትምህርትም የሚሆን ነው።

ከሃያ ስምንት ዓመታት በፊት ስኬታማ ወደሆነበት ‹‹የማራቶን ሩጫ ቤተሰብ›› ጎራ ያለው እዮብ በስፖርቱ ከምንም ተነስቶ የጀገነበትን ብዙ ታሪክ ጽፏል። ከዜሮ ጀምሮ ዛሬ የስኬት ማማ ላይ ያስቀመጠው የታላቅ ሙያ ባለቤትም ሆኗል። በ1995 የመጀመሪያውን ማራቶን ውድድሩን በሎስ አንጅለስ ማራቶን በመሮጥ የሚወደውን የአርባ ሁለት ኪሎ ሜትር የሩጫ ታሪኩን አንድ ብሎ የጀመረው ብርቱው ሰው በየዓመቱ በዚህ ውድድር ከሦስት አስርት ዓመታት ላላነሰ ጊዜ ወጥ በሆነ አቋም እየተሳተፈ በስኬት ማጠናቀቅ ችሏል። ይህን ታሪክ በመስራትም የሚስተካከለውን ማግኘት አዳጋች ነው።

ከሚኖርባት ከተማ ሎስ አንጀለስ ማራቶን ባሻገር፣ እንደ ዝነኞቹ የቦስተን፣ ኒው ዮርክ፣ ሺካጎ፣ በርሊንና የጃፓን ማራቶን ውድድሮች በመሳተፍም በርቀቱ በርካታ ጊዜ ሮጦ ማጠናቀቅ ችሏል። በሃምሳ ዓመት እድሜው ሃምሳ የማራቶን ውድድሮችን ሮጦ ማጠናቀቅ የቻለው ጠንካራው የስፖርት ሰው በአጠቃላይ ሰባ አራተኛ የማራቶን ውድድሩን ባሳለፍነው ሐምሌ ወር ሎስ አንጀለስ ዙሪያ በሚገኝ ማራቶን ውድድር አድርጎ ለሚቀጥለው ዓመት በቦስተን ውድድር ላይ እንዲወዳደር የሚያስችለውን መስፈርት አሟልቶ፣ በብቃትና በጥሩ ውጤት ፈጽሟል ቢባል የተጋነነ ሊመስል ይችላል። ግን እሱ አድርጎታል። ይህ ሰው በማራቶን ብቻ የሮጠውን ርቀት ብንደምረው 3108 ኪሎ ሜትር ሮጧል ማለት ነው።

‹‹የስፖርት ፍቅሬን፣ ስሜቴን፣ ጤንነቴንና የመንፈስ ጽናቴን ጠብቄ፣ አልበቃ ብሎኝ ነው እኩል ወደምወደውና እነሆ 28ኛ ዓመት ወዳስቆጠርኩበት የማራቶን ሩጫ ቤተሰብ ተሸጋግሬ እስከዛሬ ድረስ የቀጠልኩበት›› ይላል እዮብ በባህርማዶ ትልቅ ዝና ወዳተረፈበት የማራቶን ቤተሰብ ውድድር እንዴት እንደገባ ሲያስታውስ።

የማራቶን ውድድር እጅግ አድካሚና ትልቅ ጽናትን የሚሻ እንደመሆኑ የዓለማችን ታላላቅ አትሌቶች እንኳን በስፖርቱ በሚቆዩባቸው ዘመናት ሊሮጡ የሚችሉት ውድድር ብዛት የተወሰነ ነው። እዮብ ምናልባትም በዓለም በርቀቱ በርካታ ውድድሮችን በማድረግ ማጠናቀቅ የቻለ ብቸኛው ኢትዮጵያዊ ሰው ሊሆን ይችላል። ወደ ፊትም ተጨማሪ ውድድሮችን የማድረግ አቅምና ተነሳሽነቱ አሁንም ድረስ አብሮት እንዳለ ሲታሰብ ደግሞ ይህን ሰው የተለየ ያደርገዋል። ይህም በርካቶች እሱን እየተመለከቱ የአካል ብቃት እንቅስቃሴን እንዲያዘወትሩ ብርታትና ተነሳሽነት ሆኗቸዋል። የእዮብ ስኬትና ታሪክ ግን በማራቶን ብቻ የተወሰነ አይደለም። ሰማንያ ዘጠኝ የግማሽ ማራቶን ውድድሮችን ጨምሮ በበርካታ የአስርና አምስት ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ውድድሮችን አድርጎ ማጠናቀቅ ችሏል። በነዚህ ሁሉ ውድድሮችም የኢትዮጵያ ስም ከፍ ብሎ እንዲጠራ ሲያደርግ ኖሯል፣ አሁንም እያደረገነው።

## እዮብ ከታላቁ ድል ጀርባ

እዮብ በቅርቡ በዩጂን፣ ኦሬገን ለ18ኛ ጊዜ በተካሄደው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ከምንጊዜውም የላቀ ውጤት ሲያስመዘግቡ ከልኡካን ቡድኑ ጎን ቆሞ የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማበርከት የቀደመው የለም። ውድድሩ ዩጂን ከተማ ይካሄዳል ሲባል የዘወትር የኢትዮጵያ ኩራት የሆኑትን ብርቅዬ አትሌቶች ቤቱ ቁጭ ብሎ በቴሌቪዥን መስኮት ብቻ ለመከታተል ልቦናው አልፈቀደም። 74ኛ ማራቶን ውድድሩን በጥሩ ውጤት ባጠናቀቀ ማግስት ውስጡ ያለው ከፍተኛ ስፖርታዊ ስሜት ገንፍሎ ወጣ። የአገርና የወገን ፍቅር ስሜቱ አላስችል ቢለው አረንጓዴ፣ቢጫና ቀይ ሰንደቅዓላማውን ታጥቆ፣ ቤተሰቡንና ሥራውን ትቶ፣ ለአንድ ሳምንት ያህል በከፍተኛ ወጪ በእንቁዎቹ አትሌቶች መንደር ኦሪገን ከትሟል። የኢትዮጵያ ኩራት የሆኑትን ከዋክብት አትሌቶችን ሩቅ መንገድ ተጉዞ በባዶ እጁ ለመቀበልም አልፈለገም ነበር። የሎስ አንጅለስ ማራቶን ውድድርን ለ27 ተከታታይ ዓመታት በጤና፣ በትጋትና ለተለያዩ የኢትዮጵያ ማህበራዊና ሌሎች በጎ አድራጎት ድርጅቶች "ተወካይ አምባሳደር ሯጭ" በመሆን ያፈራውን እውቅና በመጠቀም አንድ ነገር ለማድረግ ወሰነ። "ለምወዳቸው፣ለማደንቃቸውና ለማከብራቸው ወንድሞቼና እህቶቼ ለሆኑት የኢትዮጵያ ስፖርት ልኡካን(ስፖርተኞች፣ አሰልጣኞች፣ ባለሙያዎችና አመራሮች በጠቅላላ) መተዋወቂያ ናሙና የሚሆን 60 በልዩ መልክ የተዘጋጁ መታሰቢያ ካናቴራዎች (ቲ-ሸርቶች) በሻንጣዬ ሰንቄ፣ በእህቴ ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ በተመቻቸልኝ መድረክ ላይ ለማበርከት በቅቻለሁ" ሲል እዮብ ቡድኑን እንዴት እንደተቀበለ ይናገራል።

ውድድሩ ለአንድ ሳምንት በቆየባቸው ቀናት በየእለቱ የኢትዮጵያን ልኡካን ቡድን በማግኘት፣ በግል ጀግኖቻችንን በመተዋወቅና ሙያዊ ምክር በመለገስ ያላሰለሰ ድጋፍና ፍቅሩን ሲገልጽ ሰንብቷል። ባካባቢው ከነበረው የኢትዮጵያ የዳያስፖራው ማህበረሰብና ደጋፊዎች ጋር በመሆንም ትልቅ የሞራል ድጋፍ አድርጓል። ‹‹ድምጹ እስከሚዘጋ ድረስ በከፍተኛ ፍላጎት ሲጨፍርና ሲጮህ ነበር›› ይላሉ ውድድሩን በአካል ተገኝተው በመመልከት ወደ አገር ቤት የተመለሱ የስፖርት ቤተሰቦች እዮብ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በኦሪገን ተአምር ሲሰሩ የነበረውን ድባብ ሲያስታውሱ። ከድጋፉ ጎን ለጎን አልፎ አልፎ በአሜሪካውያን ተመልካቾችንና ታዛቢዎች ኢትዮጵያንና አትሌቶቹን በተመለከተ ይቀርቡ ለነበሩ ጥያቄዎች የተለያዩ ምላሾችና ማብራሪያዎችን በመስጠት በገጽታግንባታ ረገድ ሲያበረክት የነበረው አስተዋጽኦም ቀላል አልነበረም። ከሶስት አስርት ዓመታት በኋላ በአካል ያገኛትና "እህቴ" የሚላት እንቁዋ አትሌትና የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዘዳንት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ እንዲሁም በልኡካን ቡድኑ መሪ አቶ ተፈራ ሞላ አማካኝነትም እዮብ ጠርቀም ያለውንና አጠቃላይ ይዘት ያለውን የረጅም ጊዜ ሙያዊ ችሎታውንና ልምዱን ለቡድኑ ማካፈል ችሏል። ይህንን ሙያዊ ድጋፉን ወደ ፊትም በነጻ ለማበርከት ዝግጁ መሆኑን በመግለፅ፣ ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጋር በቅርቡ የሥራግንኙነት ለመፍጠር ፍላጎቱን እንደገለጸላቸው ይናገራል። የልኡካን ቡድኑ በዩጂን በነበረው ቆይታ ባደረገው አስተዋጽኦ ግን የረካ አይመስልም። ‹‹በውድድሩ ወቅት ለኢትዮጵያ ልኡካን ቡድን ያደረኩት አስተዋጽኦና ድጋፍ እጅግ በጎላ መንገድነው ብዬ ባላምንም፤ እንደ መነሻና መተዋወቂያ ይሆናል ብዬ በማሰብ የበኩሌን ለማድረግ ሞክሬያለሁ፣በዚህምተደስቻለሁ›› ይላል።

## እዮብ በስኬት ጎዳና

እኤአ በ2004 "በካሊፎርኒያ ግዛት እጅግ አነቃቂው ሯጭ" የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል። ይህም ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ እንደ ሶኮኒ፣ ናይኪ፣ ኤሲክስ፣ ኬ ስዊስ፣ ስኬቸርስ፣ ሆካና ከሌሎችም ዓለም አቀፍ እውቅና ካላቸው ታላላቅ ኩባንያዎች እውቅና አግኝቶና ድጋፍ ተደርጎለት በጋራ ለመስራት አስችሎታል። በደቡብ ካሊፎርኒያ ግዛት በሚካሄዱ በርካታ የጎዳና ላይ ውድድሮች ብዙዎች ተሳታፊ እንዲሆኑ የ"ሌጋሲ ራነርስ" መስራች የሆነው እዮብ በትልልቅ መገናኛ ብዙሃን ትኩረት የሚሰጠው ሰው ነው። የሎስ አንጀለስ የስፖርትና አካል ብቃት መጽሄት ሰፊ ሽፋን የሰጠው ሲሆን፣ ኬኤንቢሲ ቻናል 4 ስፖርትስ፣ኬቲኤልኤፍ ቻናል 5 ቴሌቪዥን በእንግድነት ካቀረቡት መካከል ተጠቃሽ ናቸው። ከነዚህ በተጨማሪም ማህበረሰብ አቀፍ በሆኑ በሌሎች በርካታ የመገናኛ ብዙሃን ፕሮግራሞች ላይም በተደጋጋሚ በክብር እንግድነት መቅረብ ችሏል። እኤአ በ2014 የካሊፎርኒያ ግዛት ምክር ቤት እውቅና የተቸረው ሲሆን፣ የሎስ አንጀለስ ከተማ ምክር ቤት እንዲሁም ከንቲባው ኤሪክ ጋርሴቲ እዮብ ለሃያ ዓመታት በማህበረሰብ ስፖርት እንቅስቃሴ ውስጥ ላበረከተው አስተዋጽኦ እንዲሁም በነዚህ ዓመታት በሃምሳ ዓመት እድሜው ሃምሳ የማራቶን ውድድሮችን ማሳካት በመቻሉ እውቅና ሰጥተውታል።

## እዮብና በጎ አድራጎት

እዮብ በማህበረሰብ ስፖርት ውስጥ ከሚያደርገው ሰፊ እንቅስቃሴ ጎን ለጎን ከበርካታ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር የሩጫ አምባሳደር ሆኖ በመስራት የተለያዩ ድጋፎችን በማሰባሰብ አንቱታን አትርፏል። ከነዚህም መካከልሽርሽበርግ ፓንክሬቲክ ካንሰር ሶሳይቲ፣ ወርልድ ቪዥን፣ የልብ ህሙማን ማህበር፣ ፍሬገነት የህጻናት ትምህርት ፋውንዴሽን እና በሎስ አንጅለስ የኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ ድርጅት (ኢሲኤልኤ) ጋር በተያያዘ ከተለያዩ በጎአድራጎት ድርጅቶች ጋር ገቢ በማሰባሰብ ይሰራል።

## እዮብ በሌሳኛው የሙያ ገጽ

እዮብ የሎስ አንጀለስ የአካል ብቃት አማካሪ ቡድን (LA ENDURANCE SPORTS CONSULTING GROUP) መስራችም ነው። በዚህ ተቋምም ስር ከአካል ብቃትና ከስፖርት ጋር በተያያዘ ለማህበረሰብ ጠቃሚ የሆኑ በርካታ አገልግሎቶችን ይሰጣል። የአትሌቲክስ አሰልጣኝና አማካሪ ሆኖም ይሰራል። በአካል ብቃትና በስፖርቱ ዓለም በየጊዜው እየተጋበዘ አነቃቂ ንግግሮችን ለአማርኛም ሆነ ለእንግሊዝኛ አድማጮች በማድረግ ይታወቃል።

ባለትዳርና የአራት ልጆች አባት የሆነው እዮብ፣ የተለያዩ አትሌቶች ማኔጀርና ተወካይ በመሆንም ይሰራል።በዚህም የተለያዩ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በተለይም በሎስ አንጀለስ ማራቶን እንዲወዳደሩ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ይታወቃል። ከነዚህም መካከል ባለፈው መጋቢት በተካሄደው 37ኛው የሎስ አንጀለስ ዓመታዊ የማራቶን ውድድር ላይ እንዲሳተፉ መንገዱን የጠረገላቸው ሶስት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ብርሃኑ በቀለ በርጋ፣ግዛቸው ሃይሉ ነጋሽና በላይነሽ ሽፈራ ይገዙ ተጠቃሽ ናቸው።

# ዓለም አቀፍ

## አልሻባብ በሞቃዲሾ ሆቴል ላይ በፈጸመው ጥቃት አስር ሰዎች ተገደሉ

የአልሻባብ ታጣቂዎች በሶማሊያ ዋና ከተማ ሞቃዲሾ ውስጥ የሚገኝ አንድ ሆቴልን ጥሰው በመግባት በፈጸሙት ጥቃት ቢያንስ አስር ሰዎች መገደላቸውን ባለሥልጣናት አስታወቁ። ፖሊስ እንዳለው ጥቃት ፈጻሚዎቹ ሃያት ከተባለው ሆቴል ውጪ ሁለት ፈንጂዎችን ካፈነዱ በኋላ ወደ ሆቴሉ ሕንጻ በመግባት ተኩስ ከፍተው ነው ሰዎችን የገደሉት።

ታጣቂዎቹ ወደ ሆቴሉ ከገቡ ከሰዓታት በኋላ በሕንጻው የመጨረሻ ፎቅ ላይ መሽገው መቆየታቸው ተዘግቧል። ጥቃቱን ተከትሎ ወደ ሆቴሉ የተሰማራው የሶማሊያ ልዩ የፖሊስ ኃይል ወደ ሆቴሉ በመግባት በርካታ የሆቴሉ እንግዶች እና ሠራተኞችን ከታጣቂዎቹ ማትረፍ ችሏል።

“በሆቴሉ ውስጥ የነበሩ አብዛኞቹ ሰዎች እንዲወጡ ሲደረግ እስካሁን ቢያንስ አስር ሰዎች ተገድለዋል። የፀጥታ ኃይሎች በሆቴሉ ክፍሎች ውስጥ የመሸጉትን አሸባሪዎች ለመደምሰስ የሚወስዱት እርምጃ ቀጥሏል” ሲሉ ሞሐመድ አብዲካዲር የተባሉ የመንግሥት ባለሥልጣን ተናግረዋል። ቀደም ሲል ከአልሻባብ ጋር ቅርበት ያለው ድረ ገጽ የቡድኑ ታጣቂዎቹ ወደ ሆቴሉ “በኃይል ጥሰው” መግባታቸውን እና “ተኩስ መክፈታቸውን” ጽፎ ነበር።

ጥቃቱ የተፈጸመበት የሞቃዲሾው ሃያት ሆቴል የአገሪቱ ፌደራል መንግሥት ሠራተኞች የሚገናኙበት ታዋቂ ቦታ እንደሆነ ይነገራል።በሞቃዲሾ ውስጥ የአምቡላንስ አገልግሎት የሚሰጠው ተቋም ኃላፊ የሆነው አብዲካዲር አብዲራህማን ለሮይተርስ ዜና ወኪል እንደተናገረው፣ በጥቃቱ የቆሰሉ ዘጠኝ ሰዎችን መውሰዳቸውን ገልጿል።

ፍንዳታ እና የሰዎች ጩኸት የሚሰማበት እንዲሁም ከሆቴሉ ጭስ ሲወጣ የሚያሳዩ ትክክለኛነታቸው ያልተረጋገጡ ምስሎች በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ሲዘዋወሩ ታይተዋል።“ሁለት በመኪና ላይ የተጠመዱ ቦምቦች ሆቴሉን ኢላማ አድርገው ፈንድተዋል” ሲሉ አንድ የፖሊስ መኮንን ለሮይተርስ በሰጡት ቃል ገልጸዋል።

“አንደኛው ከሆቴሉ በር ፊት ያለውን ማገጃ የመታ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የሆቴሉን የውጪ በር መትቷል። አሁን ታጣቂዎቹ በሆቴሉ ውስጥ እንዳሉ እናምናለን።”ከአል ቃኢዳ ጋር ግንኙነት ያለው አል ሻባብ ከሶማሊያ መንግሥት ጋር ለዓመታት የዘለቀ ጦርነት ውስጥ የሚገኝ ታጣቂ እስላማዊ ቡድን ነው።


ጉዳት የደሰበት ሃያት ሆቴል

የአልሻባብ ቡድን አብዛኛውን የደቡብ እና ማዕከላዊ የሶማሊያ ክፍልን በቁጥጥሩ ስር ያስገባ ሲሆን፣ ተጽዕኖውን መቀመጫውን ሞቃዲሾ ውስጥ የሚገኘው የአገሪቱ ፌደራል መንግሥት በመቆጣጠራቸው ስፍራዎች ጭምር ማስፋት ችሏል።በቅርቡ ከቡድኑ ጋር ግንኙነት ያላቸው ታጣቂዎች ሶማሊያ ከኢትዮጵያ ጋር በምትዋሰንባቸው የድንበር አካባቢዎች ጥቃት ሰንዝረው ነበር። ይህም አልሻባብ አዲስ አይነት የጥቃት አቅጣጫን እየተከተለ ይሆን የሚል ስጋትን ፈጥሯል።

አልሻባብ ትናንት አርብ በዋና ከተማዋ ሞቃዲሾ ውስጥ የፈጸመው ጥቃት ባለፈው ግንቦት ወር የተመረጡት ፕሬዝዳንት ሐሰን ሼክ ሞሐመድ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ የመጀመሪያው መሆኑን ቢቢሲ ዘግቧል።

**ከፐብሊክ ሰርቪስ የሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ጋር በመተባበር የሚታተም**

## የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ከፈተ

**ታምራት ተስፋዬ**

በኢትዮጵያ የትራፊክ አደጋ የእለት ተእለት አስደንጋጭ ክስተት ከሆነ ሰነባብቷል። በዚህም በሰው ሕይወት፣ በአካልና ንብረት ላይ ከቀላል እስከ ከባድ አደጋ ይመዘገባል። በየቀኑም በርካቶችም ይሞታሉ፣ ለአካል ጉዳት ይዳረጋሉ። ለወራት ከፍ ሲል ለአመት በሕክምና ተቋማት የሚያሳልፉም ቁጥራቸው እየጨመረ መጥቷል።

የበርካቶችን ቤት ባዶ ያስቀረው፣ ሠርተው መኖር የሚችሉትን ያሰነካከለው የትራፊክ አደጋ ምክንያት፡ ሰዎች ሀገር ሰላም ሁሉ ደህና ብለው በወጡበት ሲቀሩ፤ ከእነ ሙሉ አካላቸው ወጥተው ጉዳት ደርሶባቸው የአልጋ ቁራኛ ሲሆኑ፤ ሠርተው መኖር ሲሳናቸው፤ ሀብት ንብረት እንደ ዘበት ሲወድም መመልከት ከጀመርን ሰንበትበት ብለናል፡

ባለሙያዎች እንደሚያስረዱት፤ ለየተሽከርካሪ ባህሪ ወይም የቴክኒክ ጉድለት፣ ሠዋዊ ባህሪ እና አካባቢያዊ ባህሪ መሠረታዊ የመንገድ ትራፊክ አደጋ ችግሮች ናቸው። ብቃቱ የተረጋገጠ አሽከርካሪን በማፍራት ረገድ የስልጠና ሰጪ ተቃማት ድክመትንም ጨምረው ይጠቁማሉ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በማናቸውም ጊዜያት አደጋ ሊከሰት ይችላል በሚል ዘወትር ጥንቃቄ በማድረግ አደጋን ማስቀረት የቻሉ አሽከርከሪዎች እና አሽከርካሪዎቻቸው አደጋን ባለማድረስ ስማቸውን ሁሌም የሚያሥጠሩላቸው ተቋማትም አሉ። ከእነዚህ ተቋማት መካካል ቀድሞ ስሙ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሰው የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት ነው።

የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት የመንግስት ሰራተኛው በከተማው ባለው የትራንስፖርት አገልግሎት እጥረት ምክንት ይደርስበት የነበረ ወከባ ፣እንግልትና ወጪ በማስቀረት ምቾቱና ድህንነቱ ተጠብቆ በሚፈለገው ጊዜና ፍጥነት በአስተማማኝ ሁኔታ ወደ ሰራና ቤቱ በማድረስ ረገድ አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት መስከረም 5 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ በየጊዜው አደረጃጀቱንና የአገልግሎት አሰጣጡን በማሻሻል ላይ ይገኛል።

በአሁን ወቅትም ለመንግስት ሰራተኞች አገልግሎት ከመስጠት ባሻገርም ከስራ መግቢያና መውጫ ሰዓት ውጪ የዘመኑ የቴክኖሎጂ በተገጠመላቸው ምቾታቸው አስተማማኝ በሆኑ አውቶቡሶች የህዝብ ትራንስፖርት ታክሲ አገልግሎት እየሠጠም ይገኛል።

የአገልግሎት አድማሱን ከፍ በማድረግ ኢትዮጵያ ውስጥ ወደ ተለያዩ ክፍለ አገሮች የትራንስፖርት አገልግሎት ወደ መስጠት ተሸጋግሯል። በአሁን ወቅትም በሌላ ምእራፍ የአሽከርካሪ ማስልጠኛ በመክፈት አገልግሎት መስጠት ጀምሯል።

የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋም የንድፈ ሃሳብ አሰልጣኝ አቶ ያሬድ መስፍን፣የፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት በዘመናዊ መልኩ ባስገነባው አሽከርካሪ ማሰልጠኛ በአውቶሞቢል፣ በህዝብ 1 እና በህዝብ 3 ደረጃ ስልጠና መስጠት ጀምሯል።

በዘርፉ ውስጥ በመሳተፍም የተሻለ ስልጠና በመስጠት ፣በትክክለኛው መንገድ አሽከርካሪነትን ተምሮ እውቀት አግኝቶ ተፈትነው የመንጃ ፈቃድ በማግኘት አደጋን የሚከላከሉ አሽከርካሪዎችን ለማፍራት ልዩ ዝግጅት አድርጋል።

ተቋሙ ስልጠናን ለመስጠት በሚያስችል መልኩ ከሌሎች ተቋማት በተሻለ ሞዴል በተባለ ደረጃ ሁለንተናዊ አደረጃጀቶችን አሟልቷል። የአሽከርካሪ ስልጠና ለመስጠት መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች ሁሉ በማሟላት ከሚመለከታቸው አካላትም ህጋዊ እውቅናን ማግኘት ተችሏል።

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ባወጣው መመሪያ መስረት ሙሉ መስፈርቶችን በማሟላት ሃምሌ ወር ላይም የብቃት ማረጋገጫው ተሰጥቶናል።ስራ ወደ መጀመርም ተሸጋግረናል።

እንደ አቶ ያሬድ ገለጻ፤ በአብዛኛው አሽከርካሪዎች አደጋ የሚያደርሱት በቂ የሆነ የቴክኒክ እውቀት ስለሌላቸው ነው። ተቋሙ በሚሰጠው ስልጠናም በተለይም ቴክኒኪ ላይ ልዩ ትኩረት ይሠጣል።በቴክኒክ ብቁ የሆኑ አሽከርካሪዎች ማፍራት፣በማሽከርከር ሂደት ላይ ሊፈጠር የሚችለውን የተሽከርካሪ አደጋ ለመቀነስ ወሳኝ ሚና አለው።

ስልጠና የሚሰጥባቸው ክፍሎችም የተሻሉና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደራጁ ናቸው።ስልጠናው የሚሰጥባቸው ተሽከርካሪዎችም ዘመናዊ እና አዳዲስ ሞዴሎች ናቸው። ስልጠናው የሚሰጡት አሰልጣኙም በቂ እውቀት እና የረጅም አመት የስራ ልምድ ያላቸው ናቸው። ከዚህ ባሻገር በስነምግባርም የታነፁ ናቸው።ይህም የሰልጠናውን ሂደት ውጤታማ በማድረግ ረገድ ጉልህ አቅም የሚፈጥር ነው።

በአሁን ወቅት ከተለያዩ ማሰልጠኛ ተቀማት ወጥተው ማሽከርከር የጀመሩ አብዛኞቹ አሽከርካሪዎች በብቃት ማነስ እና በቸልተኝነት አደጋን እያደረሱ ናቸው።በዚህም በርካቶች ውድ ህይወታቸውን እየተነጠቁ ፣ለአካል እና ስነ ልቦና ጉዳት እየተዳረጉ ናቸው። በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰ ይገኛል።

በስልጠናው ሂደት እኛ ብቁ ሙያተኞችን በማፍራት ኢትዮጵያ ውስጥ የሚከሰት አደጋን ዜሮ የማድረግ ግብን አስቀምጠናል።የእኛ ተሽከርሪዎች በከተማው ውስጥ ለሲቪል ሰራተኛውና ለማህበረሰቡ ለተለያዩ የትራስፖርት አገልግሎት ይሠጣሉ። አሽከርካሪዎችም አደጋ ባለማድረስ ስማቸው ቀድሞ የሚጠራ ነው።ይሕን ልምድ ሌሎች ተቋማት ብሎም ባለድርሻ አካላት ሊወስዱት ይገባል።

ስልጠናው ፈልገው ወደ ተቋሙ የሚመጡ ሰልጣኝ ማሟላት የሚጠበቅባቸው መስፈርቶች አሉ።በየደረጃው የተቀመጡ መስፈርቶ አሉ።እድሜ ቀዳሚ ሲሆን 18 አመት በላይ መሆን ይጠበቅበታል።የትምህርት ማስረጃ ማቅረብ እንዲሁም የጤና ምርመራ ይዞ መቅረብ ግድ ይላል።

ከዚህ ባሻገር የታደሰ መታወቂያ ይዞ መምጣትም ሊረሳ አይገባም።መታወቂያ የሌላቸው የልደት ሰርተፍኬት ወይንም ፓስፖርት ሊኖራቸውን ይገባል።ይህን የሚያሟሉም አምስት ጉርፍ ፎቶ ግራፍ ይዘው መምጣት ይጠበቅባቸዋል። ይህን ማሟላት የሚችሉም ሜክሲኮ አደባባይ አልሳም ጨለለቅ ህንፃ ፊት ለፊት በሚገኘው የማሰልጠኛ ማእከሉ ስልጠናው ለማግኘት መመዝገብ የሚችሉ ይሆናል።

በዚህ ዘርፍ ላይ ተሰማርተው ስልጠና የሚሰጡ አካላት ገንዘብን ብቻ ታሳቢ ማድረግ የለባቸውም። ይልቁንም በስነ ምግባር የታነፁ፣በቂ እውቀትና እና የቴክኒክ ክህሎት ያላቸው ሰልጣኞችን ለማፍራት ልዩ ትኩረት መስጠት ይኖርባቸዋል።ይህ ማድረግ ሲቻል በአሁን ወቅት በየእለቱ እየተስተዋሉ የሚገኙ አሳዛኝ እና አሰቃቂ የትራፊክ አደጋዎችን መቀነስ ይቻላል።




# ቡሔ በሉ ልጆች ሁሉ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ሰላም ልጆች! እንዴት ሰነበታችሁ፤ ሳምንቱ እንዴት አለፈ? ጥሩ ነበር አይደል? መቼም አዎ እንዳላችሁኝ አልጠራጠርም፡፡ ምክንያቱም ቀናችሁን ሁሉ ደስተኛ ሆናችሁ ከቤተሰባችሁ ጋር እያሳለፋችሁ እንደሆነ ስለምገምት ነው፡፡ በተለይ ይህ ወቅት ደግሞ ለልጆች ልዩ ወር እንደሆነ አስባለሁ፡፡ ምክንያቱም በዚህ ወር በርካታ ልጆችን የሚያስደስቱ ክንዋኔዎች የሚደረግበት ነው፡፡ አንዱ የቡሔ በዓል የሚከበርበት ጊዜ መሆኑ ሲሆን፤ በዓሉን ለማክበር የተለያዩ ዝግጅቶችን ስታደርጉ እንደሰነበታችሁ አምናለሁ፡፡

በቡሔ ጊዜ ጅራፍ ማጮህ የሚፈቀድበት እለት በመሆኑ አዲስ ጅራፍ መስራታችሁ አይቀርም፡፡ እናንተ ባትችሉበት እንኳን ሌሎች ልጆች እንዲሰሩላችሁ ታደርጋላችሁ፡፡ ይህ ደግሞ ልምድን መካፈል ጭምር ያስተምራችኋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የቡሔ እለት በየሰው ቤት እየሄዳችሁ የምትጨፍሩበት በመሆኑ ልዩ ቀናችሁ ነው፡፡ ምክንያቱም የዚህን ጊዜ ብዙ ነገር ታገኛላችሁ፡፡ አንዱ ስጦታችሁን መለየታችሁ ሲሆን፤ በጊዜው ለጭፈራው ቡድን ስትመሰርቱ እከሌ ይህንን አድርግ ትባባላላችሁ ትመዳደባላችሁ፡፡ እናም እናንተ የሚደርሳችሁ ሥራ ተሰጥኦአችሁ እንደሆነ ትረዳላችሁ፡፡ ለምሳሌ፡- ገንዘብ ያዥ ከሆናችሁ ታማኝ መሆናችሁን፤ መዝፈን ከሆነ ድርሻችሁ ደግሞ ድምጻዊ መሆናችሁን ታረጋግጣላችሁ፡፡ በተመሳሳይ ማስተባበር ላይ ከሆነ ምድባችሁ የአለቅነት ቦታ ይዋጣላችኋል ማለት ነው፡፡

ልጆች እዚህ ላይ ልብ ልትሉት የሚገባው አንድ ነገር አለ፡፡ ለምን ለእኔ ምንም ሥራ አልተሰጠኝም ማለት የለባችሁም፡፡ ምክንያቱም በቡድን ውስጥ ሁሉም አለቃ መሆን አይችልም፡፡ ሁሉም ገንዘብ ያዥና ሌላም ሌላም ሊሆን አይችልም፡፡ መሳተፍና ለሌሎች ድምቀት መሆንም





አንዱ የሥራ ድርሻ ነው፡፡ ስለዚህም በዚያ ቡድን ውስጥ ምንም ኃላፊነት ያልተሰጠው ሰው ቦታው ስለማይበቃ እንጂ ምንም ተሰጥኦ ስለሌው እንዳልሆነ መረዳት አለባችሁ፡፡ በዚያ ላይ እናንተ ባትኖሩ ኖሮ ጭፈራው አይከናወንም፡፡ ምክንያቱም ማን ሊያጨበጭምና ሊያጅብ ይችላል? ስለሆነም ይህንን ኃላፊነት በማግኘታችሁ ደስ ሊላችሁ ይገባል፡፡

ሌላው በቡሔ ቀን ደስ የሚያሰኘው ነገር ብዙዎች ጋር በልጅ ልክ የሚመጣው የሙልሙል ዳቦ ጉዳይ ነው፡፡ ያው ቀደም ባለው ጊዜ ልጆች በየቤቱ ሲጨፍሩ ጭምር ሙልሙል ዳቦ ይሰጥ ነበር፡፡ አሁን ግን ነገሮች ተገልብጠው ብር ካልሆነ አንቀበልም አሉ እንጂ፡፡ ነገር ግን በየቤቱ የቡሔ ተብሎ የሚሄደው ጥንትም ነበር፡፡ እናም ያንን እየገመጡ መጨፈር ልዩ ደስታን ከሚሰጠው መካከል ነው፡፡

ልጆች ሌላው የቡሔ ጥቅም ነጻነታችሁን የምታገኙበት ጊዜ መሆኑ ነው፡፡ የዚያን ጊዜ አባቶች ይመርቋችኋል እንጂ አይቆጧችሁም፡፡ እንደውም በቡሔ ጨዋታ ምን እንደሚባል ታውቃላችሁ? « በቡሔ ጨዋታ አይቆጡም ጌታ» ነው፡፡ ስለሆነም ጨፍራችሁ ሳይሰጣችሁ ሲቀር በግጥማችሁ ስትሸነቁጧቸው የማይቆጧችሁ ለዚህ ነው፡፡

በቡሔ እለትና ከዚያ በኋላ ሰማይ ከጭጋግአማነት ወደ ብሩህነት ይለወጣል፡፡ የክረምቱ አፈና ተወግዶ የብርሃን ወገግታም ይመጣል፡፡ የዚህን ጊዜ ወንዙ ይጎላል፡፡ ዝናብም አይከብድም፡፡ እናም ለመጫወት ምቹ ጊዜ ይፈጥርላችኋልና እንደልባችሁ ችግር ሳገጥማችሁ ትቦርቃላችሁ፡፡ ስለዚህም ይህ የብራ ጊዜ የልጆች የነጻነት ወቅት እንደሆነም ይነገራል፡፡

ልጆች ለመሆኑ የቡሔን ትርጉም ታውቃላችሁ? ትንሽ ነገር ልበላችሁና ሃሳቤን ልቋጭ፡፡ እናንተ ደግሞ ትርጉሙን መሰረት በማድረግ የምታገኙትን ጥቅም እያሰባችሁ በዓሉን አክብሩ፡፡ ሌሎች ልጆችም በባህሉና በወጉ መሰረት እንዲያከብሩ ምክራችሁን ለግሱ፡፡ ምክንያቱም ባህሉን ባለማወቅ በጭፈራ ግጥሞቻቸው ጭምር እየተበላሹ ስለሆነ ማስተካከል አለባችሁ፡፡

የቡሔ በዓል መሠረቱ የክርስቲያን እምነት ተከታዮች ሲሆን፣ ደብረ ታቦር እየተባለም ይጠራል፡፡ በግዕዝ የታቦር ተራራ ማለት ነው፡፡ ደብረ ታቦር ወይንም የታቦር ተራራ ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን ይዞ ወደ ተራራው የወጣበትና ፊቱ እንደፀሐይ የበራበት ልብሱም እንደብርሃን ነጭ የሆነበት ቦታ ነው፡፡ ይህ ቦታ ጌታ ብርሃነ መለኮቱን የገለጠበት ተራራ ነውም ይባላል። በአገራችን ደግሞ ሁሉም እንዲያከብረው ተደርጎ በባህል ጭምር የታሰረ በዓል ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ በዓል የክረምቱ አፈና ተወግዶ የብርሃን ወገግታ የሚታይበት ጊዜን የሚነግረን ነው፡፡

ቡሄ ማለት ከትርጉሙ ብንነሳ ገላጣ፣ ብራ ማለት ነው፡፡ እንደውም በጨዋታው ሳይቀር እንለዋለን፡፡ « ቡሔ መጣ ያ መላጣ፤ ቅቤ ቀቡት እንዳይነጣ» ይህ ማለት ደግሞ በሚገላለጥበት ጊዜ አቧራ እንዳይጠጣ ለምለሙን አልብሱት እንደማለት እንደሆነም ይነገራል፡፡ ልጆች ይህ በዓል ከላይ እንዳልኳችሁ በገጠር አካባቢ በስፋት ይከበራል፡፡ በየከተማም ቢሆን ይከበራል፡፡ ነገር ግን ከገጠሩ አንዳንድ ነገሮች ይለያያሉ፡፡

አንዱ እንደገጠር ልጆች ጅራፍ አለመገመዳቸው ሲሆን፤ በዚያ ፋንታ ርቺት ማጮሃቸው ነው፡፡ በየቤቱ እየሄዱ ሲጨፍሩ ግጥሞቻቸውም ቢሆኑ ባህሉን የጠበቁ አይደሉም፡፡ በዚህ ወቅት እናቶች ሳይቀሩ ለበዓሉ ልዩ ዝግጅት ያደርጋሉ፡፡ ምክንያቱም «ቡሔ» ለሚሉ ልጆች ሙልሙል ዳቦ መስጠት ግድ ነው፡፡ በከተማ አካባቢ ግን ይህ አይፈጸምም፡፡ ምክንያቱም ልጆች ሲጨፍሩ የሚፈልጉት ብር እንጂ ዳቦ አይደለም፡፡ ነገር ግን እንደ ገጠሩ ልጅ በአንድነት ተሰባስበው ችቦ እያበሩ ይጨፍራሉ፡፡ አያችሁ ልጆች የገጠርና የከተማ የቡሔ አከባበር ልዩነቶችን የሚያስተናግድ ነው፡፡ እናም እናንተ ማወቅ ያለባችሁ ባህሉን አለመልቀቁን ነው፡፡ ከባህሉ ውጪ የሚያደርጉ ልጆችን መምከር አለባችሁ፡፡ ከላይ አደራ ያልኳችሁም ለዚህ ነው፡፡ በሉ ለዛሬ በዚህ እንሰነባበት በቀጣይ ሳምንት ሌላ ጉዳይ ይዤላችሁ እንደምቀርብ ቃል በመግባት መልካም በዓል እንዲሆንላችሁ ተመኘሁ፡፡ ሰላም!!

# ስፖርት





# ተሸንፎ ማሸነፍ

**ቦጋለ አበበ**

ብርቱ ፉክክር በነገሰባት የውድድር ዓለም ጠንካራው ደካማውን ጥሎ ሲያልፍ ማየት የተለመደ ነው። ዛሬ ደካማ የሆነው ነገ ጠንክሮ ወደ አሸናፊነት ለመምጣት የሚደረገው ትንቅንቅም በዚያው ልክ ሃያል ነው። አሸናፊነት የሰው ልጆች ተፈጥሯዊ ባህሪ ነው። ማንም ሰው ማሸነፍን እንጂ መሸነፍን አይፈልግም። አሸናፊነት ይዞት የሚመጣው ተድላና የተመቻቸ አለማዊ ኑሮ አለና የብዙዎች መሻት ቢሆን አይገርምም። ብዙዎች «ዓለም ለአሸናፊዎች እንጂ ለደካሞች ቦታ የላትም» ብለው እንዲያምኑ የሚያደርጋቸውም ይህ የዓለም እውነታ ነው።

ስፖርት የውድድር አውድማ ነው። አሸናፊዎች ከተሸናፊዎች የሚለዩበት መድረክ። በስፖርታዊ ውድድሮች ወደ ፍልሚያው ሜዳ የሚገቡ ሁሉ አሸናፊነትን እንጂ ሽንፈትን አልመውና አቅደው ሊመጡ አይችሉም። ስፖርተኞች የትኛውንም ፉክክር በአሸናፊነት ለመወጣት ከዝግጅት ጀምሮ ብዙ ይለፋሉ። በማሸነፋቸው የሚያገኙትን ጥቅምና ሽልማት እያለሙም ሌት ተቀን ይዘጋጃሉ። የልፋትና ድካማቸውን ፍሬም የሚያፍሱት በውድድር በሚያስመዘግቡት ውጤት ነው። ስለዚህ አንዴ ወደ ውድድር ከገቡ ከተቻለ በአቅምና ብቃታቸው ካልሆነም የተፎካካሪያቸውን ደካማ ጎን ተጠቅመው ለማሸነፍ ይጥራሉ። ይህ የስፖርቱ ዓለም ሃቅ ቢሆንም አንዳንዴ የተገላቢጦሽ ታሪኮች ይከሰታሉ።

ልፋትና ጥረትን፣ ህልምና የረጅም ጊዜ እቅድን ሁሉ ወደ ጎን ትተው ማሸነፍ የሚችሉትን ውድድር የሚሸነፉ የስፖርቱ ዓለም በታሪክ የማይረሳቸው የብዙዎች ተምሳሌት ሆነው ይገኛሉ። እነዚህ ታሪክ የማይዘነጋቸው ስፖርተኞች ስማቸውና መልካም



**ኬንያዊቷ አትሌት ጃኩሊን ኔይቲፔ ኪፕሊሞ የስፖርታዊ ጨዋነት ጥግ ማሳያ ተደርጋ በጉልህ ትጠቀሳለች፣**

ተግባራቸው ከአሸናፊዎች ተለይቶም በወርቅ ቀለም ይጻፋል። ውድድር ማሸነፍ ባይችሉም የዓለምን ሕዝብ ልብ ማሸነፍ ከቻሉ ታሪካዊ ስፖርተኞች አንዷ ኬንያዊቷ አትሌት ጃኩሊን ኔይቲፔ ኪፕሊሞ በጉልህ ትጠቀሳለች።

እኤአ በ2010 ዤንካይ ዓለም አቀፍ የማራቶን ውድድር ላይ ይህች ኬንያዊት አትሌት የፈጸመችው መልካም ተግባር ለዓለም ሕዝብ ተሸንፎም ማሸነፍ እንደሚቻል ትምህርት የሰጠ ነበር። በዛሬው የስፖርት ማህደር አምዳችን ይህ አስተማሪ የስፖርቱ ዓለም ድንቅ ታሪክና ክስተት ተዳሷል።

ኪፕሊሞ በርካታ ዶላሮችን ለሚያሳቅፈው ውድድር እንደማንኛውም አትሌት ለማሸነፍ በቂ ዝግጅት አድርጋ ወደ ውድድር ገብታለች። የአርባ ሁለት ኪሎ ሜትሩን ፈታኝ ፉክክርም በትልቅ የራስ መተማመን መምራት የጀመረችው ገና በጊዜ ነው። አሸናፊነትን በውስጧ እያሰበች የመጨረሻውን ክር በድል ለመበጠስ የሚያስችላት ሙሉ አቅምም አላት። ገና ውድድሩ አስረኛ ኪሎ ሜትር ላይ እያለ ጀምሮ ግን አንድ ነገር ማስተዋል ጀመረች። ከማራቶን ውድድሩ ጎን ለጎን አካል ጉዳተኞችም የራሳቸውን ውድድር በተመሳሳይ ጎዳና ላይ እያካሄዱ ነው። በዚህ ውድድር ላይ እየተሳተፈ የሚገኝ አንድ ቻይናዊ አካል ጉዳተኛ ከአስረኛው ኪሎ ሜትር ጀምሮ በውድድሩ ላይ ከነበረው ከፍተኛ ሙቀት ጋር ሲታገል አስተዋለችው። አካል ጉዳተኛው አትሌት ውድድሩን አላቋረጠም፣ በጽናት ወደ ፊት መግፋቱን ተያይዞታል። የሮጡት ኪሎ ሜትር እየጨመረ ሲሄድ ከፍተኛው የሙቀት መጠን የሚፈጥረው የውሃ ጥም ስቃይም እየጨመረ ሄዷል። ይህ አካል ጉዳተኛ አትሌት የደረቀ ጉሮሮውን እንደ ሌሎቹ አትሌቶች በውሃ ለማርጠብና ጥሙን አስታግሶ በተሻለ ብርታት ወደ ፊት ለመግፋት አንድ የሚያግደው ችግር አለ። አትሌቶች በተወሰነ ርቀት ውሃ አንስተው ከሚጎነጩበት ስፍራ የተዘጋጀውን ውሃ ለማንሳት ሁለት እጅ ስለሌለው ተቸግሯል። ቆም ብሎ ውሃውን ለማንሳት ቢሞክር ወደ ኋላ መቅረቱ ነው። የወሰደው አማራጭ የውሃ ጥም ስቃዩን ችሎ በደረቀ ጉሮሮው ወደ ፊት መግፋት ነው።

ይህ አካል ጉዳተኛ አትሌት በዚህ ሁኔታ ውስጥ እየታገለ መሆኑን ኬንያዊቷ አትሌት ከመጀመሪያ ጀምሮ አስተውላለች። ውድድሩ ሰላሳ ስምንተኛ ኪሎ ሜትር ላይ ደርሷል። ኬንያዊቷ አትሌትም ውድድሩን ለማሸነፍ ከፊት እየመራች ከአራት ኪሎ ሜትር ያልበለጠ ርቀት ይቀራታል። እየሮጠች ባለችበት ፍጥነት ከቀጠለች ውድድሩን ለማሸነፍ የሚያስችላት እድል ሰፊ ነው። ትንሽ ከዘገየች ግን ከኋላ ለምትከተላት ተፎካካሪዋ አሸናፊነቱን አሳልፋ ትሰጣለች። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለች ግን አንድ ነገር ውስጧን ይታገለዋል። በውሃ ጥም የራደው አካል ጉዳተኛ አትሌት ህመሙ ተሰማት። ከአስር ኪሎ ሜትር ጀምሮ ሁኔታውን ያስተዋለች ቢሆንም ህሊናዋ በስተመጨረሻ በዝምታ እንድታልፈው አልፈቀደላትም። በዝምታዋ ቀጥላ የራሷ ውድድር ላይ ብቻ ትኩረት አድርጋ እንዳትቀጥል የሚያግዳት አንዳች አለማዊ ህግ የለም። ከአለማዊ ህግ በላይ ህሊና የሚባል ታላቅ የተፈጥሮ ህግ ግን ከዚህ በላይ በዝምታ እንድትጓዝ አላደረጋትም። የአሸናፊነት ግስጋሴዋን ገታ አድርጋ ለተጠማው አካል ጉዳተኛ አትሌት በሚመቸው መንገድ ውሃ አንስታ ጥማቱን እንዲያስታግስ ረዳችው። ይህም ቅጽበት አሸናፊ ሆና ማጠናቀቅ የምትችለውን ውድድር ሁለተኛ ሆና እንድትፈጽም አደረጋት።

ኪፕሊሞ ለህሊና ዳኝነት ተገዝታ ዋጋ ከፈለች። ቀዳሚ ሆና በማጠናቀቅ የምታገኘውን የገንዘብ ሽልማት አጣች። ከአሸናፊነት የሚገኝን ክብር አሳልፋ ሰጠች። በውድድር አውድማ ተሸነፈች። ነገር ግን በመልካም ተግባሯ የአለምን ሕዝብ ስሜት አሸነፈች። ከውድድሩ በኋላም ባሉት ቀናት የዓለም ሕዝብ ትኩረት ቀዳሚ ሆና ባጠናቀቀችው አትሌት ላይ አልነበረም። ማህበራዊ ድረ ገጾችና ታላላቅ ሰዎችም «ኬንያዊቷ አትሌት ተሸንፋ ሰብአዊነት አሸነፈ» ሲሉ ሙገሳቸውን አዥጎደጎዱላት።

ስፖርታዊ ጨዋነት የስፖርት ሥነ ምግባራዊ ገጽታ ነው። እንደ ፍትሃዊ ጨዋታ፣ ታማኝነትና ለተቃዋሚዎች፣ ለቡድን አጋሮች፣ ለደጋፊዎችም ጭምር አክብሮት ባላቸው መልካም ባህሪያት ጥምረት ይታያል። ስፖርታዊ ጨዋነት በተሸናፊነት ጊዜም ቢሆን ጨዋነትን በማሳየትና ከሌሎች ጋር ባለን ግንኙነት ራስን በመግዛት ማሳየት ይቻላል። በስፖርት ውስጥ የሚደረጉ ማንኛውም የሞራል ተግባራት ስፖርታዊ ጨዋነትን የሚወክሉ ሲሆን፤ እንደ ደጋፊም ቢሆን የስፖርታዊ ጨዋነት መንፈስን መጠበቁ በእኛና በተቀናቃኞቻችን መካከል ሰላምን፣ ፍቅርንና መከባበርን ያቆያል። የኬንያዊቷ አትሌት ተግባር ግን ስፖርታዊ ጨዋነት ከዚህም እንደሚልቅ ማሳያ ነው።